አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

# አዲስ ልሳን

ቅጽ 32 ቁጥር 3547 | ቅዳሜ ህዳር 6 ቀን 2018 ዓ.ም | ዋጋው 10.00 ብር




# ኢትዮጵያ በአየር ንብረት ለውጥ

## “ኮፕ 32ን ያካተተ ጠንካራ እና ትርጉም ያለው ውጤት ለማምጣት ቁርጠኛ ነች”

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

➜ 5




ፎቶ- ከገፀ ድር

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ኢትዮጵያ የኮፕ 32 ጉባኤ አዘጋጅ ሆና በመመረጧ ምስጋና እና መልዕክት አስተላልፈዋል

### ከህብር የተገኘ በረከት

➜ 4



ፎቶ- ከገፀ ድር

አዲስ አበባ የሁሉም ኢትዮጵያዊ የጋራ መኖሪያ ቤት መሆኗ ዘርፈ ብዙ ትሩፋቶችን አጎናጽፏታል

### ተቋማቱ ከሰልጣኞች ምዝገባ ጋር በተያያዘ ምን ገጠማቸው?

➜ 9




ፎቶ በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል

በተለያየ የሙያ መስኮች ስልጠና በመስጠት የሚታወቀው የንፋስ ስልክ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ

### አብሮነት በስዕል ሲገለጥ

➜ 11



ፎቶ- ከገፀ ድር

ኢትዮጵያዊ አብሮነትን ከሚያሳዩ ስራዎች መካከል

# የኢትዮጵያ የባህር በር ጥያቄ

## “ሁሉንም አሸናፊ የሚያደርግ መንገድ ነው”

የህግ ባለሙያው አቶ ኪያ ፀጋዬ

**በስንታየሁ ምትኩ**

ኢትዮጵያ ለዘመናት የራሷ የሆነ የባህር በር ነበራት፡፡ ይህም ከዓለም ጋር በተሻለ የመገናኘት፣ የመነገድ፣ የማደግ... እንቅስቃሴዋ ላይ አዎንታዊ አስተዋጽኦ ማድረጉን ሰነዶችና የዘርፉ ምሁራን የሚያብራሩት ሃቅ ነው፡፡ የባህር በሯን ካጣችበት ከ1983 ዓ.ም ወዲህ እያሳደረ እና በቀጣይ ሊያሳድር የሚችለውን ተጽዕኖ ከግምት በማስገባት ጉዳዩ መልስ እንዲያገኝ ማድረግ ውዴታ ሳይሆን ግዴታ እየሆነ መጥቷል፡፡ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር

ወደ ገጽ 6 ዞሯል

ፎቶ- ከገፀ ድር

የህግ ባለሙያው አቶ ኪያ ፀጋዬ

# በአንድ ጀንበር የስራ ዕድል ፈጠራ መርሃ ግብሩ

- 20 ሺህ 900 ዜጎች ወደ ስራ ይገባሉ
- ባለፉት አራት ወራት ብቻ 137 ሺህ 111 ዜጎች የስራ ዕድል ተፈጥሮላቸዋል
- ከ2013 እስከ 2017 ዓ.ም ብቻ ለ1 ሚሊዮን 841 ሺህ 532 ዜጎች የስራ ዕድል ተፈጥሯል

**በመለሰ ተሰጋ**

ወጣት ይሄይስ መንግስቱ በጋርመንት አካባቢ በአንድ የኮንስትራክሽን ድርጅት በረዳት የማሽን ኦፕሬተርነት ሙያ ተቀጥሮ እየሰራ ነው፡፡ ቀደም ሲል ስራን በማማረጥ ብዙ ጊዜውን እንዳሳለፈ አስታውሶ፣ አሁን ግን በመዲናዋ እየተከናወኑ

ወደ ገጽ 3 ዞሯል



# ርዕሰ አንቀፅ




## የሚፈጠሩ የቱሪዝም እድሎችን ለመጠቀም ከወዲሁ ይሰራ!

ያልተነካ እምቅ ሀብት፤ የሀገራችን የቱሪዝም ዘርፉ መገለጫ ከሆነ ቆይቷል፡፡ በሚያስገኘው ዘርፈ ብዙ በረከት "ጭስ አልባው ኢንዱስትሪ" እንደሆነ ቢነገርለትም ለዘርፉ የነበረን ቁንጽል እይታ ባለን ልክ እንዳንጠቀም እንዳደረገን የቅርብ ግዜ ትውስታ ነው፡፡ ኢኮኖሚው ከግብርና ጥገኝነት ወደ ብዝሃ ኢኮኖሚ ከተቀየረበት ከባለፉት ጥቂት ዓመታት ወዲህ ዘርፉ ላይ እየታየ ያለውን መነቃቃት አጠናክሮ ማስቀጠል ያስፈልጋል፡፡

አዲስ አበባ ስሟን የሚመጥን ስራ መስራት ላይ ዳተኛ ሁና መቆየቷን ብዙዎች ይስማሙበታል፡፡ ከተማዋ የአፍሪካ መዲና፣ የዲፕሎማቲክ ማህበረሰቡም መቀመጫ ናት፡፡ የአፍሪካ ህብረትን ጨምሮ የተለያዩ አህጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ተቋማት ይገኙባታል፤ ስብሰባዎችም ይካሄዱባታል፡፡ ሆኖም በቂ እና ደረጃቸውን የጠበቁ ሆቴሎች ቁጥር ከዚህ ግባ የሚባል አልነበረም፡፡ ጽዳቷ እና የመዝናኛ አማራጮቿ እንግዶች ቀናቸውን አራዝመው እንዲጎበኟት የሚገፉፉ አልነበሩም፡፡ ይህ ደግሞ የቱሪስቶች መሸጋገሪያ እንጂ መዳረሻ እንዳትሆን አድርጓት ቆይቷል፡፡

አሁን ላይ እንደ ሀገር እየተከናወኑ ያሉት ዘርፈ ብዙ ስራዎች ዓለም አቀፍና አህጉር አቀፍ ስብሰባዎች እንዲበራከቱ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ ኢትዮጵያ ባለፉት 6 ዓመታት ከ48 ቢሊዮን በላይ ችግኞችን መትከል ችላለች፡፡ በወንዝ ዳርቻዎች ልማት ሰፋፊ የአካባቢ ጥበቃ ስራ እያከናወነች ነው፡፡ ግዙፍ ታዳሽ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫዎችንም እየገነባች ትገኛለች፡፡ እነዚህ እና መሰል ተግባራት ከሁለት ዓመት በኋላ እ.ኤ.አ. በ2027 የኮፕ 32 ጉባኤን እንድታስተናግድ የበኩላቸውን ሚና ተጫውተዋል፡፡ ከዚህ በፊት የተካሄዱት ስብሰባዎችም የዚሁ ነጸብራቅ ናቸው፡፡ ለዚህ ግን አሁንም ምቹ መደላድሎችን እየፈጠሩ፣ የሚፈጥረውንም ዕድል አሟጦ እየተጠቀሙ መሄድ ያስፈልጋል፡፡

በኮሪደር ልማቱ ተሞክሮ የሚቀሰምባቸው ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ የአዲስ አበባ ከንቲባ ጽህፈት ቤት መረጃ፣ በ1ኛ እና በ2ኛ ዙር የኮሪደር ልማት ስራዎች ከተጠናቀቁ መሰረተ ልማቶች መካከል 342 ኪሎ ሜትር የእግረኛ መንገድ፣ 185 ኪሎ ሜትር የተሽከርካሪ መንገድ፣ 241 ኪሎ ሜትር የሳይክል መንገድ፣ ዘመናዊ የመንገድ መብራቶች፣ በርካታ የህዝብ መገልገያ እና መዝናኛ ቦታዎች፣ በርካታ የሕዝብ አገልግሎት መስጫ መሰረተ ልማቶች፣ 101 የህፃናት መጫወቻዎች፣ 155 የስፖርት ማዘውተሪያዎች፣ 153 ዘመናዊ ፓርኪንግ እና ተርሚናሎች እንዲሁም 210 የሕዝብ መፀዳጃዎች ተገንብተዉ አገልግሎት መስጠት መጀመራቸውን ያመላክታል፡፡ ይህን ወደ ሌሎች የከተማዋ እና የሀገሪቱ አካባቢዎች እንዲሰፋ ማድረግ ይገባል፡፡

የከተማዋ የቱሪዝም አቅም አሁን ካለውም በላይ መጎልበት አለበት፡፡ በኮንፍረንስ ቱሪዝሙም እየተፈጠሩ ያሉ ዕድሎችን እና መልካም አጋጣሚዎች ሳይባክኑ መጠቀም ይገባል፡፡ ለዚህ ሆቴሎችን ጨምሮ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ወቅቱን በዋጀ መልኩ በርከት ባለ ቁጥር እንዲስፋፉ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ለስብሰባ የሚመጡ እንግዶች ከተማዋን እንዲጎበኙ እየተደረገ መሆኑ የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖራቸው የሚያደርግ ነውና ተጠናክሮ መቀጠል መቻል አለበት። የቱሪዝም ባለሙያዎችም ለጎብኚዎች በቂ ግንዛቤ የሚያስጨብጥ ስንቅ መያዝ የግድ መሆኑን ከግምት ማስገባት አለባቸው፡፡ እንደ ሀገር ኢኮኖሚያዊ እይታ ጭምር እንዲይዝ ከተደረገው ቱሪዝም በሀብታችን ልክ ለመጠቀም የተጀመረውን ርብርብ አጠናክሮ ማስቀጠል ግድ ይላል፡፡ የኮፕ 32 አይነት ለኮንፍረንስ ቱሪዝም አቅም የሚፈጥሩ ዕድሎችን በአግባቡ ለመጠቀምም ከወዲሁ ይሰራ!

# የእኔ እይታ

ይህ ገፅ ዜጎች በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ሃሳባቸውን በነፃነት የሚያንፀባርቁበት ሲሆን ይህም የጋዜጣዋን የዝግጅት ክፍል አቋም አይገልፅም።

## አውቶብሶችን የናፈቁ መንደሮች

### በቻቺ ከለሚ ኩራ

እውነት ለመናገር መንግስት የህብረተሰቡን የትራንስፖርት ችግር ለማቃለል በተለይ በአዲስ አበባ ከተማ ደረጃ ዘርፈ ብዙ ተግባራትን እያከናወነ ነው፡፡ የከተማ አስተዳደሩ አንበሳ የከተማ አውቶብስ እና ሸገር የብዙሃን ትራንስፖርትን አጣምሮ ለያዘው የአዲስ አበባ ከተማ የአውቶብስ አገልግሎት ድርጅት ከሚያደርገው ድጎማ ባሻገር ሌሎች አዳዲስና ዘመናዊ አውቶብሶችንም ወደ ስምሪት እያስገባ መሆኑ የሚያስመሰግን ነው፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ የአውቶቡስ አገልግሎት ድርጅት አውቶብሶች የማይደርሱባቸው የከተማዋ ክፍሎች የሉም ብል ያጋነንኩ አይመስለኝም። እነኝህ የህዝብ ትራንስፖርቶች መስጫ አውቶብሶች ከመሃል ከተማ ተነስተው የከተማዋን ጫፍ እና አጎራባች አካባቢዎችን ጭምር ሲያካልሉ የሚውሉ ናቸው፡፡ በዚህም በየቀኑ በሺዎች የሚቆጠሩ የከተማዋን ነዋሪዎች ሲያገለግሉ እንደሚውሉም አምናለሁ።

ምንም እንኳን የከተማ አውቶብሶች ይህን ህዝባዊ አገልግሎት ቢሰጡም፣ በአንዳንድ አካባቢዎች ግን ተገልጋይን የሚያማርሩ የአሽከርካሪ ባህርያትና የስምሪት ሁኔታዎች ማጋጠማቸው አልቀረም። በአንዳንድ አዳዲስ የጋራ መኖሪያ መንደሮች ያለው የስምሪት ሁኔታ መፈተሽ ያለበት ሆኖ ይሰማኛል፡፡

ለምሳሌ እኔ በቅርብ በማውቀው የቦሌ በሻሌ (ውሃ ታንከር)፣ አያት አምስት 40/60 እና እዚያው አካባቢ ያለው ነባር የ20/80 የጋራ መኖሪያ መንደሮች የስምሪት ውስንነት እንዳለባቸው ካስተዋልኩባቸው አካባቢዎች መካከል ተጠቃሾች ናቸው። አካባቢው መነሻ ትራንስፖርት ባለመመደቡ ነዋሪዎች ለስራም ሆነ ለተለያዩ ጉዳዮች ከቤታቸው ሲወጡ ረጅም ሰዓት ቆመው ትራንስፖርት ለመጠበቅ ይገደዳሉ፤ ሲገኝም ግፊያውና መጉላላቱ ቀላል አይደለም።

የአካባቢው ነዋሪዎች "ከቦሌ በሻሌ (ውሃ ታንከር) እና ከአያት አምስት 40/60 የሚነሱ የከተማ አውቶብሶች ባለመኖራቸው ከአራብሳ ሞልተው የሚመጡትን እንጠቀማለን፤ ከመሃል ከተማ ወደ እነዚህ አካባቢዎች በሚደረግ የመልስ ጉዞም እንግልቱ አይቀርም፤ ምክንያቱም ከመገናኛም ሆነ ከአያት ለቦሌ በሻሌ ሳይት ተብሎ የተመደበ ትራንስፖርት ባለመኖሩ በአራብሳ ታሪፍ በመክፈል ለተጨማሪ ወጪና መጉላላት እንዳረጋለን" የሚል ቅሬታ ያቀርባሉ፡፡

ይህን ችግር ለሚመለከታቸው አካላት ለማሳወቅ የሞከሩ ነዋሪዎች ቢኖሩም አመርቂ ምላሽ አላገኙም። እኔም እንደታዘብኩት የአዲስ አበባ ከተማ የአውቶቡስ አገልግሎት ድርጅት አውቶብሶችም ሆኑ ሌሎች የትራንስፖርት አማራጮች በተለይም ሃይገር፣ ቅጥቅጥ ባሶችና ታክሲዎች በአካባቢው መነሻ ፌርማታ ስለሌላቸው ነዋሪዎች በእጅጉ መቸገራቸውን ነው፡፡

ከነዋሪው ብዛት ጋር የተናበበ የትራንስፖርት ስምሪት ሊኖር ግድ ይለዋል ብዬ አምናለሁ፡፡ እንደኔ እምነት ነዋሪዎች በመንግስት ተቋማትም ሆነ በግል ሰርተው ለመቀየር፣ የዕለት ጉርስ ለማግኘት፣ ተማሪዎችም ተምረው ወደ ቤታቸው ለመመለስ ትራንስፖርት አንዱና ዋነኛው ነው፡፡ በቂና ተመጣጣኝ የትራንስፖርት አቅርቦት ከሌለ ደግሞ የዘወትር የስራ መሥናክሉ አይቀርም፡፡ የሚመለከተው አካል ጉዳዩን በአንክሮ አጢኖት ተገቢውን ምላሽ ቢሰጥ እላለሁ፡፡

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ እየተዘጋጀች

ዘወትር ቅዳሜ ወደ አንባቢያን
የምትደርሰው ይህች ጋዜጣ

ግንቦት 1985 ዓ.ም
ተመሰረተች

**አድራሻ**
አምስት ኪሎ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት
በሚገኘው ማህበረ ቅዱሳን ህንፃ ጎን
ስልክ ቁጥር 0111-574923
ፖ.ሣ.ቁ 27080 code 1000
ፋክስ - 559368
addislisan1985@gmail.com

**የገበያ አገልግሎት እና የማስታወቂያ ዝግጅት ዳይሬክቶሬት**
ስልክ 0111 - 112218

**አታሚ**
ሜልባ ፕሪንቲንግ ፐብሊሺንግ ኤንድ ፓኬጂንግ ሼር ካምፓኒ

**ግራፊክስ ዲዛይን**
ዳንኤል ተስፋይ

**ሌይአውትና ዲዛይን**
ፍልሰታ አየለ
መና ዮሐንስ

**የእርምት ባለሙያ**
ቸርነት ዋለልኝ
ገነት መላኩ

**የዕለቱ አዘጋጆች**
ለይላ መሀመድ
አብርሃም ገብሬ
ፋንታነሽ ተፈራ
ሽዋርካብሽ ቦጋለ
ይግለጡ ዓዴ
ሄለን ጥላሁን

**ዋና አዘጋጅ**
ተካልኝ አማረ
Tekalignteke123@gmail.com
አድራሻ ለሚ ኩራ ክ/ከተማ
ወረዳ 3 የቤት ቁጥር B91/17

**ም/ዋና አዘጋጅ**
ሰውነት ኃ/ጊዮርጊስ
መለስ ተሰጋ

**ከፍተኛ አርታኢያን**
ደረጀ ታደሰ
ጊዜው አማረ
ስንታየሁ ምትኩ
ሳህሉ ብርሃኑ

ዜና ትንታኔ

# በአንድ ... ከገጽ 1 የዞረ

ያሉ ልማቶች በተለይም ቀንና ሌሊት የሚሰሩ ፕሮጀክቶችና በተለያዩ አጋጣሚዎች የሚሰጡ ስልጠናዎች ስራን ሳይንቅ እንዲሰራ ብርታት እንደሆኑት አጫውቶናል። እሱም ሆነ ጓደኞቹ ቀንና ሌሊት በሺፍት እየሰሩ የተሻለ ገቢና የስራ ልምድ እያገኙ መሆናቸውን በመጠቆም "መስራት መሰልጠን ነውና ወጣቶች የስራ ባህላቸውን አሻሽለን እራሳችንን ብቻ ሳይሆን ሀገራችንን ከፍ እናድርግ" ሲል መልዕክቱን አስተላልፏል፡፡

በአንድ ጀንበር የስራ ዕድል ፈጠራ መርሃ ግብር፣ እንደከተማ እየተከናወነ ስላለው የስራ ዕድል ፈጠራ እና ተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ ከአዲስ ልሳን ጋዜጣ ጋር ቆይታ ያደረጉት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የስራ እና ክህሎት ቢሮ የስራ ስምሪት አገልግሎት ዳይሬክተር አቶ ሰበሃዲን ሱልጣን እንደገለፁት፣ ከዚህ በፊት እንደከተማ በስራ ዕድል ፈጠራ ላይ ትልቅ ችግር ሆነው ከሚጠቀሱ ነገሮች መካከል ደካማ የስራ ባህል ዋናው ማነቆ ነው፡፡

ወጣቱ ስራ ይፈልጋል፤ ይህንንም ተከትሎ በስራ ፈላጊ መዝገብ ላይ ስሙን ያሰፍራል፡፡ ይሁን እንጂ ስራው ሲቀርብለት ጠዋት ወጥቶ ሲሰራ ውሎ ማታ መግባትን አይፈልግም፡፡ ከባባድ ተግባራት ላይ ሳይሆን በቀላሉ ጥቂት ገንዘብ ማገኛ መንገድ ላይ መሰማራትን ይፈልግ እንደነበር አውስተዋል፡፡

አሁን ግን ይላሉ አቶ ሰበሃዲን፤ በከተማዋ በተሰሩና እየተሰሩ ባሉ ፕሮጀክቶች እየተለመደ የመጣው የቀንና የሌሊት ስራ (7/24) ትልቅ ተሞክሮ ሆኖናል፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ በመንግስት ደረጃ የተሰሩና እየተሰሩ ያሉ ትልልቅ ፕሮጀክቶች ቀንና ሌሊት በሦስት ሺፍት የሚሰሩ በመሆናቸው በርካታ የስራ ዕድል መፍጠር ችለዋል፡፡ ለአብነትም በሦስት ሺፍት ሦስት የተለያየ ሰው በአንድ ፕሮጀክት ላይ የሚሰማራበት እድል መፈጠሩን ጠቅሰዋል፡፡

በመሆኑም ይህ አይነት አሰራር በአንድም በሌላም መንገድ በርካታ የስራ ዕድል እንዲፈጠር እና ስራን ሳይንቁ ቀንም ሌሊትም መስራት እንደሚቻል ማስተማሪያ መሆን በመቻሉ የብዙዎችን አስተሳሰብ እየለወጡ ነው ብለዋል። በተለይም "ለካ በማታም መስራት ይቻላል?" የሚለው አስተሳሰብ በወጣቶች የስራ ባህልና በከተማዋ ሁለንተናዊ ዕድገት ላይ ብዙ ለውጥ እያመጣ ነው ብለዋል አቶ ሰበሃዲን፡፡

አሁን ላይ ወጣቶችን ስለ ስራ እና ተያያዥ ጉዳዮች ለማስተማር ንድፈ ሀሳብ ላይ ብቻ የተመሰረተ ስልጠና ከመስጠት ወጥቶ 7/24 መስራት የሚችሉ ወጣቶችን በተሞክሮነት ማቅረብ ተጀምሯል፡፡ ለዚህ ደግሞ በመዲናዋ እየተገነቡ ያሉ የኮሪደር ልማቶችና መሰል ፕሮጀክቶች ያላቸው ድርሻ ከፍ ያለ ስለመሆኑም ነግረውናል፡፡

ከዝግጅት ክፍላችን ጋር ቆይታ ያደረጉት በጎንደር ዩኒቨርሲቲ የኢኮኖሚክስ ትምህርት ክፍል ተባባሪ ፕሮፌሰር ይንገስ አለሙ (ዶ/ር) እንደሚሉት፣ በአዲስ አበባ ከተማ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየተከናወኑ ያሉ ልማቶች የከተማዋን ውበትና ዘመናዊነት ከፍ ከማድረጋቸው ባሻገር በትውልዱ ዘንድ አዲስ የስራ ባህልን እያስተዋወቁ መሆናቸውን ተከትሎ በርግጥም ከተማዋ በአዲስ የስራ ባህል የተሻለ ለውጥ እያመጣች እና ለበርካቶችም የስራ ዕድል እየፈጠረች መሆኗን የሚያሳይና በኢኮኖሚው ዘርፍም ትልቅ እምርታ የሚያመጣ ነው፡፡

በአንድ ጀንበር የስራ ዕድል ለመፍጠር የተጀመረው ጥረትም ያሉንን ፀጋዎች በሚገባ መለየትና መጠቀም ከቻልን ለበርካቶች የስራ ዕድል መፍጠር እንደምንችል የሚያመላክትና ተጨባጭ ኢኮኖሚያዊ ለውጥ የሚያመጣ ነው፡፡ ወጣቱ የስራ ዕድል አገኘ ማለት ኑሮውን ከማሻሻሉ ባሻገር በምርትና ምርታማነት ላይ ተጨማሪ አቅም ይፈጥራል፡፡

ይህ ደግሞ ከከተማዋ ከፍታ ባሻገር በሀገር ሁለንተናዊ ዕድገት ላይ ጉልህ ዕድገትን የሚያመጣ በመሆኑ ሌሎች ከተሞችም የስራ ድል የመፍጠር አቅማቸውን በሚገባ በመፈተሽ መስራት ከተቻለ የሀገሪቱን ዕድገት የበለጠ ማፋጠን እንደሚቻልም ጠቁመዋል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የስራ እና ክህሎት ቢሮ የስራ ስምሪት አገልግሎት ዳይሬክተር አቶ ሰበሃዲን ሱልጣን እንደገለፁት ቢሮው በበጀት ዓመቱ ለ350 ሺህ ዜጎች የስራ ድል ለመፍጠር አቅዶ እየሰራ ነው፡፡ ባለፉት አራት ወራት ብቻ ለ137 ሺህ 111 ዜጎች ስራ ዕድል መፍጠር ተችሏል፡፡

ይሁን እንጂ አሁን በተያዘው ሁኔታ የዜጎችን ጥያቄ ምላሽ እየሰጡ ከመሄድ ጋር በተያያዘ ትንሽ ውስንነት ያለበት በመሆኑ ተቋሙ ልዩ ዕቅድ በማቀድ ከጥቅምት እስከ ህዳር 30 ቀን 2018 ዓ.ም ባሉት ጊዜያት ውስጥ ለ20 ሺህ 900 ዜጎች የስራ ዕድል ለመፍጠር ልዩ ዕቅድ አውጥቶ እየሰራ ነው፡፡

"በአንድ ጀንበር የስራ ዕድል መፍጠር" የተሰኘው ልዩ ዕቅድ ስኬታማነትም ቀደም ብሎ ምዝገባ የማካሄድ፣ ፀጋዎችን የመለየት እና እነዚህስ ጸጋዎች በትክክል ለዜጎች ዳቦ የሚያበሉ ናቸው ወይ? የሚለውን ነገር የመፈተሽ ስራዎች እየተከናወኑ እንደሆነም ጠቁመዋል፡፡

አቶ ሰብሃዲን አክለውም፣ እንደ ከተማ ባለፉት አራት ወራት 222 ሺህ ዜጎች "የስራ ዕድል ይፈጠርልኝ" በሚል ተመዝግበዋል፡፡ ከዚህ ውስጥ ወደስራ የገቡት 137 ሺህ 111 ናቸው፡፡ በመሆኑም በዚህ መሃል ስራ ያልተፈጠረለት ዜጋ አለ።

ስለሆነም ያደራጀናቸውና ተደራጅተውም የተቀመጡ ዜጎች በመኖራቸው አሁንም የስራ ዕድል ይፈልጋሉ፡፡ ስለዚህ እንደ ከተማ የስራ ዕድል ሊፈጥሩ የሚችሉ በሚል የተለዩ 18 ስራ ፈጣሪዎች እና 5 አመቻቾች ተቋማት በድምሩ 23 ባለድርሻ አካላት አሉ፡፡

በመሆኑም ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን የተለያዩ ስራዎች መሰራታቸውን የጠቀሱት አቶ ሰብሃዲን ለአብነትም በኮንስትራክሽን፣ በማኑፋክቸሪንግ፣ በከተማ ግብርና፣ በአገልግሎት እና በንግድ ዘርፎች ያሉ የስራ ዕድል ጸጋዎች ተለይተዋል፡፡ ስራ ፈላጊዎችም ተደራጅተው ወደ እነዚህ ዘርፎች እንዲገቡ እየተሰራ ነው ብለዋል፡፡

ህዳር 30 ቀን 2018 ዓ.ም በአንድ ጀምበር በአዲስ አበባ ስቴዲዮም ከፍተኛ የከተማዋ የስራ ኃላፊዎች በሚገኙበት በሚደረግ ዝግጅት ለዜጎቹ ስራዎቹ በይፋ ይሰጣሉ፡፡ ወደ ስራም ይገባሉ። ይህም ዕቅዳችንን የምናሳካበት አንዱ መንገድ ነው ያሉት አቶ ሰበሃዲን፣ ይህ የአንድ ጀንበር የስራ ዕድል ፈጠራ ልዩ ዕቅድ ትኩረቱ ከቅጥር ባለፈ መደራጀትን መሰረት ያደረገ እንደሆነም ተናግረዋል፡፡

ክፍለ ከተሞችም ቀደም ብለው ስራ ፈላጊውን እና ቀጣሪውን የሚያገናኝ አውደ ርዕይ በማዘጋጀት በቀን 1 ሺህ እና ከዚያ በላይ የስራ ዕድል እየፈጠሩ ነው። በማዕከል ደረጃም ህዳር 30 ቀን 2018 ዓ.ም ይፋ በሚደረገው መርሃ ግብር ለ20 ሺህ 900 ዜጎች ስራ ዕድል ይፈጠራል ብለዋል፡፡

የአንድ ጀንበር ስራ ዕድል ፈጠራ ትልቁ ዓላማው በበጀት ዓመቱ የተያዘውን ዕቅድ ማሳካት ሲሆን፣ ይህም ለበርካታ ዜጎች የስራ ዕድል እየፈጠሩ በ6 ወር ውስጥም ከተያዘው ዕቅድ በላይ በማሳካት ተደራጅተው ወደስራ ያልገቡ ወጣቶችን ፍላጎት ማሟላት የሚያስችል ነው፡፡

እንደ ቢሮው መረጃ፣ በ5 ዓመቱ ስትራቴጂክ እቅድ ክንውን መሰረት በ2013 ዓ.ም ለ345 ሺህ 62፣ በ2014 ዓ.ም ለ421 ሺህ 850፣ በ2015 ዓ.ም ለ416 ሺህ 999፣ በ2016 ዓ.ም ለ291 ሺህ 577 እንዲሁም በ2017 ዓ.ም ለ366 ሺህ 44 ዜጎች የስራ እድል ተፈጥሯል፡፡ ከዚህ ውስጥ እስከ 2015 ዓ.ም ያለው ቋሚ እና ጊዜያዊ የስራ ዕድል ሲሆን፤ የቀሩት ሁለት ዓመታት ደግሞ ቋሚ የስራ ዕድሎች ናቸው፡፡ በእነዚህ አምስት ዓመታትም በጥቅሉ 1 ሚሊዮን 841 ሺህ 532 የስራ ዕድሎች ተፈጥረዋል፡፡

መርሃ ግብሩ ስራና ሰራተኛን የምናገናኝበት አንዱ መሳሪያችን ነው። እያንዳንዱ ተግባርም በየሳምንቱና በየአስራ አምስት ቀናቱ እንደ ከተማ በተዋቀሩ የአመራርና ቴክኒካል ቋሚ ኮሚቴዎች እየተገመገመ ሲሆን፣ እስካሁን ባለው ሂደትም ውጤታማ ስራዎች ተከናውነዋል፡፡

የአንድ ጀንበር የስራ ዕድል መርሃ ግብሩ በማዕከል ደረጃ የሚገኙ ስራ እድል የሚፈጥሩ ባለድርሻ ተቋማት የሚፈጠር ነው፡፡ ስራ እድሉም ትኩረት የሚያደርገው ኢንተርፕራይዝ በማደራጀት እንደሆነም አቶ ሰብሃዲን ተናግረዋል፡፡




ፎቶ- ከገፀ ድር

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከ2013 እስከ 2017 ዓ.ም የተፈጠረውን የስራ ዕድል የሚያሳይ ሰንጠረዥ

## ማስታወቂያ

በገነት ብሩ ጥላሁን ስም የተመዘገበ በካርታ ቁጥር የካ/6203/12 የሴሪ ቁጥር 1500289 የተሰጠበት ቀን 20/11/12 ዓ.ም የቤቱ ስፋት በሰነድ 86.04 ሜ.ካ የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ በእኛ ተቋም የተሰጠ መሆኑ ይታወቃል፡፡

ይሁንና በገነት ብሩ ጥላሁን ስም የተመዘገበ በካርታ ቁጥር የካ/6203/12 የሴሪ ቁጥር 1500289 የተሰጠበት ቀን 20/11/12 ዓ.ም የቤቱ ስፋት በሰነድ 86.04 ሜ.ካ የሆነው ቤት ማረጋገጫ ካርታ ከእጃቸው የጠፋ ስለሆነ ቤቱን በዕዳ ይዤዋለሁ፤ አስይዤዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለተቋሙ እንዲያሳውቁን እያልን በዚህ ምክንያት ለ30 ቀናት የሚቆይ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ እየጠየቅን ይህ ጋዜጣ ጥሪ ከተደረገ በኋላ ካርታ የምናደራጅ እና ኃላፊነት የማንወስድ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

# ከህብር የተገኘ በረከት

## “አዲስ አበባ የብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች መናኸሪያ መሆኗ ለጋራ መግባባት እንደ ትምህርት ቤት ያገለግላል”

**በሐሮማያ ዩኒቨርሲቲ የማህበራዊ ሳይንስ ትምህርት ክፍል መምህሩ ጉተማ ኢማና**

**በሳህሉ ብርሃኑ**


ፎቶ- ከገፀ ድር
አዲስ አበባ የሁሉም ኢትዮጵያዊ የጋራ መኖሪያ ቤት መሆኗ ዘርፈ ብዙ ትሩፋቶችን አጎናጽፏታል

የቻይና ዋና ከተማ የሆነችው ቤጂንግ በዋነኝነት የሃን ብሔር የሚኖርባት ብትሆንም ልክ እንደ ቻይና ሁሉ የተለያዩ ብሔረሰቦችን የያዘች ህብረ ብሔራዊት ከተማ ናት። የተለያዩ ሀገራት ዜጎችን ጨምሮ እንደ ሁይ፣ ማንቹ፣ ሞንጎል ያሉ ብሔሮችን በውስጧ የያዘችው ቤጂንግ እያንዳንዱ ብሔረሰብ የራሱን ባህል፣ ወግ፣ ምግብ፣ ቋንቋ እና የአለባበስ ዘይቤ ወደ ከተማዋ ያመጣል። ይህ ደግሞ ቤጂንግን የበለፀገች እና ዓለም አቀፋዊ ከተማ እንድትሆን አድርጓታል።

ከኢኮኖሚ አስተዋጽኦ አንጻር ከተመለከትነው የቤጂንግ ብሔረሰቦች በተለያዩ ዘርፎች ማለትም በንግድ፣ በትምህርት፣ በሳይንስና ቴክኖሎጂ፣ በቱሪዝም ኢንዱስትሪ ውስጥ በመስራት ለከተማዋ የኢኮኖሚ ዕድገት አስተዋፅኦ ያደርጋሉ። በሌላም በኩል ቤጂንግ የቻይና ፖለቲካዊ ማዕከል እንደመሆኗ መጠን፣ የሁሉም ብሔረሰቦች ተወካዮች እና ምሁራን መኖራቸው የብሔራዊ አንድነት ስሜት እንዲጎለብት ያደርጋል። የቤጂንግ ብሔረሰቦች ብዝሃነት የከተማዋን ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ መሠረት በማጠናከር ዓለም አቀፋዊ ከተማ እንድትሆን ትልቅ ሚና ይጫወታሉ፡፡

ይህ የቤጂንግ ተሞክሮ ታዲያ በሪቻርድ ፍሎሪዳ ወደተፃፈው “ዘ ራይዝ ኦፍ ዘ ክሬኤቲቭ ክላስ” (The Rise of the Creative Class) መጽሐፍ ወደያዘው ጽንሰ ሀሳብ ያመራናል፡፡ ይህ መጽሐፍ እ.ኤ.አ በ2002 ለህትመት ሲበቃ ይዞት የመጣው ሀሳብ በተለይ በከተማ ልማት ዘርፍ አዲስ የአስተሳሰብ አዝማሚያ የፈጠረ ነበር። መጽሐፉ የዘመናዊ ከተሞችን ኢኮኖሚያዊ ዕድገት እና ስኬት የሚወስነው የፋብሪካዎች ወይም የባንኮች መኖር ሳይሆን፣ ከተሞች ፈጠራ ያላቸውን ሰዎች ለመሳብና ለማስቀረት ባላቸው አቅም ላይ መሆኑን ይሞግታል።

ደራሲው ሪቻርድ ፍሎሪዳ እንደሚሉት አንድ ከተማ የፈጠራ ሰዎችን መሳብና ማቆየት የምትችለው ደግሞ ሦስት ዋና ዋና ነገሮች ሲሟሉ ብቻ ነው። እነዚህም የቴክኖሎጂ አቅርቦትና መሠረተ ልማት፣ ከፍተኛ የሰለጠነና የተማረ የሰው ኃይል ብዛት እና የከተማዋ ክፍትነትና የብዝሃነት ተቀባይነት ሊኖራቸው እንደሚገባ ደራሲው ሪቻርድ ፍሎሪዳ ያብራራሉ፡፡ በተለይም ከተሞች ዘር፣ ኃይማኖት፣ የጾታ ዝንባሌ ወይም የአኗኗር ዘይቤ ሳይለይ ማንኛውንም አይነት ሰው በደስታ የምትቀበል መሆን አለባት ይላሉ ደራሲው።

ከላይ በአስረጅነት ከተጠቀሰችው ቤጂንግ በተጨማሪ እንደ ለንደን፣ ኒው ዮርክ እና ቶሮንቶ ያሉ ከተሞችም ብዝሃነትን በብቃት በመምራት ዓለም አቀፍ የንግድና የፋይናንስ ማዕከል ሆነው መቀጠል ችለዋል። የኢትዮጵያ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ሕይወት ማዕከል

**የተለያየ አስተሳሰብና ባህል ያላቸው ሰዎች በአንድ ቦታ ሲሰባሰቡ፣ የፈጠራ እና አዲስ ሥራ የመጀመር አቅም ይጨምራል። ከተለያየ ብሔር የመጡ ግለሰቦች የራሳቸውን የንግድ ልምድና ፍላጎት ይዘው ሲመጡ፣ የተለያዩ የንግድ ዓይነቶችና አገልግሎቶች እንዲፈጠሩ ያደርጋል**

የሆነችው አዲስ አበባ ከዚህ አንጻር ስትመዘን የዘር፣ የኃይማኖት፣ የጾታ ዝንባሌ ወይም የአኗኗር ዘይቤ ሳይለይ ማንኛውንም አይነት ሰው ከሚኖርባቸው ከተሞች መካከል ሆና እናገኛታለን፡፡

መዲናዋ የሁሉም ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች መኖሪያ መሆኗ ለከተማዋ እድገት ትልቅ ሀብት እንደሆነ ምሁራን ይስማማሉ። የባህል ብዝሃነት ደግሞ የከተሞችን ምርታማነት፣ የፈጠራ አቅም እና ማህበራዊ ጥንካሬ በከፍተኛ ደረጃ ያሳድጋል ይላሉ።

አዲስ አበባ የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ (Economic Powerhouse) ስትሆን፣ ከሀገር የከተማ ጠቅላላ ምርት (Urban GDP) ከፍተኛውን ድርሻ ትይዛለች። ይህ ስኬት ከከተማዋ የብዝሃነት ባህሪ ጋር በቅርብ የተሳሰረ ነው ተብሎ ይታሰባል። ለመሆኑ የሁሉም ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች መኖሪያ የሆነችው አዲስ አበባ የሁሉም ቤት መሆኗ ምን አስገኝቶላታል? እንደ አዲስ አበባ አይነት አወቃቀር ያላቸው ከተሞችስ ከዚህ አንጻር እንዴት ይታያሉ? የሚሉ ጉዳዮችን መዳሰስ ተገቢነት ይኖረዋል፡፡

የስነ ልቦና ምሁራን እንደሚጠቁሙት፣ የተለያየ አስተሳሰብና ባህል ያላቸው ሰዎች በአንድ ቦታ ሲሰባሰቡ፣ የፈጠራ እና አዲስ ሥራ የመጀመር አቅም ይጨምራል። ከተለያየ ብሔር የመጡ ግለሰቦች የራሳቸውን የንግድ ልምድና ፍላጎት ይዘው ሲመጡ፣ የተለያዩ የንግድ ዓይነቶችና አገልግሎቶች እንዲፈጠሩ ያደርጋል። ለምሳሌ የባህል ምግብ ቤቶች፣ የቱሪዝም ኢንዱስትሪውና የንግድ አቅርቦት ሰንሰለቶች ከብዝሃነት ከፍተኛ ጥቅም እንደሚያገኙም “ዘ ራይዝ ኦፍ ዘ ክሬኤቲቭ ክላስ” (The Rise of the Creative Class) መጽሐፍ ደራሲው ሪቻርድ ፍሎሪዳ ይገልጻሉ።

ከተለያየ ባህልና አስተዳደግ የመጡ ሰዎች አብረው ሲሰሩ፣ ለተለያዩ ችግሮች መፍትሔ ለመስጠት አዳዲስና ፈጠራ የሞሉባቸው ሀሳቦችን ለመፍጠር ያግዛል የሚሉት ደግሞ በሐሮማያ ዩኒቨርሲቲ የማህበራዊ ሳይንስ ትምህርት ክፍል መምህሩ ጉተማ ኢማና ናቸው። በአዲስ አበባ ያለው እውነታም እንደሚያሳየው የተለያዩ የንግድ ዓይነቶች፣ ሬስቶራንቶች እና አገልግሎቶች (ለምሳሌ፡- የየብሔሩ ባህላዊ ምግቦች) መኖራቸው የፈጠራ ውጤት እና የገበያ ተፈላጊነት ማሳያ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል።

ከተለያዩ ክልሎች የመጡ ሰዎች ልዩ ልዩ ክህሎቶችን፣ የንግድ ልምዶችን እና የፈጠራ ሀሳቦችን ይዘው ይመጣሉ። ይህ የሰው ኃይል ብዝሃነት የሥራ ፈጠራን ያበረታታል፤ የገበያ ተወዳዳሪነትን ይጨምራል፤ ከተማዋን ለተለያዩ ኢንዱስትሪዎች ማዕከል እንድትሆን ያደርጋታል ይላሉ። እንደዚሁም የብዝሃነት ባህሪው የተለያዩ ምርቶች እና አገልግሎቶች እንዲፈጠሩ ያደርጋል። የብሔረሰብ ምግቦች፣ የባህል አልባሳት፣ እደ-ጥበብ እና የቋንቋ አገልግሎቶች በስፋት ይገኛሉ። ይህ የገበያ ብዝሃነት የከተማዋን የንግድ እንቅስቃሴ ያሳድገዋል።

በሌላም በኩል መዲናዋ የኢትዮጵያ ማዕከል ከመሆኗም ባሻገር የአፍሪካ ህብረት እና የተለያዩ ዓለም አቀፍ ተቋማት መቀመጫ በመሆኗ ዓለም አቀፍ ትኩረት አላት። የብሔረሰቦች ባህላዊ ልዩነትና ብዝሃነት ይህን ዓለም አቀፋዊ ገፅታ ያጠናክረዋል፤ ቱሪስቶችና የውጭ ባለሀብቶችን የመሳብ አቅሟን ከፍ ያደርጋል። ከተማዋ ከተለያዩ ክልሎች የመጡ ሠራተኞችንና ባለሙያዎችን ስለሚስብ፣ የንግድ ድርጅቶች ሰፊ የክህሎት ምርጫ ያገኛሉ። ይህም የሥራ ገበያውን የበለጠ ተለዋዋጭ እና ጠንካራ ያደርገዋል። የተለያዩ የምግብ አይነቶች፣ ጥበቦች እና የአኗኗር ዘይቤዎች ለቱሪስቶች ልምድ የሚያበለፅጉ ሲሆን ለከተማዋ የኢኮኖሚ ዕድገት የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ያደርጋሉ።

አዲስ አበባ የየብሔረሰቡን ሙዚቃ፣ የጥበብ ስራዎች፣ ክብረ በዓላትና የአለባበስ ዘይቤ በአንድነት የምታስተናግድ ማዕከል ነች። ይህ የባህል ብልፅግና የከተማዋን ነዋሪዎች የሕይወት ጥራት ያሳድጋል፤ እንዲሁም ለቱሪዝም ኢንዱስትሪው ትልቅ መደላድል ይፈጥራል። የማህበራዊ ሳይንስ ተመራማሪዎች እንደሚሉት አዲስ አበባ የብሔረሰቦች መናኸሪያ መሆኗ ለማህበራዊ መሳሳብ እና ለጋራ መግባባት እንደ ትምህርት ቤት ያገለግላል። ከተለያዩ ብሔሮች የተዋቀረ ማህበረሰብ ውስጥ ግለሰቦች የሌላውን ባህል፣ ቋንቋ እና ልማድ በየዕለቱ በመስተጋብር ይማራሉ።

በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ሀቢታት (UN-Habitat) በተዘጋጀው “State of Addis Ababa 2017 Report” ላይ እንደተገለጸው፣ የከተማዋ ነዋሪዎች የማህበራዊ መረቦችን ሳያጡ በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ ያላቸው ተሳትፎ እያደገ መጥቷል። የተለያዩ ብሔረሰቦች ጎን ለጎን ሲኖሩ፣ የግድ የባህል ልውውጥ ይፈጠራል። ይህ መቻቻልን፣ መግባባትን እና ብሔራዊ አንድነትን በማጠናከር ለከተማዋ ማህበራዊ መረጋጋት እና ሰላማዊ ዕድገት አስተዋጽኦ እንዳለውም ሪፖርቱ ያትታል።

በቻርለስ ላንድሪ እና ፊል ውድ የተጻፈው ‘The Intercultural City:- Planning for Diversity Advantage’ የተሰኘውን መጽሐፍ ጠቅሰን ጉዳያችንን እንቋጭ፡፡ ከተሞች ብዝሃነትን እንደ ችግር ሳይሆን እንደ ስልታዊ ጠቀሜታ (Strategic Advantage) መውሰድ እንዳለባቸው የሚመክረው መጽሐፉ የባህል እና የብሔረሰቦችን ልዩነት እንደ ችግር ወይም እንደ ግዴታ ከማየት ይልቅ እንደ ዋና የኢኮኖሚና ማህበራዊ ሀብት በመጠቀም ለከተማዋ ጥቅም ማዋል እንደሚቻል ያብራራል፡፡ ይህን የተረዳችው የአፍሪካ ህብረት መቀመጫ የሆነችው አዲስ አበባም የሁሉም አቃፊ ቤት መሆኗ ከተማዋን የበለጠ ዓለም አቀፋዊ ገፅታ እንድትይዝ አስችሏታል።

ኢኮኖሚ

# ኢትዮጵያ በአየር ንብረት ለውጥ

## “ኮፕ 32ን ያካተተ ጠንካራ እና ትርጉም ያለው ውጤት ለማምጣት ቁርጠኛ ነች”

**ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)**

**በጊዜው አማረ**

ኮፕ (Conference of the parties- COP) በየዓመቱ የሚካሄድ እና የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም የሚደረግ ትልቅ ዓለም አቀፍ ስብሰባ ነው። ይህ ጉባኤ የሚካሄደው በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የአየር ንብረት ለውጥ ስምምነት (United Nations Framework Convention on Climate Change- UNFCCC) ስር ነው። ሀገራችን ኢትዮጵያም ከሁለት ዓመት በኋላ ይህን ጉባኤ ለማካሄድ የተመረጠችው ከሰሞኑ ብራዚል ውስጥ በተካሄደው የዘንድሮው ስብሰባ ላይ ነው።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አፍሪካ በብራዚል ቤሌም በተካሄደው የተባበሩት መንግስታት የ2025 የአየር ንብረት ጉባዔ (ኮፕ 30) ላይ በአንድነት ድምጿን አሰምታለች። በዓለም ደረጃም ተደምጣለች ሲሉ ተናግረዋል፡፡




ፎቶ- ከገፀ ድር

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ኢትዮጵያ የኮፕ 32 ጉባኤ አዘጋጅ ሆና በመመረጧ ምስጋና እና መልዕክት አስተላልፈዋል

ኢትዮጵያ እ.ኤ.አ. በ2027 ኮፕ 32ን በአዲስ አበባ ለማስተናገድ ያቀረበችውን ጥያቄ የአፍሪካ ቡድን ተደራዳሪዎች በሙሉ ድምፅ በማፅደቃቸው ልባዊ ምስጋናዋን ታቀርባለች ሲሉም ገልጸዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው ባስተላለፉት መልዕክት በሰው ልጅ ላይ ከሚጋረጡ ፈተናዎች አንዱ የሆነውን የአየር ንብረት ለውጥ ለመቅረፍ የጋራ ጥረት የሚጠይቀውን ጉባኤ እንድንመራ ለተሰጠን እድል እናመሰግናለን ብለዋል።

ይህ ዕውቅና ዓለም በኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥ ርምጃ መሪነት እና ዋና ዋና ዓለም አቀፍ ዝግጅቶችን የማስተናገድ አቅም ላይ እምነት እንዳለው ያሳያል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ “ኢትዮጵያ በአየር ንብረት ለውጥ ላይ የጋራ ዕርምጃዎችን የሚያራምደውን ኮፕ 32ን ያካተተ ጠንካራ እና ትርጉም ያለው ውጤት ለማምጣት ቁርጠኛ ነች” ሲሉ አስታውቀዋል።

እ.ኤ.አ. በ2027 የሚደረገውን ኮፕ 32 ኢትዮጵያ እንድታስተናግድ የተመረጠችው ናይጄሪያን በመብለጥ ነው። በጉባኤው የዓለም አገራት እና ሌሎችም በሺዎች የሚቆጠሩ ተሳታፊዎች የሚካፈሉ ሲሆን፣ ወሳኝ ድርድሮች እና ስምምነቶችም ይደረጉበታል። ለመሆኑ ኢትዮጵያ ለዚህ ጉባኤ የተመረጠችበት ምክንያት ምንድን ነው? ጉባኤው በአዲስ አበባ መካሄዱ ምን እንደምታ እና ጥቅም ይኖረዋል?

ረዳት ፕሮፌሰር ደረጀ በቀለ በጅማ ዩኒቨርሲቲ የተፈጥሮ ሀብት አስተዳደር ትምህርት ክፍል መምህር ናቸው፡፡ እርሳቸው እንደሚሉት፣ ኢትዮጵያ ሰፊ የተፈጥሮ ጥበቃ ስራዎችን የምታከናውን ሀገር ናት፡፡ በአረንጓዴ አሻራና በደን ልማት ለብዙ ሀገራት ምሳሌ መሆንም ችላለች፡፡

ስለዚህ ኮፕ 32 አዘጋጅ ሆና እንድትመረጥ በማድረጉ ረገድ ባለፉት አመታት የተከናወኑ የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብሮች ከፍተኛ አስተዋጽ አላቸው፡፡ ምክንያቱም አንድ ሀገር የኮፕን ጉባኤ ለማስተናገድ ከመመረጡ በፊት በሀገርና አህጉር ደረጃ ያለው ሚናና የሰራው ስራ ከግምት ይገባል፡፡ ስለዚህ ኢትዮጵያ በተፈጥሮ ጥበቃ የምትታወቅና በካይ ጋዝ እንዲቀንስ በአለም የአፍሪካን ድምጽ የምታሰማ ሀገር መሆኗ ከሁለት አመት በኋላ የሚካሄደውን ትልቅ ጉባኤ እንድታስተናገድ ለመመረጥ ረድቷታል ይላሉ፡፡

ኢትዮጵያ እንደ የአረንጓዴ አሻራ (Green Legacy Initiative) ያለ ትልቅ እና ስኬታማ የአካባቢ ጥበቃ ስራን በማካሄድ የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም ያላትን ቁርጠኝነት አሳይታለች። እንደ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ያሉ የሃይል ማመንጫ ፕሮጀክቶች ላይ ያላት ንፁህ የኃይል ፍላጎትን የሚያሳዩ ፕሮጀክቶች ለጉባኤው አዘጋጅነት በሙሉ ስምምነት እንድትመረጥ አወንታዊ ተፅዕኖ አሳድረዋል ማለት ይቻላል።

በግብርና ሚኒስቴር የተፈጥሮ ሃብት ጥበቃና አጠቃቀም መሪ ስራ አስፈጻሚና በአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር የቴክኒክ ኮሚቴ ጸሃፊ አቶ ፋኖሴ መኮንንም በረዳት ፕሮፌሰር ደረጀ ሃሳብ ይስማማሉ፡፡

አቶ ፋኖሴ ኢትዮጵያ ሰፊ የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብርና የተፈጥሮ ጥበቃ ስራን እያከናወነች ነው፡፡ ይህም ስራን ጨምሮ የኢኮኖሚ እድልን ፈጥሯል፡፡ ትልቅ የዲፕሎማሲ ስኬት አስገኝቷል። ይህ ስራ ኢትዮጵያ ለኮፕ32 ጉባኤ አዘጋጅነት እንድትመረጥ አድርጓል ይላሉ፡፡

ኢትዮጵያ በተለይም የአፍሪካ የአየር ንብረት ጉባኤን (Africa Climate Summit) በማዘጋጀት ያገኘችው ልምድ እና የመዲናዋ የመሰብሰቢያ ቦታዎችና የሆቴል አቅም እያደገ መምጣትም ለጉባኤ አዘጋጅነት እንድትመረጥ የረዳት ሌላኛው ጉዳይ ነው፡፡

አዲስ አበባ የአፍሪካ ኅብረት (AU) እና የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት (UN) የአፍሪካ ኢኮኖሚ ኮሚሽን (UNECA) መቀመጫ በመሆኗ ምክንያት፣ ዓለም አቀፍ ኮንፈረንሶችን እና ከፍተኛ የዲፕሎማሲ ስብሰባዎችን የማስተናገድ ረጅም እና የተረጋገጠ ልምድ አላት። ይህም ለኮፕ32 (የተባበሩት መንግሥታት የአየር ንብረት ለውጥ ኮንፈረንስ) አስተናጋጅነት እንድትመረጥ ትልቅ አበርክቶ አለው፡፡

የአዲስ አበባ ከፍተኛ የዲፕሎማሲ ማዕከልነት፣ ዓለም አቀፍ ተሳታፊዎችን በብቃት የማስተናገድ፣ የሎጂስቲክስና የፀጥታ አቅምዋን ያሳያል። በቅርቡ በሀገራችን በስኬት የተካሄደው የአፍሪካ የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤን ለዚህ እንደ ማስረጃ መጥቀስ ይቻላል፡፡

ጉባኤው በአዲስ አበባ መዘጋጀቱ አንድምታውና ጠቀሜታ እጅግ በርካታ ነው፡፡ የኮፕ ጉባኤ አስተናጋጅ ሀገር በስብሰባው የፕሬዝዳንትነት ሚና አለው። የጉባኤውን ግቦች መቅረጽ ይችላል፡፡ የራሱን የአየር ንብረት ለውጥን የተመለከቱ ስራዎችን የማስተዋወቅ እድልና መብትም አላቸው፡፡ ስለዚህ ኢትዮጵያ በጉባኤው ወቅት የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብርን ጨምሮ ለሌሎች የተፈጥሮ ጥበቃ ስራዎችንና አየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል እየሰራች ያለውን ስራ ለዓለም ማስተዋወቅ ትችላለች። በጉባኤው በርካታ የሀገራት መሪዎች፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት እንዲሁም የመገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎች የሚገኙ በመሆኑ ለኢትዮጵያ መልካም አጋጣሚን ይፈጥራል፡፡

ስለዚህ በርካታ የዓለም መሪዎች፣ ሳይንቲስቶች እና ባለድርሻ አካላት ወደ ሀገሪቱ ሲመጡ፣ ኢትዮጵያ ከሌሎች ሀገራት ልምድ የመቅሰም እና የራሷን የልማት ፕሮጀክቶች (ለምሳሌ አረንጓዴ አሻራ) ስራዎችን የማሳየትና የማስተዋወቅ፣ የቱሪስት መዳረሻዎችን የማስጎብኘት ዕድል ታገኛለች።

ረዳት ፕሮፌሰር ደረጀ ኢትዮጵያ ከዚህ ቀደም ስታራምደው የነበረውን የአየር ንብረት ለውጥ አቋም በጉባኤው ለማንጸባረቅና በእድገት ላይ የሚገኙ ሀገራትን ድምጽ ለማሰማት እድል አላት። ምክንያቱም የአደጉ ሀገሮች በካይ ጋዝን ለመቀነስ የሚስችሉ አማራጮችን ለማድረግ ቃል ቢገቡም ወደ ተግባር ለመለወጥ ግን ቁርጠኝነት ይጎድላቸዋል፡፡

ስለዚህ ኢትዮጵያ እንደ አዘጋጅ ሀገር በጉባኤው ላይ የአየር ንብረት ለውጥን በተመለከተ በሚደረጉ ድርድሮች ወቅት የሚከሰቱ አለመግባባቶችን የመሸምገል እና መፍትሄ የማስቀመጥ ስልጣን ያላት በመሆኑ ጉባኤውን ማስተናገዷ እንድምታውና ጥቅሙ ከፍተኛ ነው፡፡

ኢትዮጵያ ጉባኤውን ማስተናገዷ የአፍሪካን አቋም እና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ጉዳዮች እንድታቀርብ ያስችላል፡፡ በአየር ንብረት ለውጥ ድርድር በግንባር ቀደምትነት እንድትሳተፍ ትልቅ እድል ይሰጣል። የአፍሪካ የአየር ንብረት ለውጥ ስጋት እና ፍትሐዊ የፋይናንስ ድጋፍ ጥያቄዎች ላይ ያላትን ተጽዕኖና የመደራደር አቅም ይጨምራል።

በጅማ ዩኒቨርሲቲ የተፈጥሮ ሀብት አስተዳደር ትምህርት ክፍል ምሁሩ ረዳት ፕሮፌሰር ደረጀ በቀለ ጉባኤው ከሚሰጠው ጥቅም አንዱ ኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥን በተመለከተ እየሰራች ያለችውን ስራ በሚገባ ለማስተዋወቅ እድል የሚፈጥር መሆኑ ነው፡፡ የአየር ንብረት ለውጥን በተመለከተ ከዚህ በፊት የተደረጉ አለም አቀፍ ስምምነቶችና ፖሊሲዎች ወደ ትግበራ እንዲመጡ ግፊት ማሳደር ትችላለች ይላሉ፡፡

በአጠቃላይ ለጉባኤው አዘጋጅነት መመረጥ ለኢትዮጵያ ትልቅ ዲፕሎማሲያዊ ስኬት ነው። በዓለም አቀፍ ደረጃ ያላትን ክብርና የዲፕሎማሲ አቅም ያጠናክራል። እንዲሁም ኢትዮጵያ በአፍሪካ የአየር ንብረት ጉዳዮች ላይ ያላትን መሪነት ያጎላል። በተለይ በቅርቡ በአዲስ አበባ የተካሄደው 2ኛው የአፍሪካ የአየር ንብረት ጉባኤ ባስገኘው ውጤት መሠረት፣ የአፍሪካን የአየር ንብረት ለውጥ መፍትሄዎች ወደ ዓለም አቀፍ መድረክ ለማምጣት ያስችላታል።

በግብርና ሚኒስቴር የተፈጥሮ ሃብት ጥበቃና አጠቃቀም መሪ ስራ አስፈጻሚና በአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር የቴክኒክ ኮሚቴ ጸሃፊ አቶ ፋኖሴ እንደሚሉት፣ አትዮጵያ ለኮፕ32 አዘጋጅነት መመረጧ ትልቅ እድልና ተስፋ ነው፡፡ ይህ ጉባኤ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጥቅሙ ከፍተኛ ነው፡፡ ኢትዮጵያ በአለም መድረክ ያላትን ተሰሚነት ከፍ ያደርጋል፡፡ ለጉባኤው እንግዶች ሲመጡ የህዝብ ለህዝብ ግንኙነቱ ከፍ ይላል። የኢትዮጵያን መልካም ገጽታ ለዓለም ለማሳየት ይረዳል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በቅርቡ በአዲስ አበባ የተካሄደው ሁለተኛው የአፍሪካ የአየር ንብረት ጉባኤ የፈጠረውን መነቃቃት መሰረት በማድረግ አፍሪካ ለአየር ንብረት ለውጥ የመፍትሔ አህጉር ሆና እንድትቀጥል ኢትዮጵያ የመሪነት ሚናዋን አጠናክራ ትቀጥላለች ሲሉ አረጋግጠዋል።

## የኢትዮጵያ ... ከገጽ 1 የዞረ



ፎቶ- ከገፀ ድር
የህግ ባለሙያው አቶ ኪያ ፀጋዬ

ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ከሁለት ዓመት በፊት በይፋ ኢትዮጵያ የባህር በር ማግኘት እንዳለበት ካነሱ ወዲህ ጉዳዩ በሀገር ውስጥና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት እያገኘ መጥቷል፡፡

አቶ ኪያ ፀጋዬ ከመቀሌ ዩኒቨርሲቲ በህግ የመጀመሪያ ዲግሪ፣ በጣሊያን ከዩኒቨርሲቲ ኦፍ ቱሪን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በዓለም አቀፍ የኢኮኖሚና ፋይናንስ ህግ ሰርተዋል፡፡ ላለፉት 14 ዓመታትም በህግ ዙሪያ ጥናትና ምርምር በማድረግ፣ ስልጠና፣ የማማከርና የጥብቅና አገልግሎት በመስጠት እየሰሩ ይገኛሉ፡፡ በሀገራዊ ጉዳዮች ላይም ሀሳብና አስተያየት በመስጠት ይታወቃሉ፡፡ ከእሳቸው ጋር የኢትዮጵያ የባህር በር ጥያቄ አስፈላጊነት፣ የባህር በር ያጣችበት መንገድና ከዓለም አቀፍ ህግ አንጻር እንዴት እንደሚታይ ያደረግነውን ቃለ ምልልስ እንደሚከተለው አጠናቅረነዋል፤ መልካም ንባብ፡፡

### አዲስ ልሳን፡- የባህር በር ማግኘት ለኢትዮጵያ ያለውን አስፈላጊነት እንዴት ይገልፁታል?

**አቶ ኪያ፡-** ኢትዮጵያ የባህር በር ያጣችበት መንገድ በጣም ያስቆጫል፤ ኢትዮጵያዊ ብቻ ሳይሆን ለፍትህ የቆመ ማንኛውም ሰው ይህንን ይጋራዋል። በዚህ ምክንያትም ከፍተኛ ጉዳት ደርሶባታል። እንደአለመታደል በተለይ ከ1980ዎቹ ጀምሮ የመጣው ትውልድ በልዩ ሁኔታ በራስ ጥረትና ንባብ ከተረዳው ውጪ አብዛኛው ‘ወደብ’፣ ‘የባህር በር’፣ ‘የባህር ሀይል’ እንዲሁም ባህር ላይ ስላለ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ግንዛቤ የለውም፤ እንዲያውቅም አልተደረገም፡፡ የወደብ አልባነት ትርክት ሰለባ ነበር፡፡

የባህር በር ጥቅም ተቆጥሮ አያልቅም፡፡ በዋናነት ከውጪው ዓለም ጋር የሚያገናኝ መውጫ በር ነው፡፡ ቤት ሰርተህ መውጫ በር ከሌለው ወይም መግቢያህ በሰው ቤት ወይም በሰው አጥር ውስጥ ከሆነ፤ ያ የሚያሳልፈው ሰው የሆነ ቀን ደስ ካላልከው “የምታልፍበትን በር ዘግቼዋለሁ” ሊል ይችላል፡፡ ከቤትህ ለመውጣት የግለሰቡ መልካም ፈቃድና ችሮታ የግድ ያስፈልጋል፡፡ ኢትዮጵያም ትልቅ ሀገር ሆና፣ ትልቅ የህዝብ ቁጥር ይዛ፤ በታሪክም ከአንድ ሺህ ኪሎ ሜትር በላይ የባህር ጠረፍ የነበራት ሆና ሳለ፤ ከውስጥና ከውጭ በተደረገ ጫናና ሸፍጥ የባህር በር አጥታለች፡፡ ይህ ያስከተለው ችግር ዘርፈ ብዙ ነው፡፡ በኢኮኖሚው ረገድ ብናይ ለወጪና ገቢ ንግድ መውጫና መግቢያ ጂቡቲ ላይ ጥገኛ እንድንሆን አድርጎናል፡፡ ከ90 በመቶ በላይ የወጪና ገቢ ንግዳችን በአንድ ሀገር ላይ የተንጠለጠለ ሆኗል፡፡

በዓመት ለወደብ ኪራይ 2 ቢሊዮን ዶላር ወጪ እንከፍላለን፡፡ እንደ ቡና፣ የቆዳና ቆዳ ውጤቶችን እና መሰል ምርቶችን ወደ ውጭ በመላክ የሚገኘው የውጭ ምንዛሪ ለወደብ ኪራይ ክፍያ ይውላል፡፡ አንድ ሀገር ላይ ብቻ ጥገኛ በመሆናችንም፤ ከዚህ ቀደም እናገኛቸው የነበሩ ምቹ የወደብ ታሪፍ ህጎችና ጥቅሞች በየጊዜው እየጠበቁ መጥተዋል። ይህም የተፈጥሮ ሀብቶቻችንን በአግባቡ ወደ ውጪ በመላክ፣ ከሀብቶቹ ማግኘት ያለብንን ዋጋ እንዳናገኝ አድርጎናል፡፡

ባህር የዓለም ህዝብ የተፈጥሮ ሀብት ነው፡፡ ይህንን ሀብት ለመጓጓዣነትና ለተለያየ አገልግሎት የመጠቀም መብት ነው፡፡ የባህር በር የሌለን በመሆኑ ግን ተጠቃሚ መሆን አልቻልንም፡፡ ወደብ ትልቅ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ ሞተር ነው፤ ለሚሊዮኖችም የስራ ዕድል ይፈጥራል፡፡

ሌላው የራሳችን የባህር በር የሌለን በመሆኑ ከደህንነት አኳያ የእኛ የምንለው ምስጢር ብዙም እንዳይኖረን አድርጓል፡፡ ምክንያቱም እያንዳንዱ የምናስገባው እቃ ተፈትሾ ነው የሚገባው፡፡ ዛሬ ኢትዮጵያ በጦር መርከብ መሳሪያ ብታስገባ፤ ጠላት የሆነ ሀገር ጂቡቲ ላይ ቁጭ ብሎ የምታስገባው መሳሪያ ምን እንደሆነ ይቆጥራል፡፡ አንዳንድ በምስጢር መያዝ ያለባቸው እቃዎች ተጋላጭ በመሆናቸው ለደህንነት ስጋት ያጋልጠናል፡፡

ዛሬ ያለው ትውልድና አመራር ይህንን አንገብጋቢ ጉዳይ በማንሳቱ ሊመሰገን ይገባል፡፡ የባህር በር ለኢትዮጵያ እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ኢትዮጵያ በምስራቅ አፍሪካና አፍሪካ ቀንድ ቀጣና ትልቅ ሀገር ናት፡፡ ከአላት የህዝብ ቁጥር፣ የተፈጥሮ ሀብትና ኢኮኖሚ አኳያ ከአሁን በኋላ ያለባህር በር መቀጠል ከባድ ነው። አንድ መንግስት ሲፈልግ የሚዘጋብን ወይም የሚከፍትልን ሳይሆን እኛ የምንቆጣጠረው፣ ዓለም አቀፍ ህግን በተከተለና በሰጥቶ መቀበል መርህ ላይ በመመስረት የባህር በር ያስፈልገናል፡፡

የባህር በር የኢትዮጵያ ሀገረ መንግስት መቀጠልና አለመቀጠል ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ አለው፡፡ ዛሬ ጂቡቲ ላይ በርካታ ሀያላን ሀገራት የጦር ሰፈሮችን መስርተዋል። ቅኝ ገዥ ከነበረችው ፈረንሳይ ጀምሮ አሜሪካ፣ ጀርመን፣ ቻይና፣ ጃፓን፣ ጣሊያንና ሌሎች ሀገራት የጦር ሰፈር አላቸው፡፡ ነገ ከነገ ወዲያ በአካባቢው ግጭት ቢፈጠር፤ 90 በመቶ የወጪ ገቢ ንግድ በጂቡቲ ላይ በተንጠለጠለበት ሁኔታ፣ በአንድ ቀን መግባት ያለበት ነዳጅ ለአንድ ሳምንት ቢስተጓጎል የሀገሪቱ እስትንፋስ ቆመ ማለት ነው፡፡ ይህ ማለት በቀጥታ ያመረትነውን ቡና የምንሸጥበት መንገድ የለም ማለት ነው፡፡ ቀይ ባህር የኢትዮጵያን ዕጣ ፈንታ የሚወስን፤ የመኖርና ያለመኖር ጉዳይ ነው፡፡ ከደህንነት፣ ፀጥታ፣ ንግድ፣ ቱሪዝምና ጂኦፖለቲክስ አኳያ ወሳኝ በመሆኑ የባህር በር የማግኘት ጥያቄው ምላሽ እንዲያገኝ በትኩረት መሰራት ይኖርበታል፡፡

### አዲስ ልሳን፡- ኢትዮጵያ የባህር በር የማግኘት ጥያቄዋ በምን መንገድ ምላሽ ሊያገኝ ይችላል?

**አቶ ኪያ፡-** አሁን የባህር በሩን ጥያቄ አንሻፍፈው፣ ለፖለቲካ ፍጆታ ለማዋል የሚዳዳቸው አሉ፡፡ መንግስትም በተደጋጋሚ እንዳሳወቀው፤ እኔም በግሌ እንደማምነው የባህር በር የማግኘት ጥያቄያችን በዲፕሎማሲያዊ መንገድ ምላሽ ማግኘት ይችላል፡፡ መነጋገር ከተቻለ ለጎረቤት ሀገራት መስጠት የምንችለው የተፈጥሮ ሀብት ብዙ ነው። ለምሳሌ፡- በኤርትራ ከአንድ ሺህ ኪሎ ሜትር በላይ ርዝመት ያለው የባህር ጠረፍ ይገኛል፡፡ እኛ ካለን ሀይል 500 ሜጋ ዋት ሰጥተን፤ ቅንነት ካለ 20 ኪሎ ሜትር ወደ ባህር መውጫ በር ቢሰጡን ሁላችንም ተጠቃሚ እንሆናለን፡፡ በሰጥቶ መቀበል፣ መሬት ወይም ሌላ ሀብት በመለዋወጥ የባህር በር ያገኙ ሀገራትም አሉ፡፡ በቅን ልቦና እና በትብብር መንፈስ ለሚረዳ የኢትዮጵያ የባህር በር ጥያቄ ምንም ዓይነት የፖለቲካ ሸፍጥ የለበትም፡፡

ጎረቤት ሀገራት የኢትዮጵያ ጥያቄ ሰላማዊ መሆኑን በቅን ልቦናና በትብብር መንፈስ መረዳት አለባቸው፡፡ በቀዝቃዛው ጦርነት የነበረውን በጠላትነት የመተያየት የፖለቲካ ትርክት በ21ኛው ክፍለ ዘመን አስቀጥላለሁ የሚል አስተሳሰብ አሁን ቦታ የለውም፡፡ ዓለም ተለውጣለች። “ኢትዮጵያን አፍነን ወይም ዘግተን፣ በእኛ ተፅዕኖ ስርና ችሮታ እናኖራታለን” የሚለው አስተሳሰብ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ያመዝናል፡፡ ጉዳቱ ደግሞ አንድ ቦታ ብቻ የሚቆም አይደለም፡፡

130 ሚሊዮን ህዝብ ምንም ዓይነት መውጫ በር እንዳይኖረው አድርጎ አፍኖ የማኖር አስተሳሰብ በተለይ በኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች ገፋፊነት የሚደረገው እንቅስቃሴ ለጎረቤት ሀገራትም አያዋጣም፡፡ ዘመኑም፤ ትውልዱም ተቀይሯል፡፡ ትውልዱ መተባበርን ያስቀድማል፡፡ የትውልዱ ትልቁ ጥያቄ ንግድ፣ ኢንቨስትመንት፣ ኢኮኖሚ፣ የስራ ዕድል ፈጠራ ነው፡፡ በባዶ ሽለላና ቀረርቶ፣ ወታደራዊ ሰልፍ በማሳየት የህዝብ ሕይወት አይቀየርም፡፡

ላለፉት 34 ዓመታት ኤርትራ ውስጥ ምን ዓይነት ልማት እንዳለ ይታወቃል፡፡ የኢትዮጵያ ጥያቄ በጋራ እንጠቀም ነው። ዛሬ ኤርትራ ውስጥ የሀይል ችግር ስላለ የሲሚንቶ ፋብሪካ የለም፡፡ የሲሚንቶ ችግር ካለ ደግሞ የግንባታ እንቅስቃሴ አይኖርም፡፡ ለሲሚንቶ ፋብሪካ የሚሆን ሀይል ደግሞ ኢትዮጵያ ውስጥ አለ፡፡ እኛ ሀይል ስንሰጥ፤ እነሱ ደግሞ የባህር በር ሊሰጡን ይገባል፡፡ ይህ ሉዓላዊነትን የሚጋፋ አካሄድ አይደለም፡፡ ሁሉንም አሸናፊ የሚያደርግ መንገድ ነው፡፡

ኤርትራና ሌሎች ጎረቤት ሀገራት መረዳት ያለባቸው “ኢትዮጵያ የሌላን ሀብት ልዝረፍ አላለችም፡፡ ኢትዮጵያ በተፈጥሮ ሀብት የታደለች ሀገር ናት። ትላልቅ የኢኮኖሚ አውታሮችን ገንብታለች፡፡ በአፍሪካ ትልቁ አየር መንገድ የሆነው የኢትዮጵያ አየር መንገድ ባለቤት ናት፡፡ ትልቅ የንግድ መርከብ አላት፡፡ ከእነዚህ እና መሰል ፕሮጀክቶች አካፍለን በሰጥቶ መቀበል መርህ የባህር በር እንዲሰጡን ነው የምንፈልገው፡፡ አሁን ያሉት መሪዎች የባህር በርን አጀንዳ ማድረጋቸው ሊመሰገኑ ይገባል፡፡ ልጆቻችን “ኢትዮጵያ የባህር በር የሌላት ለምንድን ነው?” እያሉ መጠየቅ ጀምረዋል፡፡ ኤርትራም ብንሄድ አዲስ ትውልድ ተፈጥሯል፡፡ “ነፃ ሀገር በመሆናችን ምን ትርፍ አገኘን? ከኢትዮጵያ ጋር በኢኮኖሚ ተሳስረን ተባብረን ብንሰራ ምን እናጣለን?” የሚል ምክንያታዊ ጥያቄ ማንሳት ጀምረዋል፡፡

### አዲስ ልሳን፡- ኢትዮጵያ የባህር በር ካጣች በኋላ የባህር በር ባለቤት እንድትሆን ሲደረግ የነበረ ጥረት አለ ወይ? ካለስ ምን ይመስላል?

**አቶ ኪያ፡-** በ1960ዎቹ የኤርትራ ነፃነት እንቅስቃሴ ሲጀመር ከፍተኛ ድጋፍ ሲያደርጉ የነበሩት በመካከለኛው ምስራቅ የሚገኙ የአረብ ሀገራት ናቸው። ቀይ ባህርንም ‘የአረብ ባህር’ እያሉ ነው የሚጠሩት፡፡ እነ ጀብሃ ኤርትራን ለመገንጠል ሲንቀሳቀሱ የመጀመሪያ ድጋፍ ያደረገችው በትጥቅ፣ በስልጠናና ስምሪት በመስጠት ግብፅ ናት፡፡ ሬዲዮ ጣቢያ በመክፈት ፀረ ኢትዮጵያ ፕሮፖጋንዳዎችን ስታስተላለፍ ነበር፡፡

በተማሪዎች ንቅናቄም ኢትዮጵያውያን ወጣቶች በስህተት በእነሱ ወጥመድ ውስጥ የገቡበት ሁኔታ ነበር፡፡ በዚያን ጊዜ አንድ ተማሪ ተራማጅ ለመባል የኤርትራ መገንጠልን በመደገፍ ‘የኤርትራ ጥያቄ ትክክለኛ የቅኝ ግዛት ጥያቄ ነው፤ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ነፃ መውጣት አለባት’ በሚል ያስረዳ ነበር፡፡ በዚያን ጊዜ የነበሩ የፖለቲካ ፓርቲዎች ብዙዎቹ የተቃኙት ቀድሞ እንቅስቃሴውን በጀመሩት በአብዛኛው የኤርትራ ተማሪዎች ነበር፡፡ እነዚህ ተማሪዎች የትግራይንም ተማሪዎች በመያዝ ወደ ተማሪዎች ንቅናቄ በመግባት የኤርትራ ጥያቄ ሳይንሳዊ እንደሆነ፣ ኢትዮጵያ ከባህር ጋር ያላት ቁርኝት ግምት ውስጥ ባላስገባ መልኩ በጥራዝ ነጠቅ ሲያቀነቅኑ ነበር፡፡ ትርክቱ በመጨረሻም የኤርትራ ነፃ አውጪ ግንባር፣ የትግራይ ነፃ አውጪ ግንባር ፈጠረ፡፡ በሰነዶችም

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ የሚቀርብ

# የወንጀል ሕግ ምንነት፣ አላማው እና የወንጀል መከላከያ መንገዶች

## የመጨረሻው ክፍል

**ይነበብ ታምሩ (ዐቃቤ ህግ)**

ባለፈው ዕትማችን በዋናው ርዕስ በወንጀል ህግ የህዝብን ሰላምና ደህንነት እንዲሁም ንብረት መጠበቅ እና ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል በሚል ንዑስ ርዕስ ስር ስለወንጀል ምንነት፣ የወንጀል ህግ ዓላማ በሚሉት ላይ መረጃ ማጋራታችን ይታወሳል፡፡ የፅሁፉን የመጨረሻ ክፍል እንደሚከተለው አቅርበነዋል።



### ሐ) ወንጀለኛውን ወደ ቀደመ ሰላማዊ ህይወቱ መመለስ (rehabilitation)

የሰው ልጅ በተለያየ ምክንያት ወደአልተፈለገ ተግባር በመግባት ወንጀል ይፈጽማል፤ ነገር ግን ከዚህ ስህተቱ እንዲማር ብሎም መልካም እና ብቁ ዜጋ እንዲሆን የሕግ ተቋማት የማይተካ ሚና አላቸው፡፡ የወንጀል ሕግም ትልቁ አላማው ይህ ነው፡፡ ወንጀል የሰሩ ሰዎች በፍርድ ቤት ጉዳያቸው ታይቶ ቅጣት የሚጣልባቸው ቅጣቱን እንደበቀል በመቁጠር ለመበቀል ሳይሆን ላጠፉት ጥፋት በመፀፀት እና ወደቀደመ ሰላማዊ ህይወት እንዲመለሱ በማድረግ ለሀገር አስተዋጽዖ እንዲያደርጉ ማስቻል ነው። ለዚህም ዋነኛ ማሳያው በወንጀል ህግ አንቀጽ 157፣ 162 እና በተከታዮቹ ላይ እንደተገለጠው እድሜያቸው ከዘጠኝ ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት የሆኑ ወጣት አጥፊዎች ሕግ ተላልፈው በሚገኙበት ወቅት ፍርድ ቤቱ በመጀመሪያ የሚያደርገው እነሱን ያርማል ወደሚባልበት ተቋም እንዲሄድ በማድረግ ከጥፋታቸው እንዲታረሙ ያደርጋል፡፡ በዚህም ወጣቱ ተገቢ የሆነ ትምህርትን፣ ግብረ ገብነትን /ሞራልን/ እና ልዩ ልዩ ሙያ የሚማሩበት እና ወደ ማህበረሰቡ እንዲመለሱ የሚደረጉበት ነው።

ሌላው በወንጀል ህግ አንቀጽ 51፣ 48 እና 49 ወንጀል ፈጽመው የተገኙ አካላት በአንቀጽ 130 መሰረት ወንጀል አድራጊው ካለበት ችግር የተነሳ በሰዎች ላይ ጉዳት እንዳያደርስ እና የህዝብን ሰላም እና ጸጥታ እዳያደፈርስ ህክምና ወደ ሚያገኝበት ተቋም እንዲሄድ እና ወደ ቀደመ ማህበራዊ ህይወቱ እንዲመለስ የሚደረግበት አሰራር አለ፡፡ እንዲሁም በአንቀጽ 190 ላይ በመርህ ደረጃ እንደተቀመጠው ለጥፋቱ መነሻ የሆኑትን ምክንቶች በመመልከት ጥፋተኛውን ለማረም እና ለማሻሻል እና ወደ መደበኛ ማህበራዊ ህይወቱ ለመመለስ ጠቃሚ ከሆነ እና ፍርድ ቤቱ ካመነ በገደብ የሚለቀቅበት እና የተሰጠውን የጊዜ ገደብ ተጠቅሞ መልካም የሆነ ፀባይ ካሳየ ቅጣቱ እማይፈጸምበት እና ፍርዱ እንዳልነበረ የሚቆጠርበት ሁኔታ አለ፡፡

እንዲሁም መንግስት ዘመኑን የዋጀ እና ለታራሚ አመች የሆነ ማረሚያ በማቋቋም ታራሚዎች በቆይታቸው ከጸባይ እና መልካም ስነ ምግባር ባለቤት ከመሆን በተጨማሪ የተለያዩ የሙያ ባለቤት እንዲሆኑ እና ራሳቸውን እንዲችሉ ሙያ የሚማሩ ሲሆን፤ በዚህ ሙያቸውም የተለያዩ ስራዎችን እንዲሰሩ በማድረግ እቃዎችን መሸጥ የሚችሉ ሲሆን፤ ከዚህ ጎን ለጎን መደበኛ ትምህርትም እንዲማሩ በማድረግ ለሀገር የተማረ ዜጋ ከማፍራት አንጻር ማረሚያ ቤቶችም የበኩላቸውን አስተዋጽዖ ያደርጋሉ፡፡ ለዚህ ትልቁ ማሳያው የሸገር ኤፍም 102.1 በመስከረም 30/1/2018 ላይ የማረሚያ ቤት ኃላፊዎችን ዋቢ አድርጎ እንደዘገበው በማረሚያ ቤት ውስጥ የነበሩ ታራሚዎች በ2017 ዓ.ም የ12ኛ ክፍል ሀገር አቀፍ ፈተና በፌደራል ማረሚያ ቤት ኮሚሽን ስር ከነበሩ በዝዋይ እና በአባ ሳሙኤል ማረሚያ ቤቶች የነበሩ እና በሁለቱም ማረሚያ ቤቶች ከነበሩ 72 ታራሚ ተማሪዎች ውስጥ በቀጥታ እና በሬሜዲያል 58 ተማሪዎች የዩኒቨርስቲ መግቢያ ውጤት አምጥተዋል። ይህ የሚያመለክተው የተለያዩ ወንጀሎችን ፈጽመው ወደ ማረሚያ ቤት የሚገቡት ላጠፉት ጥፋት እንደ በቀል ሳይሆን ከስሙ እንደምንረዳው ወደ ማረሚያ በመግባት ፀባያቸው ታርሞ እና መልካም ስነ-ምግባር ይዘው ወደ ህብረተሰቡ እንዲቀላቀሉ በማሰብ ነው።

### መ) አጥፊውን መቅጣት

የወንጀል ህግ ዋነኛ አላማ የወንጀል ድርጊት ፈፅመው የተገኙ አካላትን ተገቢውን የሆነ ትምህርት በመስጠት ወደ ቀደመ መልካም ስብዕናቸው መመለስ ቢሆንም ነገር ግን ሁሉም ጥፋተኞች ደግሞ ራሳቸውን ለማሻሻል ከመጠቀም ይልቅ ሌሎች ተጨማሪ ወንጀሎችን መስራት ይቀላቸዋል፡፡ በዚህ ጊዜ በወንጀል ህግ በተቀመጠው መሰረት ለየጥፋታቸው ፍርድ ቤት ተገቢ ነው የሚለውን ቅጣት ይጥላል ለአብነትም ያህል ቅጣቱ እንደ አፈጻጸሙ እና እንደ ወንጀል አይነቶች ቢለያይም ከጽኑ እስራት ጀምሮ እስከ እድሜ ልክ እስራት የሚቀጡበት ሲሆን እስካሁን ተግባራዊ ባይሆንም የሞት ቅጣትም አንዱ ነው፡፡

### የወንጀል መከላከያ መንገዶች

ወንጀል ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ እና እየተስፋፋ እንዲሁም የሚፈጸምበት መንገድም የተወሳሰበ እየሆነ መጥቷል፡፡ እንዲሁም ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ጭካኔ የተሞላባቸው እየሆኑ መጥተዋል፡፡ በተለይም እንደሀገራችን ኢትዮጵያ ባሉ ብዙ ብሔር ብሔረሰቦች በሚኖሩበት እንዲሁም ካለን አንዱ ከአንዱ ጋር የመከባበር እና የመተሳሰብ ባህል አንጻር አሁን ላይ በየሚዲያው የምንሰማቸው የወንጀል ድርጊቶች ከበድ የሚሉ ናቸው። ከዚህ አንጻር ይህንን አብሮ በጋራ የመኖር እና የመከባበር እሴት እንዲዳበር፣ እንዳይጠፋና እንዲቀጥል እንዲሁም እነዚህ አሰቃቂ ድርጊቶች አስቀድሞ እንዲቆሙ በመከላከል የወንጀል ሕግ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል። ሀገራችንም ይሄንን እየተራቀቀ እና በተለያየ መልኩ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን ለመከላከል እና ሰላማዊ ህይወት እንዲኖር በተለያዩ ጊዜ ወጥተው የነበሩ የወንጀል ሕጎችን በማሻሻል እና እነዚህ አዳዲስ የወንጀል ድርጊቶችን በወንጀል ህግ በማካተት ሕብረተሰቡ ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ጉዳቶች መከላከል ተችሏል። እንደሚታወቀው አንድ ወንጀል በሀገራችን ወንጀል ለመባል በወንጀል ህግ ላይ በግልጽ መቀመጥ እና መጠቀስ አለበት ይህም ዜጎች በእንቅስቃሴያቸው ወቅት ቅድሚያ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ እና ሕግን አክብረው እና ተከትለው እንዲኖሩ ያደርጋቸዋል። እንዲሁም የወንጀል ሕጋችን ወንጀሎችን በድንጋጌ ብቻ ማስቀመጥ ሳይሆን ጥፋተኛ ሆነው የሚገኙ አካላትን ከጥፋታቸው ተምረው ላጠፉት ጥፋት ህብረተሰቡን የሚክሱበት ብሎም ለራሳቸው ጠቃሚ ዜጋ እንዲሆኑ የሚያደርጋቸውንም ድንጋጌ በማካተት ከቀደመ ድርጊታቸው እንዲማሩ እና ሌላ ተጨማሪ ወንጀል እንዳይፈጽሙ ይከላከላል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ወንጀል መፈጸም የሚያመጣውን ከፍተኛ የሆነ ሀገራዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ብሎም ቤተሰባዊ ችግር በተለያየ መልኩ ለህብረተሰቡ በመግለጥ ወንጀል ከመፈጸም እንዲቆጠብ በማድረግ ወንጀልን መከላከል ይቻላል። ሌላው ወንጀል አጥፍተው የተገኙ አካላትን ሕግን ተከትሎ እና መሰረት አድርጎ ላጠፉት ጥፋት ተመጣጣኝ የሆነ ቅጣት በመጣል በመጀመሪያ አጥፊዎቹ ከራሳቸው እንዲማሩ እና ተጨማሪ ወንጀል እንዳይሰሩ መከላከል ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ሌሎች የህብረተሰብ ክፍል ከሌሎች ወንጀል አድራጊዎች ቅጣት በመማር ተጨማሪ ወንጀል እንዳይፈጽሙ ይከላከላል፡፡

# ማስታወቂያ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ
CLEANSING MANAGMENT AGENCY
— ADDIS ABABA CITY ADMINISTRATION —

በአካባቢዎ የሚገኙ ደረቅ ቆሻሻዎች ሀብት መሆናቸውን ያውቃሉ?

ደረቅ ቆሻሻን ሰብስቦ ማቃጠል ለአየር ብክለት ለውጥ ጉልህ ሚና እንዳለውስ ልብ ብለዋል?

ደረቅ ቆሻሻን ማቃጠል አካባቢዎን ፅዱ ማድረግ እንዳልሆነስ ተገንዝበዋል?

ልብ ይበሉ በየዓመቱ ደረቅ ቆሻሻን ወደ ሀብት በመቀየር በቢሊዮን የሚቆጠር ብር መሰብሰብ ተችሏል፤ የውጭ ምንዛሬም በማምጣት ላይ ይገኛል።

ደረቅ ቆሻሻ በሚቃጠልበት ወቅት የአየር ብክለትን የሚያስከትሉ ኬሚካሎች በመኖራቸው ለሰው ልጆች ጤና መታወክ ምክንያት ይሆናል፤ የአካባቢዎን ቆሻሻ ማቃጠል ወንጀል መሆኑን ተገንዝበው ቆሻሻዎችን ሰብስቦ ለህብረት ሽርክና ፅዳት ማህበራት በአግባቡ በማስረከብ የበኩልዎን ይወጡ የሚሎት የአዲስ አበባ ከተማ ፅዳት አስተዳደር ኤጀንሲ ህዳር 12ን ምክንያት በማድረግ በሁሉም ክፍለ ከተሞች እና ወረዳዎች እስከ ብሎክ የዘለቀ የፅዳት ንቅናቄ ህዳር ሲፀዳ አካባቢያችን ጤና በሚል መሪ ቃል አዘጋጅቷል።



በዕለቱም ሁሉም ማህበረሰብ እና ተቋማት ህዳር ሲታጠን ሳይሆን ህዳር ሲፀዳ በሚል ሀሳብ አካባቢውን እንዲያፀዳ ጥሪውን ያቀርባል።

**ህዳር ሲፀዳ አካባቢያችን ጤና!**
**የአዲስ አበባ ከተማ ፅዳት አስተዳደር ኤጀንሲ**

## የጨረታ ማስታወቂያ

የአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ በ2018 በጀት ዓመት በጨረታ መለያ ቁጥር:- **አ/አ/አ/አካ/ግ/ጨ-0002/2018 ዓ.ም** ለአካዳሚው ስልጠናና የተለያዩ የውይይት መድረኮች የሚሰጡ የመስተንግዶ አገልግሎትን በዘርፉ የተሰማሩ አቅራቢዎችን አወዳድሮ አገልግሎቱን መግዛትና ማሰራት ይፈልጋል፡፡

**ስለሆነም ከዚህ በታች የተገለፁትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ተጫራቾች እንዲሳተፉ ተጋብዟል:-**

1. የንግድ ስራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት
2. የግብር ከፋይነት ሰርተፊኬት (TIN)
3. የአቅራቢነታቸውን ሁኔታ የሚገልፅ ከመንግስት ግዥ ኤጄንሲ የተሰጠ የምዝገባ ምስክር ወረቀት
4. የተ.እ.ታ ምዝገባ ምስክር ወረቀት (VAT)
5. ከግብር ሰብሳቢ መ/ቤት የተሰጠ ወቅታዊ የግብር ክፍያ ማረጋገጫ
6. የጨረታ ሂደቱ የመንግስትን የጨረታና የግዥ ሂደት የተከተለና በግዥ መመሪያዉ መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
   - ➢ ተጫራቾች ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጨረታ ሰነዱን አራት ኪሎ ከብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ወደ ፒያሳ በሚወስደው መንገድ 200ሜትር ላይ በሚገኘው ዳብር ህንፃ ሦስተኛ ፎቅ የግዥ ዳይሬክቶሬት ቢሮ ዘወትር በሥራ ሰዓት በመቅረብ በብር 200 ሰነዱን መግዛት ይችላሉ፡፡
   - ➢ ተጫራቾች 200,000.00 (ሁለት መቶ ሺህ) የብር መጠን ያለው የጨረታ ማስከበሪያ "ለአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ" በሚል አድራሻ በባንክ የክፍያ ትዕዛዝ (C.P.O) ወይም ቅድመ ሁኔታ ባላስቀመጠ የባንክ ዋስትና ወይም በጥቃቅንና አነስተኛ የተደራጁ ከሆነ ካደራጃቸው መ/ቤት የዋስትና ደብዳቤ "ለአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ" በሚል አድራሻ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
   - ➢ ጨረታው በሁለት(2) ኤንቬሎፕ የሚቀርብ ሆኖ ተጫራቾች አስፈላጊ የሆኑ ህጋዊ የቴክኒካል ሰነዶችን እና የጨረታ ማስከበሪያ (C.P.O)፣ በማለት በኦርጅናል እና በኮፒ እንዲሁም ዋጋ የያዘዉን ፋይናንሻል ሰነድ በኦርጅናል እና ኮፒ በማዘጋጀት በአንድ እናት ፖስታ በማሸግ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
   - ➢ ተጫራቾች ከአካዳሚው በወሰዱት የጨረታ ሰነድ የተጠየቁትን ሞልተውና እያንዳንዱ ገጽ ላይ ማሕተም በመምታት መመለስ ይኖርባቸዋል፡፡
   - ➢ ጨረታው ማስታወቂያው በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ10 (አስር) የስራ ቀናት የሚቆይ ሆኖ በ11ኛው የስራ ቀን ከላይ በተጠቀሰው አድራሻ ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ታሽጎ በዚሁ ዕለት ጠዋት 4፡30 ሰዓት ተጫራች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል፡፡
   - ➢ የጨረታው መክፈቻ አስራ አንደኛው ቀን በዓል ከሆነ ቀጥሎ በሚገኘው የስራ ቀን የሚከፈት ይሆናል፡፡
   - ➢ አካዳሚው የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

ስለ ጨረታው ተጨማሪ መረጃ ማግኘት ካስፈለገ ቀጥሎ ባለው የስልክ ቁጥር ደውሎ መጠየቅ ይቻላል:-

☏ 0116- 67-33-90

**የአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ አዲስ አበባ**

# ተቋማቱ ከሰልጣኞች ምዝገባ ጋር በተያያዘ ምን ገጠማቸው?

- **ከ2008 ዓ.ም በፊት የ12ኛ ክፍል ትምህርታቸውን ያጠናቀቁ ተማሪዎች ለምዝገባ ወደ ቴክኒክና ሙያ ቢያቀኑም መመዝገብ እንዳልቻሉ ገልጸዋል**
- **ትምህርት ፈላጊዎቹ በማንዋል እንዲመዘገቡ ለኮሌጆቹ ማሳወቁን ቢሮው ጠቁሟል**

**በስንታየሁ ምትኩ**

ወጣት አሰፋ ደመመው በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 7 ነዋሪ ነው፡፡ በ2007 ዓ.ም የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ወስዶ ወደ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም በመግባት በ2011 ዓ.ም በአግሪ ቢዝነስና ቫልዩቼን ማኔጅመንት የትምህርት መስክ የመጀመሪያ ድግሪውን እንዳገኘ ይናገራል፡፡

ከምርቃት በኋላ በተመረቀበት የስራ መስክ ስራ ማግኘት ባለመቻሉ የተሻለ ስራ የሚያገኝበትና በግሉም መስራት የሚችልበት የስራ መስክ ለመማር በመወሰን በንፋስ ስልክ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ኤሌክትሪካልና ኤሌክትሮኒክስ የትምህርት ዘርፍ ስልጠና ለመውሰድ መምጣቱን ይናገራል፡፡ ነገር ግን የመመዝገቢያ ሲስተሙ (ኢ-ስኩል) ከ2008 ዓ.ም በፊት የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና የወሰዱትን መመዝገብ እንደማይችል፣ ለጊዜው ስምና ስልክ ቁጥራቸውን ሰጥተው፣ የአዲስ አበባ ከተማ ስራና ክህሎት ቢሮ ሲፈቅድ የሚመዘገቡ መሆኑን እንደተነገራቸውና እየተጠባበቁ እንደሆነ ወጣት አሰፋ ያስረዳል፡፡




ፎቶ በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል

በተለያየ የሙያ መስኮች ስልጠና በመስጠት የሚታወቀው የንፋስ ስልክ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ

የሙያ ስልጠናው በቅጥር አሊያም በግል መስራት የሚችልበትን እድል የሚያሰፋ መሆኑን የሚያነሳው ወጣት አሰፋ፣ የቴክኒክና ሙያ ተቋማት ክህሎት የሌላቸውን ሰዎች የሙያ ባለቤትና ስራ ፈጣሪ ለማድረግ የተቋቋሙ እንደመሆናቸው ችግሩ ተፈትቶ መማር የሚችሉበት ሁኔታ እንዲፈጠር ጠይቋል።

ሌላኛው አስተያየቱን ያጋራን በአዲስ አበባ ከተማ በተለምዶ ካዲስኮ እየተባለ በሚጠራው አካባቢ ነዋሪ የሆነው ወጣት ሚኪያስ ብርሃነ ነው፡፡ የ12ኛ ክፍል ትምህርቱን ያጠናቀቀው በ2007 ዓ.ም ሲሆን አክሱም ዩኒቨርሲቲ በመግባት በኮምፒዩተር ኢንጂነሪንግ የመጀመሪያ ድግሪውን ይዟል፡፡ በተማረበት የትምህርት መስክ እየሰራበት ባለመሆኑ ራሱን ለማሻሻል በማታው ክፍለ ጊዜ በደረጃ 4 በሀርድዌር ኔትዎርኪንግ ሰርቪስ የትምህርት መስክ በንፋስ ስልክ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ለመማር ቢያመለክትም፤ ሲስተሙ ከ2008 ዓ.ም በኋላ የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ የወሰዱትን እንደማይቀበል እንደነገሩት ይገልፃል፡፡ "ስምና ስልክ ቁጥራችንን ሰጥተናል፤ የኮሌጁ ሬጂስትራር ኃላፊ ሳነጋግረው መፍትሔ እስኪመጣ ጠብቁ፤ እንደውላለን" የሚል ምላሽ እንደሰጧቸው ወጣት ሚኪያስ ነግሮናል፡፡

ሌላኛዋ አስተያየት ሰጪ ወይዘሮ ፋንቱ ተመስገን ይባላሉ፡፡ ልጃቸው (ወጣት ዮናታን ታሪኩ) የ12ኛ ክፍል ፈተናን በ2004 ዓ.ም ወስዶ የከፍተኛ ትምህርት መግቢያ ውጤት ያመጣ ቢሆንም በግል ችግር ምክንያት ወደ ዩኒቨርሲቲ አልገባም፡፡ አሁን ላይ ልጃቸው የሙያ ባለቤት በመሆን ስራ ሰርቶ የሚለወጥበት ሁኔታ ለመፍጠር በንፋስ ስልክ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ለማስመዝገብ ቢያቀኑም ማስመዝገብ እንዳልቻሉ ይናገራሉ፡፡

ከተመዝጋቢዎች የተነሱ ቅሬታዎችንና አስተያየቶችን በመያዝም የንፋስ ስልክ ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ የሚመለከታቸው ኃላፊዎችን ጠይቀናል፡፡ ወይዘሮ መስከረም አሰፋው የንፋስ ስልክ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ የስልጠና እና አካዳሚክ ጉዳዮች ምክትል ዲን ናቸው፡፡

ኮሌጁ በ2018 የትምህርት ዘመን በቀን፣ በማታ እንዲሁም ቅዳሜና እሁድ 1 ሺህ 625 ተማሪዎችን ለመቀበል አቅዶ ምዝገባ እያከናወነ ሲሆን (ይህ ጽሁፍ እስከተጠናቀረበት ህዳር 2 ቀን 2018 ዓ.ም) 1 ሺህ 219 ተማሪዎችን በሲስተም (E-School) በማስደገፍ መዝግቧል፡፡

ወይዘሮ መስከረም እንደገለፁት፣ በዋናነት የ2018 የትምህርት ዘመን የሚመዘገቡት የ12ኛ ክፍል ሀገር አቀፍ መልቀቂያ ፈተና ወስደው የመግቢያ ነጥብ ያላመጡ ተማሪዎች ናቸው፡፡ ከ2008 ዓ.ም በፊት የ12ኛ ክፍልን አጠናቅቀው ለመመዝገብ የሚመጡ ተማሪዎችን ለመመዝገብ ሲስተሙ የማይፈቅድ በመሆኑ፣ የአዲስ አበባ ከተማ የስራና ክህሎት ቢሮ አቅጣጫ እስኪሰጥ ድረስ በማንዋል (ወረቀት ላይ) እንዲመዘገቡ ተደርጓል፡፡ በሲስተም መመዝገብ ላልቻሉ ሰልጣኞች "ጉዳዩን የስራና ክህሎት ቢሮ እንዲያውቀው መደረጉንና ቢሮው በሚወስነው መሰረት እንደሚስተናገዱ" እንደተነገራቸው ገልጸዋል፡፡

የንፋስ ስልክ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ የሬጅስትራር ኃላፊ አቶ ሀብቶም አፅባሃ በኮሌጁ የ2018 የትምህርት ዘመን ምዝገባ በቴክኖሎጂ (ኢ-ስኩል) ስርዓት ተደግፎ እየተከናወነ ቢሆንም መመዝገብ የሚችሉት የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተናን በ2008 ዓ.ም እና ከዚያ በኋላ የወሰዱት ብቻ መሆናቸው ችግር እየፈጠረባቸው እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡ ከ2008 ዓ.ም በፊት የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና የወሰዱ አብዛኛው በእድሜ ከፍ ያሉና በማታው መርሃ ግብር ለመማር የሚፈልጉ ናቸው፡፡ ከ2008 ዓ.ም በፊት የ12ኛ ክፍል ሀገር አቀፍ ፈተና የወሰዱ 36 ትምህርት ፈላጊዎች በኮሌጁ ለመማር ቢያመለክቱም በሲስተሙ ምክንያት መመዝገብ ስላልተቻለ፣ የአዲስ አበባ ስራና ክህሎት ቢሮ ውሳኔ እንዲሰጥ ጥያቄ ማቅረባቸውንና እስከዚያው ድረስ ስማቸውንና የስልክ ቁጥራቸውን በመስጠት እንዲሄዱ ተደርጓል፡፡ "እንመዘግባችሁም አላልናቸውም፤ ስምና ስልክ ቁጥራቸውን ሰጥተው እንዲሄዱ ነው ያደረግናቸው፡፡ በማንዋል መዝግቡ ከተባልን እንመዘግባለን" ሲሉ ችግሩን በተመለከተ አቶ ሀብቶም አብራርተዋል፡፡

አቶ ሀብቶም፣ አሰልጣኞች የሰልጣኞችን ውጤት ወደ ሬጅስትራር የሚልኩት በኦንላይን ነው፡፡ በሲስተሙ መመዝገብ ያልቻሉ ሰዎች ቢመዘገቡ፣ ስማቸውን ኦንላይን ላይ ማግኘት አይቻልም፡፡ ባለፈው ዓመት በነበረው ምዝገባም በኢ-ስኩል እና በማንዋል የተመዘገቡ ሁለት ዓይነት ሰልጣኞች ነበሩ፡፡ ይህ ጉራማይሌ የሆነ አሰራር ለፋይል አያያዝና አስተዳደር የማይመች በመሆኑ፣ ከ2008 ዓ.ም ወደኋላ ያሉትንም ማስገባት እንዲቻል ሲስተሙ ላይ ማስተካከያ እንዲደረግ ጠይቀናል ብለዋል፡፡

በተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ከ2008 ዓ.ም በፊት የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና የወሰዱ፤ በዲፕሎማ፣ በድግሪና በሌላ ደረጃ ተመርቀው በኮሌጁ ለመማር የሚፈልጉ አመልካቾችን ለመመዝገብ ሲስተም የማይቀበል ቢሆንም፤ በማንዋል (ወረቀት) በመመዝገብ እየተቀበሉ እንደሚገኙ በኮሌጁ የሬጅስትራር ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ስመኝ ሚዴቅሳ ለዝግጅት ክፍላችን አብራርተዋል፡፡

## ቢሮው ምን ይላል?

አቶ ነጋ አርጋው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የስራና ክህሎት ቢሮ የውጤት ተኮር ትምህርትና ስልጠና ዳይሬክተር ናቸው፡፡ በ2018 የትምህርት ዘመን ተማሪዎች በቴክኒክና ሙያ ተቋማት ለመመዝገብ የኢትዮጵያ ስራ ገበያ መረጃ አስተዳደር ስርዓት (Ethiopia Labor market Information system) በመታገዝ በስልክ ቁጥራቸው ከተመዘገቡ በኋላ ኮሌጅ ሬጅስትራር በመሄድ የሙያ ዝንባሌያቸውን በመምረጥ ፈተና ይወስዳሉ፡፡ በውጤታቸው መሰረትም የትኛው ዘርፍ ላይ ቢማሩ የተሻለ እንደሚሆን መረጃ (ምክረ ሀሳብ) ያገኛሉ፡፡

ከዚህ በመቀጠልም በከተማ አስተዳደሩ የለማ የተማሪዎች መመዝገቢያ ሲስተም (ኢ-ስኩል) ይመዘገባሉ፡፡ በዚህ ሂደት በመታገዝ በከተማዋ የሚገኙ 14 የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጆች ምዝገባ እያከናወኑ ይገኛሉ፡፡ እስከአሁን ድረስም (መረጃውን እስካጠናቀርንበት እስከ 4/03/18 ዓ.ም ድረስ) ከ13 ሺህ በላይ ተማሪዎች ተመዝግበዋል፡፡ በከተማ ደረጃም በቀን፣ በማታ እንዲሁም በቅዳሜና እሁድ ፕሮግራም እስከ 19 ሺህ 500 ተማሪዎችን ለመቀበል ታቅዷል፡፡

ከምዝገባው ሂደት ጋር በተያያዘ በቴክኖሎጂ ተደግፎ የሚከናወነው (ኢ-ስኩል) ላይ የሚነሱ ቅሬታዎችን በተመለከተም አቶ ነጋ ሲመልሱ፣ ሲስተሙ ማስተካከያዎች የሚፈልጉ ነገሮች ቢኖሩም ባለው እየተሰራበት ነው። ሲስተሙ ከ2008 ዓ.ም በፊት የ12ኛ ክፍል ፈተና የወሰዱ ተማሪዎችን መቀበል አይችልም፡፡ ከዚህ በፊት የሆነ ቦታ ደረጃ ሁለት ወይም ሌላ ስልጠና ወስደውና የምስክር ወረቀት ይዘው የመጡት ተመዝጋቢዎችን ላያስተናግድ ይችላል። እነዚህን ሁለት መሰረታዊ ችግሮች እንዲስተካከሉ ሲስተሙን ላበለፀገው ድርጅት በደብዳቤ ጥያቄ መቅረቡንና በየጊዜው ክትትል እየተደረገበት እንደሚገኝ አቶ ነጋ ተናግረዋል፡፡

የዝግጅት ክፍላችን ባደረገው ቅኝት ከ2008 ዓ.ም በፊት የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ወስደው፣ በሲስተም ችግር ምክንያት ምዝገባ ያላካሄደና የእናንተን ውሳኔ የሚጠብቅ ኮሌጅ አለ። ለዚህ ምላሻችሁ ምንድን ነው ያልናቸው አቶ ነጋ፣ "ሲስተሙ እስኪስተካከል ድረስ በማንዋል (ወረቀት) መመዝገብ የሚያስችል፣ ሲስተሙን ባለማው ድርጅት የተዘጋጀ የተመዝጋቢዎች መሰረታዊ መረጃ የያዘ ቅፅ (ቴምፕሌት) አለ፡፡ ይህንንም ለኮሌጆች ልከናል፡፡ አንዳንድ ተማሪዎች ጥያቄ ሲያቀርቡም 'ተቀበሏቸው' እያልን እያሳወቅን፤ በዚህ መሰረት ምዝገባ እያከናወኑ ይገኛሉ" ሲሉ መልሰዋል።የንፋስ ስልክ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ላይ የተነሳውን ችግር በተመለከተም፤ "ተማሪዎችን እንዲቀበሉ ደውለንላቸዋል። በቴምፕሌት እንዲመዘግቧቸው ነግረናቸዋል፡፡" ብለዋል፡፡

የዝግጅት ክፍላችን ዳይሬክተሩ ያሉት ነገር ተፈጻሚ ስለመሆኑ ወደ ንፋስ ስልክ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ አቅንተው ከነበሩት ተመዝጋቢዎች የተወሰኑት ላይ ደውሎ ትክክል ስለመሆኑ ማረጋገጫ አግኝቷል፡፡

# አዳዲስ የመዲናዋ ጥበባዊ መረጃዎች

በአብርሃም ገብሬ

ባሳለፍነው ሳምንት በመዲናዋ አዲስ አበባ የተለያዩ ኪነ ጥበባዊ ዝግጅቶች እና አዳዲስ ጥበባዊ ስራዎች ለጥበብ አፍቃሪያን ሲደርሱ ቆይተዋል፡፡ ዛሬን ጨምሮ በሚቀጥሉት ቀናትም የተለያዩ ጥበባዊ መሰናዶዎች ይደረጋሉ፡፡ ከተሰናዱ ዋና ዋና ኪነ ጥበባዊ ዝግጅቶች መካከል የመጻሕፍት ህትመትና ምረቃ፣ የሥዕል አውደ ርዕይ፣ የቴአትር መርሃ ግብር እና ሌሎች መሰናዶዎች ይገኙበታል፡፡ ለመረጃ ይሆንዎት ዘንድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል እንደሚከተለው አዘጋጅቷቸዋል፡፡




ፎቶ- ከገፀ ድር

በከተማችን ከተዘጋጁ ኪነ ጥበባዊ መሰናዶዎች በከፊል

## መጽሐፍት

በ'የጦር ሜዳ ውሎ' መጽሐፍ ላይ ውይይት ይደረጋል፡፡ ዛሬ ቅዳሜ ከ8፡00 ሰዓት ጀምሮ 'የጦር ሜዳ ውሎ' በተሰኘው የብርጋዴር ጄነራል ተስፋዬ ሀብተማርያም መጽሐፍ ላይ ውይይት ይደረጋል፡፡ የመጽሐፉ ደራሲ ብርጋዴር ጄነራል ተስፋዬ ሀብተማርያም የቀድሞ የኢትዮጵያ ሰራዊት የአየር ሃይል አዛዥ የነበሩ ሲሆን፣ በተለይ የሀገርን ዳር ድንበርና ሉዓላዊነት ለማስከበር በተደረጉ ተጋድሎዎች ታላላቅ ጀብዱዎችን በመፈጸም ይታወቃሉ፡፡ መጽሐፉ ኢትዮጵያ የቀይ ባህር ዳር ድንበሯን እንዳታጣ በናቅፋና በሌሎችም የጦር ሜዳዎች የተደረጉ አስደናቂ ተጋድሎዎችን ያስቃኛል፡፡ የመጽሐፉ ውይይት ያሰናዳው ዛጎል የመጻሕፍት ባንክ ሲሆን፣ አዘጋጅና አቅራቢ ደራሲ እንዳለጌታ ከበደ ነው፡፡ ዝግጅቱ ቀበና በሚገኘው ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ (FSS) አዳራሽ ውስጥ ይከናወናል ተብሏል።

'አዲስ፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ መዝገበ ቃላት' ለንባብ በቃ፡፡ የኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚ ከኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የሳይንስና ቴክኖሎጂ የጽንሰ ሐሳብ አቻ ስያሜዎችን ከብያኔዎቻቸው ጋር የያዘ አዲስ የሳይንስና ቴክኖሎጂ መዝገበ ቃላት መጽሐፍ ባሳለፍነው ሳምንት በይፋ ተመርቆ ለገበያ ውሏል፡፡ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዕውቀት ህዝባዊ ለማድረግ ቁልፍ ሚና እንደሚጫወት የተነገረለት ይሄ የመዝገበ ቃላት መጽሐፍ የሀገሪቱ ታላላቅ ምሁራን ተሳትፈውበታል፡፡

ከመዝገበ ቃላት መጽሐፉ አርታያን መካከል አንዱ የሆነው ደራሲና ሃያሲ ቴዎድሮስ አጥላው በማህበራዊ የትስስር ገጹ ስለመጽሐፉ እንዲህ ብሏል፤ "በመጀመሪያ ዕትሙ ከ30 በላይ ከሚሆኑ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፎች የተመረጡ 11 ሺህ 600 ሙያዊ ሥያሜዎች በአቻ የአማርኛ ሥያሜዎች የተፈቱበት እና የተበየኑበት ግዙፍ መዝገበ ቃላት ነው። ይሄ ከ140 በላይ ምሁራንን ያሳተፈው መዝገበ ቃላት የሞባይል መተግበርያም እየተዘጋጀለት ነው። ይህ ደግሞ መዝገበ ቃላቱን በእያንዳንዱ ሰው ቤት ማዳረስ ከማስቻሉ በላይ፤ ሥራውን የማይቋረጥ፣ የሚያድግ፣ የሚሻሻል ያደርገዋል፡፡ እኔም በአርትዖት እና በአሳታሚነት ያቅሜን የማበረክትበት ዕድል በማግኘቴ ትልቅ ደስታ ተሰምቶኛል። ምናልባት እስከዛሬ ከተሳተፍኩባቸው የመጽሐፍ ፕሮጀክቶች ግዙፉ ይሄ ሳይኾን አይቀርም" በማለት ትልቅ ሀገራዊ ፋይዳ ያለው መጽሐፍ ለንባብ መብቃቱን በገጹ አስፍሯል። የመጻሕፍት ወዳጆችም መጽሐፉ በኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚና በሌሎች የመጻሕፍት መሸጫ መደብሮች ውስጥ ማግኘት ትችላላችሁ ተብሏል፡፡

በተጨማሪም የታዋቂዋ የወግ ጸሃፊ የህይወት እምሻው አዲሱ መጽሐፍ ዛሬ ለንባብ ይበቃል፡፡ 'ዥዋዡዌ' የተሰኘው የአጫጭር ልብ ወለዶች ስብስብ መጽሐፍ ዛሬ በአዲሱ የጃፋር መጻሕፍት መደብር ውስጥ በይፋ ለንባብ እንደሚበቃ ደራሲዋ በማህበራዊ የትስስር ገጿ አስፍራለች። የደራሲዋ አድናቂዎችና የሥነ ጽሑፍ አፍቃሪያን ዛሬ ቅዳሜ 10፡00 ሰዓት ጀምሮ ለገሃር የሚገኘው የጃፋር መጻሕፍት መደብር ተገኝተው ከደራሲዋ ጋር እየተጨዋወቱ ፊርማዋን ያረፈበት መጽሐፍ ማግኘት ትችላላችሁ ተብሏል፡፡

## ሥዕል

'አብሮነት' የሥዕል አውደ ርዕይ በመታየት ላይ ነው፡፡ ባሳለፍነው ሳምንት ረዕቡ ህዳር በፈንዲቃ የባህል ማዕከል ውስጥ በይፋ የተከፈተው አብሮነት የሥዕል አውደ ርዕይ የተለያዩ የሥዕል ሥራዎች የቀረቡበት ነው ተብሏል፡፡ ሰዓሊያን በቡድን ሆነው ባሰናዱት በዚህ የሥዕል አውደ ርዕይ አብሮነትና ህብረትን የሚያሳዩ የሥዕል ስራዎች ቀርበዋል፡፡ በአውደ ርዕዩ ላይ የሥዕል ሥራዎቻቸውን ካቀረቡ ሰዓሊያን መካከል ብሩ ወርቁ፣ ያሬድ ወንድወሰንና ዘውዱ ገብረሚካኤል ይገኙበታል፡፡ የስዕል አውደ ርዕዩ እስከ መጪው ህዳር 29 ቀን 2018 ዓ.ም ድረስ ለተመልካች ክፍት ሆኖ ይቆያል፡፡ የስዕል አውደ ርዕዩ መስቀል አደባባይ አጠገብ በሚገኘው በሃያት ሬጀንሲ ሆቴል ውስጥ ባለው በፈንዲቃ የባህል ማዕከል ውስጥ እየታየ ይገኛል፡፡

## የቴአትር መርሃግብር

በመዲናችን አዲስ አበባ ቅዳሜ እና እሁድ የተለያዩ ቴአትሮች ይታያሉ፡፡ 12ቱ እንግዶች የተሰኘው ቴአትር ቅዳሜ 8:30 ሰዓት በብሔራዊ ቴአትር ቤት ይታያል። 11፡30 ሰዓት ደግሞ ባሎችና ሚስቶች የተሰኘው ቴአትር በዚያው በብሔራዊ ቴአትር ይታያል፡፡ እሁድ በ8፡30 ሰዓት ደግሞ ንጉሥ አርማህ ቴአትር፣ እንዲሁም እምዬ ብረቷ የተሰኘው ቴአትር ደግሞ በዚሁ በብሔራዊ ቴአትር 11፡30 ሰዓት ላይ ይታያል፡፡

በሀገር ፍቅር ቴአትር ቤት ደግሞ እሁድ በ8:00 ሰዓት በዓሉ ግርማ ቤርሙዳ የተሰኘው ቴአትር ይታያል፡፡ በተጨማሪም በቀጣይ ቀናት በብሔራዊ ቴአትር የሚታዩት ማክሰኞ በ11፡30 ሰዓት ሦስቱ አይጦች፣ ረዕቡ በ11፡30 ሰዓት የቅርብ ሩቅ ቴአትር፣ ሐሙስ ቀን 11:30 ሸምጋይ ቴአትር፣ አርብ በ11፡30 ሰዓት የሕይወት ታሪክ በብሔራዊ ቴአትር ለጥበብ አፍቃሪያን ለዕይታ ይቀርባሉ፡፡

# የቁጥር ጨዋታ

## የባለፈው ሳምንት ጥያቄ መልስ

ውድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ አንባቢዎቻችን ባለፈው ሳምንት የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችሁ ነበር። የጥያቄው ትክክለኛ አሰራርና መልስ ለማግኘት በክቡ በግራ በኩል ያሉ ሶስቱ ቁጥሮች እንደምራለን። እንዲሁም በቀኝ በኩል ያሉ ሁለቱ ቁጥሮች እንደምራለን፡፡ ሶስቱ ቁጥሮች ደምረን ያገኘነው ድምር ውጤት ላይ በስተቀኝ በኩል ሁለቱ ቁጥሮች ደምረን ያገኘነው ቁጥር እንቀንሳለን። ቀንሰን የምናገኘው ቁጥር የመሃሉ ቁጥር መምጣት ይኖርበታል። ለአብነትም የመጀመሪያው ክብ አብረን እንስራው፤ 7 + 2 + 4 = 13 ከዚያ በኋላ 6 + 5 = 11 ይሆናል፤ 13 – 11= 2 ይሆናል፡፡ በዚህ መሰረት የጥያቄው አሰራርና መልስ እንደሚከተለው ይሆናል፤ 11 + 4 + 2 = 17 ከዚያ በኋላ፤ 5 + 2 = 7 ይሆናል፡፡ 17 – 7 = 10 ይሆናል፡፡ የጥያቄው ትክክለኛ መልስ 10 ይሆናል፡፡ል፡፡




## የዚህ ሳምንት የቁጥር ጨዋታ

ውድ አንባቢዎቻችን ከታች በምስሉ ላይ የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችኋል፡፡ በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ መግባት ያለበት ትክክለኛው ቁጥር ስንት ነው? በጥያቄው ራስዎን እየፈተኑ ይዝናኑ፡፡ የጥያቄውን መልስ በቀጣይ ሳምንት እትማችን ይዘን እንቀርባለን፡፡



# አብሮነት በስዕል ሲገለጥ

በጊዜው አማረ

ኪነ ጥበብ የአንድን ማህበረሰብ ሁለንተናዊ ጉዳዮች በማጉላት እና ሰዎች እንዲያስቡ፣ ያሰቡትን እንዲተገብሩ እና እንዲለወጡ በማነሳሳት ትልቅ ሚና ይጫወታል። የህይወት ልምዶችን በማንፀባረቅ በህብረተሰብ ላይ አዎንታዊ ተጽዕኖ ይፈጥራል። በአጭሩ በሰውነት እንቅስቃሴ፣ በቁስ፣ በስዕል፣ በድምጽ፣ በጽሑፍ፣ በአለባበስና አመጋገብ፣ በብልሀት ተቀናብሮ የሚቀርብ የሚታይ፣ የሚደመጥ፣ የሚዳሰስ ውበት ነው። ጀሚል ከድር የተባለ ጸሐፊ "ኪነ ጥበብ እና ፍሬዎቹ" በሚል ርዕስ ባሰፈረው ጽሑፍ ላይ እንዳተተው ኪነ ጥበብ ማህበረሰቡን ስለማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ባህላዊ እና ሌሎች ጉዳዮች በማስተማር የበኩሉን አስተዋፅዖ ያበረክታል፡፡ እንዲሁም ሰዎች ለሀገራዊ ጉዳዮች መፍትሔ እንዲሰጡ እና በህብረተሰቡ ውስጥ አዎንታዊ ለውጦች እንዲያድጉ ያነሳሳል። በማህበረሰብ ውስጥ አንድነትና አብሮነትን ከሚሸምኑ፣ ያለ ቃላት በአዕምሮ ውስጥ የሚቀር ትምህርትን ከሚቀርጹ የኪነ ጥበብ ስራዎች ውስጥ አንዱ ስዕል ነው፡፡ የአዲስ ልሳን ዝግጅት ክፍልም በነገው ዕለት የሚከበረውን ዓለም አቀፍ "የአብሮነትና መቻቻል ቀን" መነሻ በማድረግ ስዕል ለአብሮነት፣ አንድነትና የጋራ ትርክት ያለውን ሚና በተመለከተ በአጭሩ ዳሰሳ አድርጓል፡፡

ኪነ ጥበብ፣ በተለይም ስዕል፣ የሰው ልጅ ታሪክ፣ ስሜትና ተስፋ መገለጫ እንደመሆኑ መጠን፣ ከግለሰባዊ ውበት ፍለጋ የላቀ አቅም አለው። ምክንያቱም ስዕል ቋንቋ ሳይገድበው፣ ኃይማኖት ሳይለየው እና ፖለቲካ ሳይከፋፍለው የሰዎች ልብና አዕምሮ ጋር በቀላሉ የመድረስ ልዩ ኃይል አለው። በተጨማሪም በቀለም የተሳለ ምስል የጋራ ታሪክን፣ የጋራ ማንነትን እና የጋራ ርዕይን የማንጸባረቅ፣ የመቅረጽና የማጠናከር ታላቅ አቅም በውስጡ ይዟል።

ስዕል የተለያዩ ባህሎችና ማንነቶች ያሉትን ማህበረሰብ አንድ ላይ አምጥቶ፣ በልዩነት ውስጥ ያለውን ውበት እንዲያይና እንዲያከብር ያግዛል። አብሮነትና መተሳሰብን ያጎላል፡፡ በተጨማሪም ስዕል ያለፉትን የጋራ ድሎች፣ መስዋዕትነቶችና እሴቶች በምስል በማስቀመጥ ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል የሚያካትት ጠንካራና ዘላቂ የሀገር ትርክት እንዲገነባ ያግዛል። እንዲሁም የማህበረሰቡን ሀገራዊ ስሜት፣ አብሮነት፣ አዕምሯዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት ይደግፋል።

ስዕል "የጋራ ትውስታን የመጠበቅና የማስተላለፍ የረጅም ጊዜ ታሪክ አለው" የሚባለውም ለዚሁ ነው። በኢትዮጵያ የጥንት ስዕሎች ላይ የሀገር ታሪክ፣ የእምነትና የባህል ዘይቤዎች ተቀላቅለው ይገኛሉ። ይህ የሚያሳየው ስዕል ዘመን ተሻጋሪ የሆነ የማህበረሰብ ምሰሶ መሆኑን ነው።

"ስዕል በቀለምና ብሩሽ ብቻ ያለቋንቋ ትልቅ የአብሮነትና የአንድነት መልዕክት ማስተላለፍ ይችላል፡፡ የማህበረሰብ ነጸብራቅ ነው" የሚለው በአዲስ አበባ



ፎቶ ከገፀ ድር
በደቡብ አፍሪካ አብሮነትን ለማስተማር የተሰራ ስዕል


ፎቶ ከገፀ ድር
ኢትዮጵያዊ አብሮነትን ከሚያሳዩ ስራዎች መካከል

የኮሪደር ልማት ፕሮጀክቶች፣ መንገዶችና ህንጻዎች ላይ የተለያዩ የስዕል ስራዎችን በመስራት የሚታወቀውና በአሁኑ ጊዜም በመስራት ላይ የሚገኘው ሰዓሊ ቢኒያም አበበ፣ አንድ ስዕል ከብዙ ገጽ መጽሐፍ በላይ የሕዝቦችን በአብሮነት የተሞላ ህይወት ይገልጣል። ሰዎችን ስለአንድነትና አብሮነት ያስገነዝባል፡፡

ይህን የተገነዘቡ ሀገራት በስዕል አንድነትን ሰብከዋል፡፡ አብሮነትን አስተምረዋል። ማህበረሰብን ለልማት አነሳስተዋል፡፡ ልማትን አፋጥነዋል፡፡ ሀገራዊ ትርክትም እየገነቡበት ይገኛሉ፡፡

ሌሎች ሀገራት ስዕልን ለጋራ ትርክትና ለአብሮነት ግንባታ በስፋት ተጠቅመውበታል። ዲቦራ ገስትሊን የተባሉ የዘርፉ ባለሙያ "Mexican Murals and Social Art" በሚል እ.ኤ.አ በ2024 ለንባብ ባበቁት ጽሑፍ ላይ እንደገለጹት፣ ሜክሲኮ በ20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ ከረጅም የእርስ በርስ ግጭት በኋላ ብሔራዊ ማንነቷን እንደገና ለመገንባት የስዕል ጥበብን በስፋት ተጠቅማለች፡፡

እንደ ዲያጎ ሪቬራ ያሉ ታላላቅ ሰዓሊዎች በትምህርት ቤቶች፣ በመንግስት ህንፃዎች እና በህዝባዊ ቦታዎች ላይ ግዙፍ ስዕሎችን ሰርተዋል። እነዚህ ስዕሎች አብሮነትንና አንድነትን የሚያሳዩ የጋራ ትርክትን የሚገነቡና ለብሔራዊ ጥቅም በጋራ መቆምንም የሚያስተምሩ ነበሩ። ስዕሎቹ የሜክሲኮን ጥንታዊ ታሪክ፣ የአብዮቱን ሂደት፣ የገበሬዎችን ሕይወት እና የሀገሪቱን ብዝሃነት ያሳዩ ነበር። ይህም የብሔራዊ ኩራትና የመግባባት ስሜት ተጠናክሮ የጋራ ሀገራዊ ትርክት እንዲገነባ አድርጓል።

ለአብሮነትና አንድነት፣ ለጋራ ትርክትና ለብሔራዊ ጥቅም በጋራ መቆምን በስዕል አማካኝነት ግንዛቤ ፈጥሮ ውጤታማ ከሆኑ ሀገራት መካከል ደቡብ አፍሪካና ጀርመን ዋነኛ ተጠቃሾች ናቸው፡፡

ከላይ የተጠቀሱት ዓለም አቀፍ ልምዶችና ተሞክሮዎች ለሀገራችን ትልቅ ትምህርት ሰጪ ናቸው። ኢትዮጵያ በታሪክ የበለጸገች፣ በባህል የረቀቀችና በሥነ- ስዕል ጥበብ ጥንታዊና ዘመናዊ ቅርሶች ያሏት ሀገር ነች። ይህንን ውድ ሀብት ለጋራ የሀገር ትርክትና አብሮነት ለመጠቀም ከላይ በተጠቀሱት ሀገራት ልምዶች በመነሳት ተጠቃሚ መሆን ትችላለች፡፡ የሰዓሊ ቢኒያም አስተያየትም ይህን የሚያጠናክር ነው፡፡

እንደ ሰዓሊ ቢኒያም ገለጻ፣ በደቡብ አፍሪካ፣ ብራዚልና ሜክሲኮ "Mural Art" የተባለው የአሳሳል ዘዴ ለአንድነት፣ ለአብሮነትና ለጋራ ትርክት ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ኢትዮጵያም የብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ሀገር እንደመሆኗ የተለያዩ ጸጋዎችን በስዕል በማንጸባረቅ አብሮነትን ማጠናከር ይቻላል፡፡ ይህም ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ፣ በውበት የታጀበና እያዝናና የሚያስተምር ብሎም ኢትዮጵያዊ አንድነትን የሚያጠናክር ይሆናል፡፡

ከአርታዊ ጋለሪ መስራቾች ከሆኑት አንዱ የሆነው አብነት ተሾመ ከዚህ ቀደም ለአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል በሰጠው አስተያየት፣ "ወደ ጀርመን ባቀናሁበት ወቅት በአንድ ትንሽ ከተማ በርካታ የስዕልና የፎቶግራፍ ማሳያ ማዕከላት መኖራቸውን አይቻለሁ፡፡ ጀርመኖች ስዕልን ለስራ ፈጠራ፣ ለገጽታ ግንባታ፣ ለአብሮነትና ለባህል እድገት፣ ስልጣኔን እና የውጭ ምንዛሬን ለማግኘት ተጠቅመውበታል፡፡ እኛም ከእነሱ ብዙ የምንማረው ነገር አለ" በማለት ልምዱን አጋርቶን ነበር፡፡

የኢትዮጵያን የብዝሃነት ውበት፣ የጋራ ድሎች (እንደ የዓድዋ ድል እና ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ)፣ የሁሉም ክልል ህዝቦች የጋራ ታሪካዊና ባህላዊ እሴቶችን የሚያንጸባርቁ ግዙፍ የሕዝብ ስዕሎችን በየክልሉ ዋና ከተሞች፣ አደባባዮችና በትላልቅ የመንግስት ህንፃዎች ላይ እንዲሰሩ በማድረግ አብሮነትን ማጉላትና የጋራ ትርክትን መገንባት ይቻላል።

ስዕልን በቀላሉ ከመሳል አልፎ የሀሳብ መግለጫና የትንታኔ መሳሪያ እንዲሆን በማድረግ የትምህርት ቤቶች ሥርዓተ-ትምህርት ውስጥ ማካተት አስፈላጊ መሆኑ ይነሳል። ይህም አስተሳሰብን የማስፋትና የፈጠራን አቅም የማጎልበት ፋይዳ አለው። የስነ-ስዕል ተማሪዎች የሀገሪቱን ባህላዊ፣ ኃይማኖታዊና ዘመናዊ የስዕል ዘይቤዎች ጠልቀው እንዲያውቁ እና በዘመናዊ ስራዎቻቸው ውስጥ አብሮነትን፣ የጋራ ታሪክና ትርክትን እንዲጠቀሙ ማበረታታት የሚለውም ዋነኛው ጉዳይ ነው፡፡

በተጨማሪም የግልና የመንግስት ጋለሪዎችን ቁጥርና ጥራት በማሳደግ ሰዓሊዎች አብሮነትን የተመለከቱ ስራዎቻቸውን ለብዙሃኑ እንዲያቀርቡ ዕድል መፍጠር እና በቱሪዝም ዘርፍ ውስጥ የኪነ-ጥበብ ስራዎችን ግብይት በማበረታታት ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታውን ማሳደግ ሀገሪቱ ከዘርፉ ተጠቃሚ እንድትሆን ያስችላታል፡፡

"በተለይ አዲስ አበባ የአፍሪካ መዲና እንደመሆኗ ብዙ ባህል እና ቋንቋዎች የሚገኙባት ከተማ ነች፡፡ ከተማዋ በስዕል ትዕይንት አብሮነትን ማጉላት አለባት። የአንድነት መልክንም ልታንጸባርቅ ይገባል፡፡ የስዕል ጥበብ ከተማዋን የሰላም፣ የመቻቻል፣ የአብሮነትና የአንድነት መገለጫ ሊያደርጋት ይገባል" ሲል ሰዓሊ ቢኒያም ያብራራል፡፡

ቢኒያም እንደሚለው፣ ሰዓሊዎች ታሪካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊና ማኅበራዊ ፋይዳን የሚያንፀባርቁ ስዕሎችን መስራት አለባቸው። ለምሳሌ፡- የዓድዋ ሙዚየምን ጨምሮ የዓድዋን ጦርነት መንፈስ፣ ጀግንነትና አንድነት የሚያሳዩ ስራዎች ሊሠሩ ይችላሉ። እንደዚህ አይነት ስራዎች የጋራ አብሮነትን ከፍ በማድረግ ረገድ የማይተካ ሚና አላቸው፡፡

በአጠቃላይ ስዕል ከውበት ያለፈ፣ የሀገርን ሕልውና፣ አብሮነትና የጋራ ዕድገት የሚደግፍ ስልታዊ መሳሪያ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝቦች የጋራ ትርክት በብዝሃነታቸው ውበትና በመቻቻላቸው ታሪክ ላይ የተመሰረተ ነው። ሥነ-ስዕል ይህንን ታሪክና ብዝሃነት በምስል በማቅረብ፣ በአድማስና ቀለማት ልዩነት ስር ያለውን አንድ የጋራ መልክ ለማየት ያስችላል።

ኢትዮጵያም ከሜክሲኮ፣ ደቡብ አፍሪካ እና ጀርመን ልምድ በመማር፣ ጥበብን ከመንግሥት እስከ ኅብረተሰብ ባሉ ተቋማት ውስጥ ስልታዊ በሆነ መንገድ መተግበር አለባት። የጋራ አብሮነትን የሚተርኩ የስዕል ፕሮጀክቶች መጀመር፣ የኪነ ጥበብ ትምህርትን ማጠናከር እና ለባለሙያዎች ምቹ ሁኔታ መፍጠር የዛሬ ተግባራት መሆን አለባቸው።

የኢትዮጵያ ነገ የሚገነባው የጋራ ታሪኳንና ተስፋዋን በሚያንጸባርቅ አንድ የጋራ ትርክትና አብሮነት ላይ ነው። ይህ ትርክት ደግሞ በብሩሽና በቀለም ተመስሎ፣ በአደባባይ ተሰቅሎ፣ ለሁሉም ኢትዮጵያዊ ልብና አይን እንዲደርስ በማድረግ ማጠናከር ይቻላል። በስዕል የሚገለጽ አብሮነት ለጠንካራ፣ ለሰላማዊና ለበለጸገች ኢትዮጵያ መሠረት መሆን ይችላል፡፡

ምክንያቱም ስዕሎች የሀገርን አንድነት፣ የቴክኖሎጂ ዕድገት፣ የከተሜነት መስፋፋትና የማህበራዊ ለውጦችን በማንፀባረቅ ስለ ሀገሪቱ የወደፊት አቅጣጫ ፍንጭ ይሰጣሉ። ኢትዮጵያም በስዕል ጥበብ ቀደምት ከሚባሉና ራሳቸውን በአብሮነት ውበት፣ ለዓለም በስዕል መግለጥ ከሚችሉ ሀገራት መካከል ተጠቃሽ ነች፡፡

ኢኮኖሚ

# በመታመን የተገኘ ክብር

- ለታማኝ ግብር ከፋዮች የተዘጋጀ ልዩ የተጠቃሚነት ዕድል መኖሩ ተመላክቷል

**በደረጀ ታደሰ**

አቶ ሰዒድ ሀሰን፤ የሀስ ኢንተርፕራይዝ መስራች እና ሥራ አስኪያጅ ናቸው። ድርጅታቸው የተመሰረተው ከ20 ዓመት በፊት ሲሆን፤ ሥራውን የጀመረው ብረታብረት በማስመጣት እና በማከፋፈል ነበር፡፡ አሁን ላይ በሀገር ውስጥ የሚመረቱ እና ከውጭ ሀገር የሚገቡ የብረት ምርቶችን (ቱቦላሬ፣ ሺት ሜታሎች፣ ላሜራዎች...) በማስመጣት በግንባታ ሥራ ላይ ለተሰማሩ ድርጅቶችና ግለሰቦች ያከፋፍላል፡፡ ተደራሽነቱም ሙሉ የኢትዮጵያ ክፍል ነው።

ሀስ ኢንተርፕራይዝ ባሳለፋቸው ሁለት አስርት ዓመታት ዕድሜ ውስጥ ውጤታማነቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ መምጣቱን ያስታወሱት አቶ ሰዒድ፤ "አሁን ላይ በዋናው የሀስ ኢንተርፕራይዝ ስር የተለያዩ እህት ድርጅቶችን አቋቁመን ወደ ሥራ ገብተናል፡፡ በሲዳማ ክልል በ፣ ሺህ 200 ሄክታር መሬት በመስኖ እርሻ ልማት ተሰማርተናል፡፡ ዓለም ገና ላይ የብረታብረት ኢንጂነሪንግ ድርጅት አለን። ለትንባሆ ሞኖፖል ድርጅት ግብዓት የሚያቀርብ የትንባሆ ማቀነባበሪያ (የቶባኮ ፕሮሰሲንግ) ፋብሪካ አለን። ከዚህ በተጨማሪም በቤቶች ግንባታ ላይ የተሰማራ የሪልስቴት ድርጅትም ወደ ሥራ አስገብተናል" በማለት ያብራራሉ፡፡ የሀስ ኢንተርፕራይዝ እና እህት ድርጅቶቹ ከ300 በላይ ቋሚ እንዲሁም ከ600 በላይ ጊዜያዊ የሥራ ዕድል ለዜጎች መፍጠር መቻሉንም ገልፀዋል፡፡

በሥራ የሚያምኑት፣ ሠርቶ መለወጥን በተግባር ያረጋገጡት፣ ከራሳቸው አልፎ ለትውልድ እና ለሀገር የሚጠቅሙ ድርጅቶችን በማቋቋምና ለውጤት በማብቃት ምሳሌ የሆኑት የሀስ ኢንተርፕራይዝ መስራች እና ሥራ አስኪያጅ፤ ግብርን በታማኝነትና በወቅቱ በመክፈልም የተመሰከረላቸው ናቸው። ጥቅምት 7 ቀን 2018 ዓ.ም. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ "ግብር ለሀገር ክብር!" በሚል መሪ ሐሳብ ባሰናዳው የታማኝ ግብር ከፋዮች የዕውቅና ሽልማት መርሃ ግብር ላይ የፕላቲኒየም ደረጃ ተሸላሚ ከሆኑት መካከል የሀስ ኢንተርፕራይዝ አንዱ መሆኑ ለዚህ ምስክር ነው፡፡

"የንግድ ፍቃዳችንም፣ ግብር የምንከፍለውም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር ነው፡፡ ይህንን ዕውቅናና ሽልማት ስናገኝ ይህ የመጀመሪያችን አይደለም፡፡ አምናም በተመሳሳይ የፕላቲኒየም ደረጃ ተሸላሚ ነበርን" የሚሉት አቶ ሰዒድ ለሽልማት ያበቃቸውን ልምድ እና አሠራር እንደሚከተለው አብራርተዋል፤ "ለሽልማት ያበቃን የከፈልነው የግብር መጠን፣ በደረሰኝ ሽያጭ ወይም ግብይት ማድረግ ዋናው መመዘኛ ነው፡፡ እኛ ምንም ዓይነት ግብይት ያለደረሰኝ አናከናውንም፡፡ ሽያጭን በደረሰኝ ማከናወን የድርጅታችን ባህል ነው፡፡ ይህም የገቢዎች ተቋም የክትትል ሠራተኞች ወደ ድርጅታችን መጥተው በሚያደርጉት ክትትልና ቁጥጥር ለማረጋገጥ የቻሉት ሀቅ ነው፡፡ 'የእኛ የእኛ፤ የመንግስት የመንግስት ነው። የሚል መርህ በድርጅታችን በወጥነት ይተገበራል፡፡ ማንኛውም ሠራተኛ ወደ ድርጅቱ ሲቀጠር ቀድሞ ስለ ድርጅቱ የሥራ ባህል በቂ ግንዛቤ ይፈጠርለታል። መብትና ኃላፊነቱን እንዲያውቅ ይደረጋል። በመዘናጋትም ይሁን ሆን ተብሎ ያለ ደረሰኝ የሚፈፀም ግብይት ካለ፤ ለሚፈጠረው ችግር ኃላፊነት የሚወስደው በወቅቱ ለችግሩ መፈጠር ምክንያት የሆነው ሠራተኛ ነው፡፡"

ከአንድ ወር በፊት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደረጃ በተሰናዳው እና በአዲስ ዓለም አቀፍ ኮንቬንሽን ማዕከል በተከናወነው የታማኝ ግብር ከፋዮች የዕውቅና ሽልማት መርሃ ግብር ላይ የሀስ ኢንተርፕራይዝን ጨምሮ 387 ግብር ከፋዮች ዕውቅናና ሽልማት ተሰጥቷቸዋል።

በአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ የህግ ተገዥነት ጥናትና ስትራቴጂ ዝግጅት ቡድን አስተባባሪ አቶ ወንድወሠን ጥላሁን በበኩላቸው ግብር ሲከፈል ሀገር ታድጋለች፤ ግብር ከፋዮች ደግሞ ግዴታቸውን በመወጣታቸው መብታቸውን የመጠየቅ ሞራል እንደሚኖራቸው ተናግረዋል፡፡

የሀስ ኢንተርፕራይዝ መስራችና ሥራ አስኪያጅ አቶ ሰዒድ የራሳቸውን ልምድ በማከል ሀሳቡን ያጠናክራሉ። ይህንንም፤ "ድርጅታችን በዓመት እስከ 200 ሚሊዮን ብር የሚደርስ የግብር ገቢ ለመንግሥት ይከፍላል፡፡ በወቅቱ ነው የምንከፍለው። ይህንን ገንዘብ ስንከፍል የተለየ ነገር እንዳደረግን አንቆጥረውም፡፡ ምክንያቱም አንድ ግብር ከፋይ ግብር የሚከፍለው ካተረፈው ውስጥ የራሱን ድርሻ በማስቀረት እና ለመንግስት ተብሎ የተቀመጠውን ድርሻ ብቻ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ተሰብስቦ ዜጎች በጋራ ሊጠቀሙባቸው ለሚችሉ የልማት ሥራዎች የሚውል ነው" በማለት ገልጸውታል፡፡ ድርጅታቸው ግብር ከመክፈል ባለፈ፤ በከተማ አስተዳደሩ በተካሄዱ የልማት እና የበጎ አድራጎት ሥራዎች ላይ ንቁ ተሳታፊ ነው፡፡ ለአብነት በ2017 በጀት ዓመት ብቻ ከ30 እስከ 40 ሚሊዮን ብር የሚገመት የገንዘብ እና መሰል ድጋፍ ማድረጉ፣ ለዚህ ተግባሩም ዕውቅናና ሽልማት መሰጠቱን ተናግረዋል።

የዩናብ ቢዝነስ ድርጅት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር በፕላቲኒየም ደረጃ ዕውቅናና ሽልማት ከተሰጣቸው ድርጅቶች መካከል ይጠቀሳል፡፡ የዩናብ ቢዝነስ ጥቅምት 7 ቀን 2018 ዓ.ም. የፕላቲኒየም ደረጃ ሽልማትን ለ4ኛ ጊዜ እንዳገኘ የድርጅቱ ዳይሬክተር ዮናታን ዐቢይ፤ በታማኝነት የሚከፍሉት ግብር ልማት ላይ እየዋለ መሆኑን በአዲስ አበባ በተሰሩ የልማት ሥራዎች ማረጋገጣቸውን እና በዚህም ትልቅ ኩራት እንደሚሰማቸው ተናግረዋል።

"የግብር ከፋዮችን የህግ ተገዥነት ደረጃቸውን በመለካት የተሻለ የህግ ተገዢነት ደረጃ ያላቸውን እውቅና መስጠት እና ማበረታታት በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ የመምታትን ያክል ድርብ ዓላማዎችን የሚያሳካ መሆኑን የጠቀሱት በአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ የህግ ተገዥነት ጥናትና ስትራቴጂ ዝግጅት ቡድን አስተባባሪ አቶ ወንድወሠን፤ ይህም ለህግ ተገዥ ያልሆኑ ግብር ከፋዮች ላይ ተጽዕኖ በመፍጠር የህግ ተገዢነትን ለማሳደግ የሚደረገውን ጥረት ለውጤት ለማብቃት አቅም ይፈጥራል፡፡ እንደ ከተማ አስተዳደር የታዩ ስኬቶችን ዘርዝረዋል፡፡ የግብር ከፋዮች የታክስ ግዴታን በራስ ተነሳሽነት የመወጣት አቅም ማደጉን፣ በየጊዜው የሚጠበቀውን ገቢ መሰብሰቡን፣ የተቀላጠፈ አገልግሎት መሰጠቱን፣ ለህግ ማስከበር እና የግብር ገቢን ለመሰብሰብ የሚወጡ ወጪዎችን መቀነሱን፣ የግብር አሰባሰብ ሥርዓቱን ለማዘመን የሚያስችሉ አቅሞችን መፍጠሩን፣ በግብር ከፋዩ እና በግብር ሰብሳቢው መካከል ጤናማ የሆነ ግንኙነት እንዲኖር ማድረጉን እንዲሁም በህዝብ በኩል የተቋሙ ተዓማኒነት እንዲጨምር ማድረጉን ጠቅሰዋል፡፡

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ያለማቋረጥ እየተተገበረ ያለው የታማኝ ግብር ከፋዮች የዕውቅናና ሽልማት መርሃ ግብር ለታማኝ ግብር ከፋዮች በርካታ ጠቀሜታዎችን እንደሚሰጥ ተሸላሚዎቹ ይናገራሉ። ከዚህ ጋር በተያያዘ ለጋዜጣችን ሐሳብ እና አስተያየታቸውን የሰጡት የሀስ ኢንተርፕራይዝ ባለቤትና ሥራ አስኪያጅ አቶ ሰዒድ፤ "ለታማኝ ግብር ከፋዮች ዕውቅናና ሽልማት መሰጠቱ፤ የድርጅት ባለቤቶች 'ለካ መንግስት መልካም ተግባራችንን ይመለከታል' እንዲሉ ያደርጋል፡፡ ለተሻለ ሥራ ያነቃቃል። ለታማኝነት፣ ለመልካም ሥምና ዝና መጠበቅ ትልቅ ትኩረት እንዲሰጥ ያግዛል። ከዚህ በተጨማሪም፤ ለታማኝ ግብር ከፋዮች የቪአይፒ አገልግሎት ማግኛ ዕድልን ያስገኛል፡፡ እኔም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለሚገኘው አገልግሎት ቅድሚያ እንዲሰጠኝ የሚያስችል የቪአይፒ መጠቀሚያ ካርድ ተሰጥቶኛል፡፡ በዚህም በገቢዎች ቢሮ የሚሰጠውን አገልግሎት በቅድሚያ እና በፍጥነት ማግኘት ችያለሁ። ጅምሩ ሊበረታታ የሚገባው ነው፡፡" ብለዋል፡፡

ለታማኝ ግብር ከፋዮች እንደከተማ አስተዳደር የተዘጋጀ ልዩ የተጠቃሚነት ዕድል መኖሩን ያነሱት በገቢዎች ቢሮ የህግ ተገዥነት ጥናትና ስትራቴጂ ዝግጅት ቡድን አስተባባሪው፤ ለተሸላሚዎች በዕለቱ ከሚሰጠው ዕውቅና በተጨማሪ በቢሮው የተዘጋጀ የአገልግሎት ቅድሚያ ማግኛ መታወቂያ እና ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው ገልፀዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በፕላቲኒየም እና በወርቅ ደረጃ ለተሸለሙ ግብር ከፋዮች በከተማ አስተዳደሩ በማንኛውም አገልግሎት የቪአይፒ አገልግሎት እንዲያገኙ መደረጉንም ጠቅሰዋል፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ በሀገር አቀፍ ደረጃ በተካሄደው የታማኝ ግብር ከፋዮች የዕውቅናና ሽልማት መርሃ-ግብር ላይ የተገኙት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)፤ ለሀገር የታመኑ ግብር ከፋዮችን ለማበረታታት በፕላቲየም ደረጃ ዕውቅና እና ሽልማት ለተበረከተላቸው ድርጅት ባለቤቶች ወይም ሥራ አስፈጻሚዎች ዓለማቀፍ ሥራቸውን ቀላል ያደርግላቸው ዘንድ ዲፕሎማቲክ ፓስፖርት እንደሚሰጣቸው መግለፃቸው ይታወቃል፡፡ ከዚህ ባሻገር፤ ለ245 በወርቅ ደረጃ ተሸላሚዎች ደግሞ በኢትዮጵያ አየር መንገድ የቪአይፒ ተርሚናል መጠቀም እንደሚችሉ አብስረዋል፡፡ በቀጣይም የታማኝ ግብር ከፋዮች ቁጥር ከዘንድሮውም በበለጠ በብዙ አድጎ እንደሚመለከቱ ተስፋቸውን ጠቁመዋል። ለዚህም ስኬት ሁሉም የበኩሉን ኃላፊነት መወጣት እንዳለበት አሳስበዋል፡፡



ፎቶ- ከገፀ ድር

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሽልማትና እውቅና ከተሰጣቸው ታማኝ ግብር ከፋዮች መካከል

# ልጆች፤ ራሳችሁን ከትራፊክ አደጋ ለመጠበቅ የምታደርጉት ጥንቃቄ ምንድን ነው?

**በለይላ መሀመድ**



ፎቶ በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል

ከትፈፊክ አደጋ ራሳቸውን እንዴት እንደሚጠብቁ ልምዳቸውን ያጋሩን

ልጆችዬ፤ ለዛሬ ይዘንላችሁ የቀረብነው ርዕሰ ጉዳይ የትራፊክ አደጋን የተመለከተ ነው፡፡ በትራፊክ አደጋ ሰዎች ህይወታቸውን ያጣሉ፡፡ የአካል ጉዳተኛ ይሆናሉ፡፡ ንብረት ይወድማል። ለእንዲህ አይነቱ አደጋ ከሚያጋልጧቸው ዋነኛ ምክንያቶች መካከል የመንገድ ደህንነት ህጎችንና የትራፊክ ደንቦችን አለመጠበቅ ነው። እናንተ በዚህ ረገድ ያላችሁ ግንዛቤ እንዴት ያለ እንደሆነ ሃሳብ ተለዋወጡ፤ እኛ ልጆችን እና የሚመለከታቸው አካላትን አነጋግረን አስተያየታቸውን እንደሚከተለው አቅርበነዋል፡፡

ሳምራዊት ወንደሰን እባላለሁ። የትራፊክ አደጋ እንዳይደርስብኝ ጥንቃቄ አደርጋለሁ፡፡ መኪናዎች ሲያልፉ ግራና ቀኙን በደንብ አያለሁ። መስቀለኛ መንገዶችን አልጠቀምም። በአቋራጭ መንገድ ለመሄድ ስል ድልድዮችን አልዘልም፡፡ መንገድ ላይ ቀልድና ጨዋታ አላበዛም፡፡ ከጓደኞቼ ጋር ስጓዝም እርስ በርሳችን ወይም ከመንገደኞች ጋር አልገፋፋም፡፡ አስፋልት መንገድ የምሻገረው ነጭ ቀለም በተቀባው (ዜብራ) መንገድ ነው፡፡ ለእግረኛ መፈቀዱን የሚያሳይ የትራፊክ መብራት ምልክትም ጠብቄ ነው የምሻገረው፡፡

ኤልሻዳይ አስናቀ እባላለሁ፡፡ የመኪና አደጋ በጣም ስለምፈራ እንዳይደርስብኝ እጠነቀቃለሁ፡፡ እንድፈራ ያደረገኝ ምክንያት በእንዲህ አይነት አደጋ የሞቱ ሁለት ልጆችን ስለማውቅ ነው። አደጋው ሊደርስባቸው የቻለውም አስፋልት ዳር ላይ ሲጫወቱ ነው፡፡ እኔ ሁልጊዜ ብቻዬንም ሆነ ከሰው ጋር የምሻገረው ለማቋረጥ በተዘጋጀው ነጭ ቀለም በተቀባው መንገድ ነው፡፡ ቀኝና ግራ አቅጣጫን አይቼና መኪና መኖር አለመኖሩን አረጋግጬ ነው የምሻገረው። መኪና ሳይቆም አስፋልት አቋርጬ አላውቅም፡፡

ስሜ አዶኒያስ ታደሰ ይባላል፡፡ ሁልጊዜ ትክክለኛ የመንገድ አጠቃቀም ህጎችን በመከተል ራሴን ከትራፊክ አደጋ እጠብቃለሁ፡፡ በጥንቃቄ ነው አስፋልት መንገድ የማቋርጠው፡፡ የመንገድ ዳር ይዤ ነው የምንቀሳቀሰው፡፡ የትራፊክ መብራቶችን በማየትና ዜብራን በመጠቀም ነው አስፋልት መንገድ የምሻገረው፡፡ የትራፊክ መብራቶችን ጠንቅቄ አውቃለሁ፡፡ ቢጫ ለመኪና ተዘጋጅ ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ቢጫ ሲበራ አስፋልት ለማቋረጥ አልሞክርም። አረንጓዴ ለመኪና ሂድ ስለሆነ አረንጓዴ ሲበራ እቆማለሁ፡፡ ቀይ ለመኪና ቁም እና ለእግረኛ እለፍ ማለት በመሆኑ በዚህን ጊዜ የደረሱ መኪናዎችን መቆማቸውን አረጋግጭ ነው አስፋልት የማቋርጠው፡፡

ቃልኪዳን አማረ እባላለሁ፡፡ በተፈቀዱ የእግረኛ መንገዶች በመጓዝና የዜብራ ማቋረጫዎችን በመጠቀም ነው የምንቀሳቀሰው፡፡ መኪና ሲያልፍ ቅድሚያ በመስጠትና መኪና በሚነዳበት በኩል ባለመሆን ራሴን ከአደጋ እጠብቃለሁ። ከፊትና ከኋላ የሚመጡ መኪናዎችን በደንብ አያለሁ። አስፋልት ሳቋርጥ ዜብራን ብቻ ነው የምጠቀመው። ልጆች የትራፊከ ህጎችን በማክበር ራሳቸውን ከአስከፊ የትራፊክ አደጋ በመከላከል ትልቅ ደረጃ ለመድረስ መሞከር ይኖርባችኋል፡፡

ስሜ ተስፋሁን ታደገ ይባላል። በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራፊክ ማኔጅመንት ባለስልጣን የግንዛቤና አቅም ግንባታ ከፍተኛ ባለሙያ ነኝ። ልጆች እንደ ቦታው ሁኔታ እና አቀማመጥ የምትጠቀሙት መንገድ የሚለያይ ቢሆንም በየትኛውም መንገድ ስትንቀሳቀሱ የትራፊክ አደጋ እንዳይደርስባችሁ የመንገድ ህጎችንና ደንቦችን ማክበር ይኖርባችኋል፡፡

አስፋልት መንገድ በምታቋርጡበት ወቅት ግራና ቀኛችሁን ማየት አለባችሁ። ሁሌም ዜብራን በመጠቀም ነው መንገድ ማቋረጥ ያለባችሁ፡፡ ወደ ትምህርት ቤት ስትሄዱ ወይም ከትምህርት ቤት ስትመለሱ የምትይዙት ቦርሳ እይታችሁን እንዳይከልላችሁ በጥንቃቄ መያዝ ይኖርባችኋል፡፡ እጅ ለእጅ ተያይዛችሁ በምትጓዙበት ጊዜ አንዱ ወደኋላ ሌላው ወደፊት፣ አንዱ በሩጫ ሌላው በቀስታ እየተጓተታችሁ አስፋልት መንገድን ከማቋረጥ መቆጠብ ይኖርባችኋል፡፡ መንገድ ስታቋርጡ ለጸሐይ ወይም ለዝናብ ብላችሁ የያዛችሁትን ጃንጥላ ማጠፍ አለባችሁ፡፡ ምክንያቱም በጃንጥላው ራሳችሁን ከከለላችሁ የመኪናው ርቀት እንዳይታያችሁ ያደርጋል፡፡

ሌላው የጆሮ ማዳመጫ (ኤርፎን) ጆሯችሁ ላይ በማድረግ ሙዚቃ እያዳመጣችሁ አስልፋት መንገድ ማቋረጥ የለባችሁም፡፡ መንገድ እያቋረጡ ሙዚቃ ማዳመጥ፣ ቲክቶክ ማየት፣ ፊልም ማየት፣ የሞባይል ስልክ ማውራት ትኩረት ስለሚያሳጣ ለከፍተኛ አደጋ ይዳርጋል። ስለዚህ ይህንን ባለማድረግ ራሳችሁን ከአደጋ መጠበቅ ይኖርባችኋል። የትራፊክ መብራቶችን አይታችሁ መሻገርን ልምድ ማድረግ አለባችሁ፡፡ ለመኪና ጀርባችሁን ሰጥታችሁ መሻገር የለባችሁም፡፡ ልጆች እነዚህን ጥንቃቄዎች እንደምትፈፅሙ አምናለሁ፡፡

## 10 ልዩነቶችን ፈልጉ



## እንቆቅልሽ

### ያለፈው ሳምንት ጥያቄ

**ስታበላ እንደ እናት ፤ ስትቆጣ እንደ እንጀራ እናት**

**መልስ፡-** ሐ. ንብ

### የዚህ ሳምንት ጥያቄ

**አንድ ጊዜ ተዘርቶ ሁለተኛ የማይዘራ ፤ ታጭዶ ምርት የማይገኝበት ምንድን ነው?**

ሀ. ስንዴ
ለ. ፀጉር
ሐ. አረም

**ልጆች መልስ ይሆናል የምትሉትን በዌብ ሳይታችን አድርሱን፤ እኛም በተደጋጋሚ የመለሰውን እንሸልማለን፤ ስለዚህ ተሳተፉ፤ ተሸለሙ::**

**ከተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየወሩ የሚቀርብ**

# የኮሌጁ የጥበብ አሻራ

- **ለብዙ ዓመታት በዘለቀው የማሰልጠን ልምድ በርካታ የጥበብ ሰዎችን አሰልጥኖ ለውጤት አብቅቷል**

*በሄለን ጥላሁን*

የተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ በእውቀት የታገዙ፤ በብቁ ጠቢባን አሰልጣኞች የጥበብን ሀ ሁ በሚገባ የቀሰሙ፣ በሥራቸው ከሀገር አልፈው በዓለም አቀፍ ደረጃ አንቱታን ያተረፉ ሙያተኞችን አፍርቷል፤ እያፈራም ይገኛል፡፡

በተቋሙ የኤስቴቲክስ ስልጠና ዘርፍ ተጠሪ የሆኑት ወይዘሮ ዊንታና ንጉሴ ለዝግጅት ክፍላችን በሰጡት አስተያየት፤ "በበርካታ የስልጠና መስኮች ሰልጣኞችን በማፍራት እና ለከተማዋ ብሎም ለሀገር በማበርከት ረገድ አንጋፋ ነው፡፡ በተለይ በስነ ጥበብ (በኤስቴቲክስ) የስልጠና ዘርፍ በአንጋፋነቱም ሆነ ብቁና ስመጥር ሙያተኞችን በማፍራት ይታወቃል፡፡ በዚህ ዘርፍ ከሚሰጣቸው ስልጠናዎች መካከል ስዕል፣ የሃውልት ቅርጻ ቅርፅ፣ ቴአትር፣ ሙዚቃ፣ ስፖርት ተጠቃሾች ናቸው" ብለዋል፡፡

የተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ በሁሉም የቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች የሚሰጡ ስልጠናዎችን ከመስጠት ባሻገር በስነ ጥበብ (የኤስቴቲክስ) ስልጠና ዘርፍ በአሰልጣኞች እና ሰልጣኞች የተሠሩ የሙዚቃ፣ የቴአትር፣ የቅርጻ ቅርጽ እና ሥዕል ስራዎች ለታዳሚዎች ለዕይታ የሚቀርብበት ልምድ መኖሩን የሚያነሱት የስልጠና ክፍሉ ኃላፊ ወይዘሮ ዊንታና፤ በተለይ የሥዕል ዓውደ ርዕይ በማካሄድ ሰልጣኞች የሰሯቸውን ስራ ለተመልካች የሚያደርሱበት ተደጋጋሚ ዕድል አለ።

ኮሌጁ በከተማ አስተዳደር ደረጃ በብቸኝነት የሚሰጠውን የስነ ጥበብ (የኤስቴቲክስ) የስልጠና ዘርፍ በርካታ ሰልጣኞች ለመቀላቀል ፍላጎት ያሳያሉ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ መስፈርቱን የሚያሟሉ እና የስልጠና ክፍሉ ማስተናገድ በሚችለው አቅም መሰረት ተቀብሎ ያሰለጥናል፡፡ ኮሌጁ ለብዙ ዓመታት በዘለቀው የማሰልጠን ልምድና ብቃቱ በርካታ የጥበብ ሰዎችን በተለያዩ ጊዜያት አሰልጥኖ ለውጤት አብቅቷል፡፡ የቅርብ ጊዜዎቹን እንኳን ብንመለከት የሙዚቃ ባለሙያ እና ድምፃዊት የሺ ደምመላሽ፣ ድምጻዊ እሱባለው ይታየው፣ ሙዚቃ አቀናባሪ ታምሩ አማረ እና መሰል የህዝብ አድናቆት የተቸራቸው ጥበበኞች መኖራቸውን በአብነትነት አንስተዋል፡፡

ከስልጠና ዘርፍ ተጠሪዋ እንዳገኘነው መረጃ፤ የተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ የስነ ጥበብ እና ሙዚቃ በሚል በ1999 ዓ.ም. እንደ አንድ የትምህርት ክፍል ሆኖ የተጀመረበት ወቅት ነበር፡፡ ከዚህ ቀደም የተፈሪ መኮንን ባንድ በሚል



ፎቶ በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል

የስነ ጥበብ ሰልጣኞች የሙዚቃ፣ የሃውልት ቅርፃ ቅርፅ እንዲሁም የስዕል ልምምድ ሲያደርጉ

> **አሁን ላይ ለስነ ጥበብ የተሰጠው ትኩረት ካለፉት ጊዜያት ጋር ሲነፃፀር ዋጋው እጅግ የላቀ መሆኑን ተከትሎ ገና ሰልጣኞች ስልጠናቸውን ለማጠናቀቅ አንድ ዓመት ሲቀራቸው ለስራ ቅጥር የሚጠይቁ ድርጅቶች አሉ**

የሙዚቃ ቡድኖች ነበሩት፡፡ ከዚያ ቀጥሎ ነው በስልጠና ክፍል ደረጃ ትምህርት መሰጠት የጀመረው፡፡ እንደ ስልጠና አይነቶቹ በቀን፣ በማታ እንዲሁም በቅዳሜ እና እሁድ የትምህርት መርሃ ግብር ስልጠናዎችን ከደረጃ 1 እስከ ደረጃ 5 ድረስ ይሰጣል፡፡

"አንጋፋው የተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ለስነ ጥበብ የስልጠና ዘርፍ የሰጠው ትኩረት እጅግ ልዩ ነው" ያሉት የሥልጠና ዘርፍ ተጠሪዋ፤ ተፈጥሮን ለማድነቅ ብሎም አሁናዊ ክንውኖችን በእጃችን ላይ ባሉ የቀለም ብሩሾች ከትበን ለመያዝ የሚያስችለን የስዕል ጥበብ በክፍሉ አሰልጣኞች አማካኝነት በተቋሙ ቅጥር ግቢ ውስጥ ባሉ የተለያዩ ቦታዎች በመሳል ቅጥረ ግቢው የማህበረሰቡን ቀልብ እንዲስብ ትልቅ አቅም መፍጠሩን አብራርተዋል።

አንድ ሰልጣኝ ስልጠናውን ከመጀመሩ በፊት ስለሚሰለጥነው ጉዳይ ፍላጎትና ተሰጥኦ እንዳለው ማረጋገጥ ይኖርበታል አልያ የሚያደርገው ነገር በሙሉ ስራ የሚሆንበት አጋጣሚ ሰፊ ነውም ብለዋል፡፡

የስልጠና ዘርፍ ተጠሪዋ እክለው እንደገለጹት፤ በአዲስ አበባ በኮሪደር ልማት ሥራዎች እጅግ የሚያስደስቱ ተግባራት ተከውነዋል፡፡ ለዚህም የቀኝ እጅ በመሆን በበርካታ የከተማዋ አካባቢዎች በሚገኙ አጥሮችና የባቡር መንገድ ግድግዳዎች ላይ የተለያዩ ተፈጥሮን ለማድነቅ የሚያመቹ የስዕል ሥራዎች በመሳል ረገድ የተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ሰልጣኞች አሻራቸውን በስፋት አኑረዋል፡፡

በፖሊ ቴክኒክ ኮሌጁ በሚገኘው የስነ ጥበብ (ኤስቴቲክስ) የስልጠና ዘርፍ ስልጠናዎችን ጨምሮ ሌሎችም የተግባር ትምህርት 70 በመቶ እንዲሁም 30 በመቶ ደግሞ የንድፈ ሃሳብ ትምህርት ባካተተ መልኩ እየተሰጠ ነው፡፡ የተግባር ስልጠናው ሰፊ የልምምድ ጊዜ የሚወስድና 'የሰልጣኞች አቅም ምን ያህል ነው?' የሚለውን ለማወቅ እንደሚያግዝ የተናገሩት ወ/ሮ ዊንታና፤ የንድፈ ሃሳብ ትምህርቱ ደግሞ ሰልጣኞች መሰረታዊ እውቀት እንዲይዙ የሚያግዛቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡

አሁን ላይ ለስነ ጥበብ የተሰጠው ትኩረት ካለፉ ጊዜያት ጋር ሲነፃፀርም ዋጋው እጅግ የላቀ መሆኑን ተከትሎ ገና ሰልጣኞች ስልጠናቸውን ለማጠናቀቅ አንድ ዓመት ሲቀራቸው ለስራ ቅጥር የሚጠይቁ ድርጅቶች ስለመኖራቸው ገልፀዋል፡፡ አያይዘውም ሙያው እጅግ የተከበረ መሆኑን ተከትሎ የተለያዩ ድርጅቶች በስዕል፣ በሙዚቃ እንዲሁም መሰል የትምህርት ዘርፎች ላይ የተሻለ ተሰጥኦ ያላቸውን ሰልጣኞች ቅጥር ይፈፅማሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በተለያዩ የቴአትር ቤቶች፣ የሙዚቃ ቤቶች፣ የስዕል ጋላሪ ማሳያ ስፍራዎች ላይ በቀላሉ ቅጥር ይፈፅማሉ፡፡ በዚህም ስራ ቀጣሪ እና ስራ ፈላጊ በቀላሉ የሚገናኙበት አግባብ ስለመፈጠሩ ጭምር አስታውቀዋል፡፡

እንደ የስልጠና ዘርፍ ተጠሪዋ ወይዘሮ ዊንታና ገለፃ፤ በኤስቴቲክስ የስልጠና ዘርፍ ያጠናቀቁ ሰልጣኞች የመመረቂያ ስራዎቻቸውን በተለያዩ መድረኮች ላይ ያቀርባሉ፡፡ በተለያዩ የስዕል ማሳያ ኤግዚቢሺኖች፣ ቴአትር ቤቶች፣ የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር፣ ህጻናትና ወጣቶች በሚገኙበት እንደየ ዘርፋቸው ስራዎቻቸውን ያቀርባሉ፡፡

ኢኮኖሚ

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አርሶ አደር እና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# ከሸማችነት ወደ አምራችነት

- በከተማዋ በግቢና በጓሮ አትክልት ልማት 625 ሺህ 725 ተጠቃሚዎች የተሰማሩ ሲሆን፣ በዚህ ዓመት በጓሮ አትክልት 20 ሺህ 790 ቶን እንዲሁም በማሳ አትክልት ደግሞ 46 ሺህ 160 ቶን ምርት ይገኛል ተብሏል

በይግለጡ ጓዴ

አቶ አረጋ ታደሰ በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 4 ነዋሪ ናቸው፤ የአካል ጉዳተኝነት ሳይበግራቸው በዶሮ እርባታ ስራ ተሰማርተው ውጤታማ ሆነዋል፡፡ እኒህ አባት በመኖሪያ ቤታቸው ባለቻቸው ውስን ቦታ የዶሮ ኬጂዎችን በማዘጋጀት በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ኑሮአቸውን አሻሽለዋል፡፡

ዶሮ የማርባት የቆየ ፍላጎት እንደነበራቸው የሚያስታውሱት አቶ አረጋ ከሚያውቋቸው ደጋግ ሰዎችና ቤተሰቦቻቸው ባገኙት የገንዘብ ድጋፍ የመኖሪያ ቤታቸውን ከፍለው የዶሮ ቤት (ኬጅ) በመስራት የጀመሩት ስራ፣ የጉለሌ ክፍለ ከተማ አርሶ አደርና የከተማ ግብርና ጽህፈት ቤት ባደረገላቸው የ65 እንቁላል ጣይ ዶሮዎች ድጋፍ የበለጠ እንደተጠናከረላቸው ተናግረዋል፡፡

በጀመሩት የዶሮ እርባታ ስራ ውጤታማ መሆናቸውን የጠቆሙት አቶ አረጋ፣ በየቀኑ ከሚያገኙት 55 እንቁላሎች የተወሰኑትን ለቤት ውስጥ ፍጆታ በማዋል ቀሪዎቹን ለገበያ ያቀርባሉ፤ አንዱን እንቁላል በ17 ብር ሂሳብ በመሸጥ ኑሮአቸውን መደጎም መቻላቸውን ገልፀውልናል፡፡

ሆኖም የዶሮ መኖ ዋጋ ከጊዜ ወደ ጊዜ በመጨመሩ በስራቸው ላይ እንቅፋት እንደሆነባቸው አቶ አረጋ ገልፀው፣ ለቀጣይም የዶሮ እርባታ ስራቸውን በማስፋፋት ከዘርፉ ይበልጥ ተጠቃሚ ለመሆን ጠንክረው እየሰሩ ይገኛሉ፡፡

በተመሳሳይ በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 4 በተለምዶ ቀጨኔ ተብሎ የሚጠራ አካባቢ ነዋሪ የሆኑት ወይዘሮ ወይንሸት ሰብስቤ የወተት ላሞችን በማርባት ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ የወተት ላሞችን ማርባት ከ30 ዓመት በፊት እንደጀመሩ የሚጠቁሙት ወይዘሮ ወይንሸት ስራውን በተደራጀ መንገድ መስራት የጀመሩት ግን ከሁለት ዓመት በፊት በተጀመረው የሌማት ትሩፋት ፕሮግራም አማካኝነት ነው፡፡

ወይዘሮ ወይንሸት አሁን 30 የወተት ላሞች እንዳሏቸው ገልፀው፣ በግላቸው ተጠቃሚ ከመሆን አልፈው ለሶስት ወጣቶችም የስራ እድል መፍጠራቸውን ተናግረዋል፡፡

በከተማ ደረጃ ዘርፉን በተደራጀ እና በዘመናዊ መንገድ በመስራታቸው እውቅና ማግኘታቸውን ወይዘሮ ወይንሸት ጠቁመው፣ በአንድ ቀን እስከ 150 ሊትር የወተት ምርት ያገኛሉ፡፡

ወይዘሮ ወይንሸት ወተት እና የወተት ተዋጽኦ ከሀገር ውስጥ ገበያ ባለፈ ለውጭ ገበያ ያቀርባሉ፡፡ በዚህም በወተት እና ወተት ተዋጽኦ ሽያጭ ገቢያቸውን ማሳደግ መቻላቸውን ጠቁመዋል፡፡

ከላሞች የሚወጣውን ተረፈ ምርት ለባዮ ጋዝ ቴክኖሎጂ በማዋል ለምግብ ማብሰያነት ይጠቀማሉ፡፡ የወተት ልማት ዘርፉን ደስተኛ ሆነው እና በፍላጎታቸው የሚሰሩት ወይዘሮ ወይንሸት የመስሪያ ቦታ እጥረት እንዲሁም በየጊዜው የመኖ ዋጋ መጨመር በስራቸው ላይ ፈተና እንደሆነባቸው ሳይገልፁ አላለፉም፡፡




በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 9 የሚገኘው ‘ዓለማችን የካቶሊክ የአካል ጉዳተኛ ህጻናት ማገገሚያ ማዕከል’ ደግሞ በግቢው የሚገኙ አካል ጉዳተኛ ህጻናት የተመጣጠነ ምግብ እንዲያገኙ ባላቸው ትርፍ ቦታ የተቀናጀ የከተማ ግብርና የእጽዋት እና የእንስሳት እርባታ በማከናወን ለምግብ ፍጆታነት ያውላሉ።

በማዕከሉ 300 ዶሮዎችን በማርባት በቀን 300 እንቁላል በማግኘት ለህጻናት ምግብነት ያውላሉ፡፡ በቀጣይ በተቀናጀ የከተማ ግብርና ይበልጥ ተጠቃሚ ለመሆን የተጀመሩ ስራዎችን ይበልጥ በማጠናከር እንዲሁም በበግ ማድለብ ስራ ዘርፍ እንደሚሰማሩ አስታውቀዋል።

የከተማ ግብርና በከተሞች የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚደረግ ወሳኝ ጥረት ነው፡፡ ይህ ዘርፍ በውስን ቦታ ላይ ዘመናዊ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የሚከናወን ሲሆን፣ የእንስሳት፣ የዶሮ፣ የዓሳ እርባታ፣ ንብ ማነብ፣ ወተትና የወተት ተዋፅኦ ምርትን፣ ፍራፍሬ፣ የጓሮ አትክልት ማምረት እና የተመረቱ ምርቶችን ማቀነባበርንም እንደሚያካትት እሙን ነው፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች በከተማ ግብርና የሚያገኙትን ምርት ለቤት ፍጆታ ከማዋል ባሻገር ለገበያ በማቅረብ ተጨማሪ የገቢ ምንጭ ማግኘት ከጀመሩ ሰነባብተዋል፡፡ የግብርና ምርትና ምርታማነት በመጠንና በጥራት በማሳደግ ኢኮኖሚን በማሻሻል በከተማና በከተማ ዙሪያ የሚኖረው የህብረተሰብ ክፍል የምግብ ዋስትና እንዲሻሻል እያደረገ ያለ ዘርፍም ነው፡፡

በአሁኑ ወቅት በርካታ የከተማዋ ነዋሪዎች በዶሮና በወተት ልማት፣ በከብት ማድለብ፣ በንብ ማነብ፣ በሰብል እና በሌሎችም ዘርፎች ተሰማርተው ውጤታማ እየሆኑ መጥተዋል። ነዋሪዎች በመኖሪያ ቤት ቅጥር ግቢ፣ ትምህርት ቤትን ጨምሮ በተለያዩ ተቋማት የጓሮ አትክልቶችን በመትከል የምግብ ፍጆታቸውን በመሸፈን እንዲሁም የስራ ዕድል እየፈጠሩ ነው፡፡

በጉለሌ ክፍለ ከተማ የወረዳ 4 አስተዳደር የእንስሳት ሃብት ልማት ባለሙያ አቶ ጌታሁን ጉተታ በወረዳው የተቀናጀ የከተማ ግብርና ተግባራዊ እንዲሆን ሙያዊ ድጋፍ እንደሚያደርጉ ገልጸው፣ በዘርፉ የተሰማሩት ውጤታማ እንዲሆኑ የቅርብ ድጋፍና ክትትል በማድረግ ላይ ናቸው፡፡ የተቀናጀ የከተማ ግብርና ተሳታፊዎች የተሻሻሉ ዝርያዎችን እንዲጠቀሙና ህክምና እንዲያገኙ ያደርጋሉ፡፡

ባለሙያው ለተጠቃሚዎች የህክምናና የተሻሻሉ ዝርያዎችን በአግባቡ እንዲጠቀሙ የቅርብ ሙያዊ ድጋፍ በማድረጋቸውም ተጠቃሚዎች የሚያገኙት ምርት እያደገ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ የተመጣጠነ መኖ በተመጣጣኝ ዋጋ ገዝተው እንዲጠቀሙ የገበያ ትስስር መደረጉንም ጠቁመዋል፡፡

በጉለሌ ክፍለ ከተማ የአርሶ አደርና የከተማ ግብርና ልማት ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ሳልፋኮ ሻኖ የመኖሪያ ግቢ እና ክፍት ሰፋፊ ቦታ ያላቸው ተቋማት እና ነዋሪዎች በተቀናጀ የከተማ ግብርና እንዲሳተፉ እየተደረገ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

በክፍለ ከተማው የተቀናጀ የከተማ ግብርና በመንግስት እና በግል ተቋማት እንዲሁም በትምህርት ቤቶች ላይ ተግባራዊ እየተደረገ ነው። በእንጦጦ አምባ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዶሮ እርባታ፣ የጓሮ አትክልት፣ እንዲሁም በመድሐኒዓለም 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ደግሞ የበግ እና የዶሮ እርባታ እንዲሁም የጓሮ አትክልት በመትከል ተጠቃሚ መሆናቸውን ጠቁመዋል፡፡

ከትምህርት ቤቶች በተጨማሪ በጤና ተቋማት የተቀናጀ የከተማ ግብርና ስራ በመስራት ተጠቃሚ እንዲሆኑ መደረጉን አቶ ሳልፋኮ ጠቅሰው፣ በእንጦጦ የተቀናጀ የመኖሪያ መንደር ሼድ በመገንባት 40 ወጣቶችን በማደራጀት በወተት ላም እና በጓሮ አትክልት ልማት ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል ብለዋል፡፡

የተቀናጀ የከተማ ግብርና ስራ በክፍለ ከተማው ውጤታማ እንዲሆን ብድር ማመቻቸት፣ የምርጥ ዘር፣ የመስሪያ ቦታ አቅርቦት፣ የመኖ ትስስር፣ የባለሙያ ድጋፍ፣ የህክምና እና የገበያ ትስስር ድጋፎች በማድረግ ላይ መሆናቸውን አቶ ሳልፋኮ ተናግረዋል፡፡

በቀጣይም በክፍለ ከተማው የተቀናጀ የከተማ ግብርና ስራን አጠናክሮ ለማስቀጠል የ90 ቀናት እቅድ ከወዲሁ በማቀድ በትኩረት እየተሰራ መሆኑን ኃላፊው ገልጸዋል፡፡

በከተማ አስተዳደሩ በከተማ ግብርና በሌማት ትሩፋት እየተሰሩ ያሉ የተቀናጀ የከተማ ግብርና ስራዎች ውጤታማ መሆን ችለዋል፡፡ አዲስ አበባ ላይ የከተማ ግብርና ስራ አይቻልም የሚለው አመለካከት መቀየሩን እና የነዋሪዎች የይቻላል አስተሳሰብ በተግባር የተረጋገጠ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

በጉለሌ ክፍለ ከተማ በተቀናጀ የከተማ ግብርና ስራ በእንስሳት ዘርፍ 23 ሺህ 474 ተሳታፊዎች መሰማራታቸውን የጽህፈት ቤቱ መረጃ ያመላክታል። በመረጃው መሠረት፣ በእንቁላል ጣይ ዶሮዎች 22 ሺህ 678 ተሳታፊ ግለሰቦች የተሳተፉ ሲሆን፣ በቀን 18 ሺህ 142 እንቁላል ይመረታል፡፡ በወተት ከብት ደግሞ 280 ተሳታፊዎች አሉ፡፡ በዚህም በቀን 9 ሺህ 360 ሊትር ወተት ይመረታል፡፡ በጓሮ አትክልት ልማት 41 ሺህ 416 ተሳታፊዎች ተሰማርተዋል። በዚህም በቀን በአማካይ 1 ነጥብ 1 ቶን ምርት ይገኛል፡፡ በክፍለ ከተማው በቀጣይ በጓሮ አትክልት ምርት ከ1 ሺህ 377 ቶን በላይ ምርት ይገኛል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ በተቀናጀ የከተማ ግብርና ስራ በእንስሳት ዘርፍ 423 ሺህ 113 ተጠቃሚዎች እንደሚሳተፉ የከተማዋ አርሶ አደርና የከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን መረጃ ያመላክታል። በመረጃው መሠረት፣ በእንቁላል ጣይ ዶሮዎች 414 ሺህ 892 ግለሰቦች የሚሳተፉ ሲሆን፣ በ2017 ዓ.ም ብቻ 820 ሚሊዮን 58 ሺህ 469 የእንቁላል ምርት ተገኝቷል፡፡

በስጋ ዶሮ 1 ሺህ 174 ነዋሪዎች ተሳታፊ ሲሆኑ፣ 8 ሺህ 531 ቶን የዶሮ ስጋ ምርት ተገኝቷል፡፡ በተያዘው ዓመትም 10 ሺህ 665 ቶን የዶሮ ስጋ ምርት እንደሚገኝ ከወዲሁ ይጠበቃል፡፡

በወተት ከብት ደግሞ 5 ሺህ 246 ተሳታፊዎች አሉ፤ በ2017 ዓ.ም 70 ሚሊዮን 869 ሺህ 552 ሊትር ወተት ምርት ተገኝቷል፡፡ በተያዘው በጀት ዓመትም 99 ሚሊዮን 217 ሺህ 372 ሊትር ወተት ምርት እንደሚገኝ የከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን መረጃ ያሳያል፡፡

በግቢና በጓሮ አትክልት ልማት 625 ሺህ 725 ተጠቃሚዎች ተሰማርተዋል፤ ከጓሮ አትክልት 20 ሺህ 790 ቶን ምርት ተገኝቷል፡፡ በዚህ ዓመት በከተማዋ በጓሮ አትክልት ምርት 20 ሺህ 790 ቶን እንዲሁም በማሳ አትክልት ደግሞ 46 ሺህ 160 ቶን ምርት ይገኛል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# መዲናዋ የአፈር ብክለትን ለመከላከል ምን እየሰራች ነው?

- **በአዲስ አበባ የሚከሰተው የአፈር ብክለት መንስኤ በዋነኛነት ኢንዱስትሪዎች መሆናቸው ተጠቁሟል**

**በለይላ መሀመድ**

የአፈር ብክለት ከአካባቢ ብክለት ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ነው፡፡ “አፍንጫ ሲመታ አይን ያለቅሳል ለካ” እንደሚባለው የአንዱ መበከል ለሌላው ብክለት ምክንያት ይሆናል፡፡ ለምሳሌ፡- የአፈር ብክለት ከውሃ ብክለት ጋር የተሳሰረ ነው፡፡ ወንዞች ሲበከሉ በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ አፈር ይበከላል፡፡ የተበከለ ወንዝ በመሬት ውስጥ ሰርጎ ሲገባ አፈር ይበክላል፡፡ ይህንን መነሻ በማድረግ በዚህ ዕትማችን የአፈር ብክለት ምንነት፣ መንስኤዎቹ እና ተጽዕኖው እንዲሁም የአፈር ብክለትን በመከላከል እና በመጠበቅ ረገድ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ምን እየሰራ እንደሆነ እንቃኛለን፡፡



ፎቶ ከአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን
በደረቅ ቆሻሻ የተበከለ አፈር

አቶ ሙላቱ ወሰን በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአካባቢ ብክለት ጥናት ባለሙያ ናቸው። እሳቸው እንደገለፁት፤ የአፈር ብክለት አፈር በተለያዩ ምክንያቶች የተፈጥሮ ይዘቱን ማጣቱን የሚያመላክት ነው። የአፈር ብክለት በዋነኛነት በሰዎች፣ በእንስሳት እና ተክሎች አማካኝነት የሚከሰት ነው፡፡ ሰዎች ለተለያዩ አገልግሎቶች በፈሳሽ ወይም በጠጣር መልክ የሚጠቀሟቸው ኬሚካሎች ከአፈር ጋር በሚዋሀዱበት ሰዓት የተፈጥሮ ይዘቱን ጠብቆ የቆየው ጤናማው አፈር ለብክለት ይዳረጋል፡፡ ተፈጥሯዊ ይዘቱን በማጣትም ጉዳት ያደርሳል፡፡ ይህ ሁኔታ ሲከሰት የአፈር ብክለት እንዳለ ይታመናል፡፡

የጥናት ባለሙያው አክለውም፤ የአፈር ብክለት ከአካባቢ ብክለት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ የአካባቢ ብክለት እና ብክነት የሰው ልጅ ተደራራቢ እና ውስብስብ ችግሮች ውስጥ እንዲገባ ከሚያደርጉ ምክንያቶች መካከል ቀዳሚው ነው፡፡ የአካባቢ ብክለት እና ብክነት የሚከሰተው በዋናነት የሰው ልጅ ተፈጥሮን ያለአግባብ በመጠቀም እንዲሁም እንክብካቤ ባለማድረግ ሲሆን፤ ሌላው በተፈጥሯዊ ምክንያት ነው፡፡ ብክነት ሲባል የአካባቢ ሃብቶች በተለይም የተፈጥሮ ሃብቶች በአግባቡ አለመያዝን የሚያመለክት ነው፡፡ ብክለት የሚባለው ደግሞ የአንድ አካባቢ አፈር፣ ውሃ፣ አየር፣ ድምፅ የመሳሰሉት ቁስ አካላዊ (ፊዚካላዊ) እና ሥነ ህይወታዊ (ባዮሎጂካዊ) ይዘቶች ማጥፋት ወይም ማበላሸት ማለት ነው። የአካባቢ ብክለት የተፈጥሮን ወይም ሠው ሰራሽ ሀብቶችን በመበከል በሰው፣ በእንስሳት እና በሌሎች ህይወት ባላቸው ነገሮች ላይ ጉዳት ማድረስን ያጠቃልላል።

በመዲናችን አዲስ አበባ እንዲሁም በሀገራችን እየተስፋፉ ያሉ ኢንዱስትሪዎች፣ ሰፋፊ እርሻዎች በምርት ሂደት ውስጥ የሚጠቀሟቸው ግብአቶች እንዲሁም በምርቶች አያያዝ፣ አጠቃቀምና አወጋገድ ሥርዓት ማጣት ውስጥ የሚፈጠሩ ቆሻሻዎች ለአካባቢ በተለይም ለአፈር ብክለት ዋነኛ ምክንያቶች ናቸው፡፡ ከኢንዱስትሪዎች የሚመነጭ ቆሻሻ ከምንጩ እንዲቀንስ ካልተደረገ ወይም በአግባቡ ካልተያዘ በአካባቢው የሚገኙ የውሃ አካላትን፣ አፈርንና ከባቢ አየርን በቀላሉ ሊበክል ይችላሉ፡፡

ሌላው ለአፈር ብክለት መንስኤ የሆነው ሰዎች በሚኖሩበት አካባቢ ቆሻሻን በአፈር ውስጥ በመወርወር እንዲሁም በአፈር ላይ ቆሻሻ ውሃን በማፍሰስ የሚያደርጉት የተሳሳተ ልማዳዊ ድርጊት ነው፡፡ ሰዎች በምርትና ምርታማነት ሂደት ውስጥ ተገቢ ያልሆነ የግብርና ግብአቶችን መጠቀም ለአፈር ብክለት ትልቅ ምክንያት ይሆናል፡፡ ለምሳሌ፡- የሰው ሠራሽ ማዳበሪያ አጠቃቀም ላይ ከመጠን ያለፈ የናይትሮጅን፣ ፎስፎረስ እና ሌሎች ኬሚካሎች ወደ መሬት ሲገቡ አፈር ይበከላል፡፡ ከፍተኛ የእንስሳት ግጦሽ እና የእንስሳት እንቅስቃሴዎችም መሬት ላይ ያሉ ዕፅዋቶች እንዲራቆቱና እንዲጠፉ፣ አፈር እንዲሸረሸር እና ብክለት እንዲከሰት ምክንያት ሆኗል፡፡

በሌላ በኩል፤ ለውበት የሚተከሉ ዛፎች ቅጠል በተገቢው ባለመወገድ ረግፈው ሲበሰብሱ የአፈር መጨናነቅን ያስከትላሉ፡፡ ይህም ሌሎች እፅዋት የሚያገኙትን የአየር፣ የውሃ እና አልሚ ምግቦች መጠን ሊቀንስ ይችላል። እነዚህ ሁሉ አፈሩን ሊያበላሹ ስለሚችሉ የተክሎችን እድገት አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡

> **የተበከለው የወንዝ ውሃ በመሬት ላይ ወይንም ወደመሬት ሰርጎ በመግባት አፈር እንዲበከል ያደርጋል**

## የአፈር ብክለት በአዲስ አበባ

“በአዲስ አበባ ከተማ የአፈር ብክለቱ እስከምን ድረስ ነው? ከሌሎች አካባቢዎች በምን ይለያል?” ሲል የዝግጅት ክፍሉ ላነሳላቸው ጥያቄ የጥናት ባለሙያው አቶ ሙላቱ በሰጡት ምላሽ፤ “አዲስ አበባ ከተማ የበርካታ ኢንዱስትሪዎች መገኛ በመሆኗ በከተማዋ የሚከሰተው የአፈር ብክለት መንስኤ በዋነኛነት ኢንዱስትሪዎች ናቸው፡፡ አፈሩ እንዲበከል የሚያደርገው ዋና ምክንያትም በከተማዋ የሚገኙ አብዛኞቹ ፋብሪካዎች ፍሳሻቸውን ወደ ወንዝ ስለሚለቅቁ ነው። በተመሳሳይ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ያልተጣራ ፍሳሻቸውን ወደ ወንዝ ነው የሚለቅቁት፡፡ ግለሰቦችም የሚለቋቸው ደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻዎች ሌላው የአፈር ብክለት መንስኤ ነው፡፡ ወንዝ ላይ ብክለት ተከሰተ ማለት ከአፈር ጋር ግንኙነት ስላለው አፈር ተበከለ ማለት ነው። የተበከለው የወንዝ ውሃ በመሬት ላይ ወይንም ወደመሬት ሰርጎ በመግባት አፈር እንዲበከል ያደርጋል” ብለዋል። እነዚህ ከፋብሪካም ሆነ ከተቋማትና ግለሰቦች ወደ ወንዝ የሚለቀቁ መርዛማ ፈሳሽ ቆሻሻዎች ከአፈር ጋር ስለሚቀላቀሉ የአፈርን የተፈጥሮ ይዘት እንዲቀየር እንደሚያደርጉ አብራርተዋል፡፡

## ችግሩን ለመከላከል ባለስልጣኑ ምን ሠራ?

የጥናት ባለሙያው አቶ ሙላቱ የአፈር ብክለትን እንዴት መከላከል እንደሚቻልና ችግሩን በመከላከል ረገድ ምን እየተሠራ እንደሆነ አያይዘው እንደገለጹት፤ በኢንዱስትሪዎች፣ በእርሻ ቦታ፣ በከተሞች፣ በቆሻሻ መጣያ ስፍራዎች ፍሳሽ ቆሻሻ ማከም፣ ከመኖሪያ የሚወጣን ፍሳሽ በተገቢው መንገድ ማስወገድ፣ ከሰው ሰራሽ ማዳበሪያ ይልቅ የተፈጥሮ ማዳበሪያን መጠቀም እና የተበከለ ውሃን በማከም ጥቅም ላይ ማዋል ነው፡፡

ችግሩን በዘላቂነት በመከላከል ረገድ፤ ለማህበረሰቡ ግንዛቤ የመፍጠር ስራ ይሰራል፡፡ በዘርፉ ለተሰማሩ ለሚመለከታቸው አፈርን ለሚጠቀሙ በተለይም የከተማ ግብርና ላይ ለሚሰሩ ባለሙያዎች እና አርሶ አደሮች ግንዛቤ የመፍጠር ስራ እየተሰራ ነው፡፡ አፈር ሲበከል ሊያስከትል የሚችለውን የጤና ችግር ለማስገንዘብ እየተሰራ ነው፡፡ ግንዛቤ ከመፍጠር በተጨማሪ በደንብ ቁጥር 180/2017 ውሃው እንዳይበከል ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት የቅጣት እርምጃ እየተወሰደ ነው፡፡ በአፈር ውስጥ ያለውን የብክለት ደረጃ ለማወቅና “የጉዳት ደረጃው እስከምንድረስ ነው?” የሚለውን እንዲሁም ችግሩን በዘላቂነት ለመከላከል በተለያዩ አካላት ጥናቶች እየተከናወነ ነው፡፡ ጥናቱ በስፋት የሚደረገውም በመንግስት፣ በተቋማትና በግለሰቦች ቅንጅታዊ አሰራር ነው፡፡ በጥናቱም “አስጊ ነው ወይንስ ምን ላይ ይገኛል?” የሚለው ይታወቃል፡፡

## የኢትዮጵያ... ከገጽ 6 የዞረ

እንደተፃፈው፣ ህወሓት የኤርትራ ነፃ አውጪ ግንባር ታናሽ ወንድም ነው፡፡ የኤርትራ ነፃ አውጪ ግንባር ቀድሞ ነው የተመሰረተው፡፡ ከውጭ ያለውን ግንኙነት ሲመራ፣ የሚገኘውን ድጋፍ ሲያደራጅ የነበረው፣ የተሻለ ልምድና አቅም ያለው የኤርትራው ቡድን ነው፡፡ ህወሓት የኤርትራ ነፃ አውጪ ግንባር የጠየቀውን ጥያቄ ሁሉ አንድም መደራደሪያ ሳያመጣ ነው ሲቀበል የነበረው። የኤርትራን ከኢትዮጵያ መገንጠል ገና ማዕከላዊ ስልጣን ሳይቆጣጠር ነው ሙሉ በሙሉ የተስማማው፡፡ ኢትዮጵያ በቀይ ባህር የነበራትን ባህር ሀይል፣ የጦር መርከቦች፣ የነዳጅ ማጣሪያ ላይ ጥያቄ ሳያቀርብ ሙሉ በሙሉ ለኤርትራ አስረክቧል፡፡

በህግ ባልና ሚስት ሲፋቱ ንብረት ይከፋፈላሉ፡፡ ንብረት ብቻ ሳይሆን እዳም ካለ ይካፈላሉ፡፡ በዓለም አቀፍ ህግ ኤርትራ በአጠቃላይ በኢትዮጵያ ስም የመጣ ብድር ወይም እዳ ካለ እሱንም ይዛ መሄድ ነበረባት፡፡ ደቡብ ሱዳን ከሱዳን ስትለይ የነዳጅ ቦታዎችን ብቻ አይደለም ይዛ የሄደችው፡፡ ሱዳን እንደሀገር ከተቀበለችው እዳ በሚደርስባት ልክ ተሰልቶ ይዛ ሄዳለች። የኢትዮጵያ መንግስታት በኤርትራ የሰሯቸው ትላልቅ ፕሮጀክቶች ነበሩ፡፡ ፕሮጀክቶቹ በኢትዮጵያ ህዝብ ስም በመጣ ብድር የተሰሩ ናቸው፡፡ በከተማ ልማት፣ የወደብ ማስፋፊያ፣ የነዳጅ ማጣሪያ እና ሌሎችም ስራዎች ከፍተኛ ሀብት ፈስሶባቸዋል። ነገር ግን ኤርትራ ከኢትዮጵያ ስትለይ እነዚህን ሀብቶች ምክንያት በማድረግ ድርድር አልተደረገም፡፡ ገና ህዝበ ውሳኔ ሳይደረግ ነው ኢትዮጵያ የባህር በር ያጣችው፡፡

**አዲስ ልሳን፡- ኢትዮጵያ የባህር በር ያጣችበት መንገድ የህግ መሠረት እንደሌለው የሚያነሱ ወገኖች አሉ። እርስዎ ይህን እንዴት ያዩታል?**

**አቶ ኪያ፡-** አዎ! የህግ መሰረት የለውም። በመጀመሪያ ኢህአዴግ አሸንፎ ማዕከላዊ መንግስቱን ከተቆጣጠረ በኋላ ሰኔ ወር ላይ የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ያሳተፈ ኮንፈረንስ ተካሂዶ ነበር፡፡ በርግጥ በኮንፈረንሱ እነማን ይሳተፉ የሚለውን የወሰነው ህወሓት ነው፡፡ ያኔ የበላይነት የነበረው ህወሓት ነበር፤ ከጀርባው ደግሞ ሻእቢያ ነበረ፡፡ በሰኔው ጉባኤ የሽግግር መንግስት ተቋቋመ፡፡ አርማው ድልድይ ሲሆን ስሙ እንደሚያመላክተው ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ የሚያሸጋግር እንጂ በኢትዮጵያውያን ይሁንታ የተመረጠ መንግስት አልነበረም፡፡ በሽግግር መንግስቱ ወይም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደረጃ ወደብን በተመለከተ ምክክር የተደረገበት ቃለ ጉባኤ ወይም ደብዳቤ የለም፡፡

በዓለም አቀፍ ህግ አንድ ሀገር፣ ሀገር ለመባል አራት ነገሮች መሟላት አለባቸው። ህዝብ፣ ግዛት፣ መንግስት እና ዓለም አቀፍ እውቅና ናቸው፡፡ ብዙ ሀገራት የሚቸገሩት ዓለም አቀፍ እውቅና ማግኘት ነው፡፡ ለምሳሌ፡- ሶማሊላንድ ሶስቱን አሟልታ ሀገር ለመሆን የጎደላት እውቅና ማግኘት ነው፡፡ ይህም የሆነው የሶማሊያ ማዕከላዊ መንግስት እውቅና ስላልሰጠ ነው፡፡ በዓለም አቀፍ ህግ የሀገራት የግዛት አንድነት መጠበቅ ትልቅ ዋጋ የሚሰጠው መርህ ነው። የአፍሪካ ህብረትና የተባበሩት መንግስታት ድርጅት መቋቋሚያ አዋጅን ብናይ የሀገራት የግዛት አንድነት ማስጠበቅ ዋና መሰረቱ ነው፡፡

ህወሓት የእውቅና ደብዳቤ ለሻእቢያ ባይሰጥ፤ ሻእቢያ አስመራንም ይዞ ዕድሜ ልክ ይዋጋል እንጂ ኤርትራ ሀገር አይሆንም ነበር። በዓለም ላይ ለሚገነጠል ሀገር ከነባህርና ወደቡ እውቅና ስጡልኝ ብሎ የለመነ ሀገር የለም፤ ከህወሓት መንግስት በስተቀር፡፡ ኤርትራ ከኢትዮጵያ የተገነጠለችበት፣ ኢትዮጵያ የባህር በር ያጣችበት የህግ ሂደት በጣም በብዙ ስህተቶች የተሞላ፣ የኢትዮጵያን ዘላቂ የሆነ ብሔራዊ ጥቅም ያላስከበረ፣ በአፈሙዝ ተፅዕኖ የተደረገ ነው፡፡ በጣም የሚያሳዝነው የኤርትራ ነፃነት እውቅና ሲሰጥ፣ በምላሹ ቢያንስ 20 ኪሎ ሜትር ስፋት ያለው ወደ ባህር መውጫ በር ኢትዮጵያ እንድታገኝ በዓለም አቀፍ ህግ ተቀባይነት ያለው ገዥ የሆነ ውል መዋዋል ያስፈልግ ነበር፡፡ የባህር ጠረፉ ረዥም ነው፡፡ ከራስ ዱሜራህ እስከ ራስ ካሳር ድረስ ከ1 ሺህ 200 ሜትር በላይ ይሸፍናል፡፡

ከመነሻው የኤርትራ ጥያቄ፣ ኤርትራዊያን ነፃ ወጥተው፣ በኢኮኖሚ አድገው የተሻለ ሀገር መፍጠርን ከግምት የከተተ አይደለም። ዋና ዓላማው ኢትዮጵያ ከውጭ ዓለም ጋር የምትገናኝበትን መውጫ በር መዝጋት ነው። ከውስጥ ኤርትራውያን የመጣ ሳይሆን በውጭ ሀይሎች የተጫነ ነው፡፡

የተባበሩት መንግስታት የባህር ህግ ኮንቬንሽን በአንቀፅ 125 እና 127 ላይ የባህር በር የሌላቸው ሀገራት ወደ ባህር የመዝለቅ መብት ይደነግጋል፡፡ የባህር በር የሌላቸው ሀገራት የባህር በር ባለው ሀገር በኩል ማንኛውንም የትራንስፖርት አማራጭ በመጠቀም ወደ ባህር መዝለቅ ይችሉ ዘንድ የባህር በር ያላቸው ሀገራት መተባበር እንዳለባቸው ያስቀምጣል፡፡ ባህር የመላው ዓለም ንብረት ነው፡፡ በዚህ ንብረት ላይ የኢትዮጵያ መርከቦች የመቅዘፍና የትራንስፖርት አገልግሎት የመስጠት ሙሉ መብት አላቸው፡፡ የባህር ጠረፍ ያላቸው ሀገራት የባህር በር የሌላቸው ሀገራት ባህር እንዳይጠቀሙ መከልከል አይችሉም፡፡

ከዚህ ባሻገር በንግግር፣ በሁለትዮሽ፣ ባለብዙ ወገን ድርድር፣ ሁሉንም አሸናፊ በሚያደርግ መንገድ የባህር በር ማግኘት የሚቻልበት መንገድ አለ፡፡ ይህ ካልሆነ ኤርትራ ከኢትዮጵያ የተለየችበት መንገድ ኢትዮጵያን የባህር በር አልባ ያደረገውን፣ የህግ መሰረት የሌለውን ሂደት በማንሳት የመከራከር መብት አለን፡፡

ሌላው መታወቅ ያለበት ልክ ዓባይ ላይ ግድብ እንዳይሰራ ሲደረግ እንደነበረው፣ የትኛውም 'የነፃነት ታጋይ ነኝ' ከሚል፣ የኢትዮጵያን ሀገረ መንግስትና ገዥ መንግስት ከሚቃወም ቡድን ጀርባ ግብፅ አለች፡፡ ደፈር ብሎ ኢትዮጵያ ወደብና የባህር በር ይገባታል የሚል መንግስት ካለ እንደ አደጋ በመውሰድ፣ ኢትዮጵያ ሁልጊዜ በውስጥ ጉዳዮቿ እንድትጠመድ ታሪካዊ ጠላቶች ይሰራሉ፡፡ ከኢትዮጵያ በተቃራኒ የሆነን ማንኛውንም ሀይል የጦር መሳሪያ በማስታጠቅ፣ ስልጠና በመስጠት፣ በፕሮፖጋንዳ፣ በዓለም አቀፍ ተቋማት፣ በጋዜጠኞች፣ በሰብአዊ መብት ተሟጋቾች ጫና ለመፍጠር እንደሚሰሩ ታይቷል፡፡

**አዲስ ልሳን፡- የባህር በር የማግኘት ጥያቄ እውን እንዲሆን ከኢትዮጵያውያን ምን ይጠበቃል?**

**አቶ ኪያ፡-** ጥያቄውን አጠናክሮ መቀጠል፤ የተለያዩ አማራጮችን ማቅረብ በተለይ ደግሞ ሰላማዊና ዲፕሎማሲያዊ አማራጮችን መከተል ያስፈልጋል። ትውልዱም የፖለቲካ አመራሩም ትኩረት ሰጥቶ፣ በውስጥ ያሉ ትናንሽ ችግሮችን፤ የብሔር ይሁን የኃይማኖት ልዩነትን ወደ ጎን በመተው፣ ኢትዮጵያን እንደ ሀገር፤ ኢትዮጵያውያንን እንደህዝብ አንድ የሚያደርግ አጀንዳ አድርጎ መሄድ ያስፈልጋል፡፡ የሽምግልና አማራጮችንም በደንብ መከተል ያስፈልጋል፡፡ የሁለቱ ሀገራት ህዝቦች (ኢትዮጵያና ኤርትራ) በባህል፣ በቋንቋና እምነት የተሳሰሩ ናቸው። መንግስታት ይቀያየራሉ፤ ህዝብ ግን ይቀጥላል፡፡ የሁለቱን ሀገራት ዘላቂ ጥቅም ግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ ዘላቂ የሆነ መፍትሔ ያስፈልጋል፡፡

**አዲስ ልሳን፡- ስለሰጡን ማብራሪያ እናመሰግናለን፡፡**

**አቶ ኪያ**፡- እኔም አመሰግናለሁ፡፡

# ማስታወቂያ

### የአማኑኤል ፀጋ የከተማ ንግድ ሱቅ ቤቶች ልማት አ/ማ 35ኛው መደበኛ እና 7ኛ ድንገተኛ የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ጥሪ ማስታወቂያ

የአማኑኤል ፀጋ የከተማ ንግድ ሱቅ ቤቶች ልማት አ/ማህበር የዳይሬክተሮች ቦርድ በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት 35ኛውን መደበኛ እና 7ኛ ድንገተኛ ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባኤ እሁድ ታህሳስ 12/2018 ዓ.ም ከጠዋቱ በ2፡30 ሰዓት ጀምሮ በገበያ ማዕከሉ የመሰብሰቢያ አዳራሽ ሁሉም የማህበሩ አባላት እና ሕጋዊ ተወካዮች በተገኙበት ጠቅላላ ጉባኤውን ያከናውናል፡፡

በመሆኑም የአክሲዮን ማህበሩ አባላቶች በሙሉ ለዚህ ጠቅላላ ጉባኤ ትኩረት በመስጠት የስብሰባው ተካፋይ እንድትሆኑ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን፡፡

- በጠቅላላ ጉባኤው ላይ መገኘት የማይችሉ አባላት እና ሕጋዊ ወኪል የሌለው ከስብሰባው ሁለት ቀን በፊት ጀምሮ በጽ/ቤቱ ተገኝተው የተዘጋጀውን የውክልና ፎርም በመሙላት ውክልና መስጠት ይችላሉ፡፡
- እያንዳንዱ አባል ወደ ስብሰባው ሲመጡ የታደሰ መታወቂያ /ፓስፖርት/፣ የመንጃ ፈቃድ እና የውክልና ሰነድ ይዘው መምጣት ይጠበቅባቸዋል፡፡
- ተወካይ ወደ ስብሰባው ሲመጡ የታደሰ መታወቂያ /ፓስፖርት/፣ የመንጃ ፈቃድ እና የውክልና ሰነድ ይዘው መምጣት ይጠበቅባቸዋል፡፡

**የመደበኛ ጉባኤው አጀንዳዎች**

- የዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት
- የ2017 በጀት ዓመት የውጭ ኦዲተር ሪፖርትን ማዳመጥ
- በጎደሉ የቦርድ አባል ምትክ የተመረጡትን ማጽደቅ
- የቁጥጥር ቦርድ አባል ማጽደቅ
- የውጭ ኦዲተርን አወዳድሮ መቅጠር

**የድንገተኛ ጉባኤው አጀንዳዎች**

- የአባላት ካፒታል ማሳደግ በተመለከተ

የዳይሬክተሮች ቦርድ

**የአማኑኤል ፀጋ የከተማ ንግድ ሱቅ ቤቶች ልማት አክሲዮን ማህበር**

---

አመልካች ሃና አሰፋ ዘውዱ ህጋዊ ተወካይ የሆኑት አቤል አሰፋ ዘውዱ በቀን 28/02/2018 ዓ.ም ባቀረቡት አቤቱታ መሰረት የካርታ ቁጥር ቦሌ9/15/7/4/4705/47575/01 ባቀረቡት አቤቱታ መሰረት የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የጠፋብኝ ስለሆነ በምትኩ እንዲሰጠኝ በማለት ሃና አሰፋ ዘውዱ ስም የተመዘገበ መጥፋቱ ተገልጾ ለፖሊስ ጣቢያ እና ለአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ እንዲጻፍልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

በመሆኑም ማህደራቸው ወጧልን በማንዋል ባጣራነው መሰረት በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት ሃና አሰፋ ዘውዱ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ የካርታ ቁጥር ቦሌ9/15/7/4/4705/47575/01 የሴሪ ቁጥር 065156 የተሰጠበት ቀን 11/12/08 ዓ.ም የቦታ ስፋት 147 ካ.ሜ የቦታ አገልግሎት ለመኖሪያ የሆነ የቦታው አገልግሎት ለመኖሪያ የሆነው ቤት ማረጋገጫ ካርታቸው የጠፋ ስለሆነ ቤቱን በዕዳ አስይዤዋለሁ የሚል አካል ለ30 ቀናት የሚቆይ የጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ እየጠየቅን ይህ ጋዜጣ ጥሪ ከተደረገ በኋላ ማህደሩን የምናደራጅ እና ኃላፊነት የማንወስድ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ አንዱዓለም ግርማ በጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 3 የቤት ቁጥር 211 ካርታ ቁጥር 32711 ተመዝግቦ የተሰጣቸው በእጃቸው መገኘት የነበረበት ካርታ የጠፋ በመሆኑ ይህንኑ አስመልክቶ የሚቀርብ ማንኛውም መቃወሚያ ካለ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ በ30 ቀን ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ ጉለሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ማስረጃውን ይዞ ካልቀረበ ካርታው እንደጠፋ ተቆጥሮ በምትኩ አዲስ ካርታ በማዘጋጀት አገልግሎት የምንሰጥ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የጉለሌ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በቂርቆስ ክፍለ ከተማ በአዲሱ ወረዳ 6 በቀድሞ ወረዳ 21 ቀበሌ 04 የቤት ቁጥር 386 በካርታ ቁጥር CKS 10/68/542/03 በቀን 08/06/2013 ዓ.ም በሴሪ ቁጥር 070616 እነ አስናቀች ካሳ (6 ሰዎች) ስም ተመዝግቦ የሚገኘው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ኮፒ ከማህደሩ ላይ የጠፋ ስለሆነ በማንኛውም ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ካለ ጋዜጣ ከወጣበት ቀን እስከ 30 ቀን ድረስ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ የመሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ይዞ እንዲቀርብ እየጠየቅን ይዤዋለሁ የሚል ከሌለ በምትኩ ሌላ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የቂርቆስ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

## ግልፅ የጨረታ ማስታወቂያ

በልደታ ክፍለ ከተማ ስር የሚገኝ ዳግም ህዳሴ ጤና ጣቢያ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ዕቃዎች በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል፡፡ በመሆኑም፡-

1. ሎት 1 የደንብ ልብስ የጨረታ ማስከበሪያ 4000 ብር
2. ሎት 2 የፅዳት እቃዎች የጨረታ ማስከበሪያ 4000 ብር
3. ሎት 3 እስቴሽነሪ እቃዎች የጨረታ ማስከበርያ 4000 ብር
4. ሎት 4 የቋሚ የፈርኒቸር እና ኤሌክትሮኒክስ እቃዎች የጨረታ ማስከበርያ 7000 ብር
5. ሎት 5 የጥገና ስራዎች እና የማስፋፋት ስራ የጨረታ ማስከበርያ 7000 ብር
6. ሎት 6 መድኃኒት እና የህክምና እቃዎች ጨረታ ማስከበርያ 7000 ብር

ስለዚህ ብቃት ያላቸውና በመስኩ የተሰማሩ ተጫራቾችን አወዳድሮ ግዢ መፈፀም ይፈልጋል፡፡ በዚሁ መሰረት፡-

1. በጨረታው ለመወዳደር ፋላጎት ያላቸው ተጫራቾች የታደሰ የንግድ ፈቃድ ያላቸው የዘመኑን ግብር የከፈሉ በመንግስት የግ/ን/አስ/ኤጀንሲ ላይ በአቅራቢዎች ምዝገባ ዝርዝር የተመዘገቡ የቲንና የቫት ተመዝጋቢ የሆኑና የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ፡፡
2. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ በባንክ የተረጋገጠ ሲፒኦ ብቻ ከጨረታ ሰነድ ጋር አያይዘው ማቅረብ የሚችሉ፡፡
3. ተጫራቾች ጨረታው በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ከወጣበት ዕለት አንስቶ ለ10 ተከታታይ የስራ ቀናት የማይመለስ ብር 200 (ሁለት መቶ ብር) በመክፈል ዳግም ህዳሴ ጤና ጣቢያ 4ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 409 በመምጣት የጨረታ ሰነድ መግዛት ይኖርባቸዋል፡፡
4. ተጫራቾች የመጫረቻ ሰነዶቻቸውን በታሸገ ኤንቨሎፕ ኦርጅናል እና ኮፒ ጋር ማስታወቂያው ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ10 ተከታታይ የስራ ቀናት ዳግም ህዳሴ ጤና ጣቢያ 4ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 409 በመምጣት ለጨረታ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡ እንዲሁም የጨረታ ማስከበርያ ሲፒኦ ከቴክኒክ ሰነድ ጋር አያይዘው ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
5. ጨረታው ተጫራቾች ወይንም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በ10ኛው ቀን ከቀኑ በ11፡00 ሰዓት ታሽጎ በ11ኛው ቀን በ4፡00 ሰዓት ዳግም ህዳሴ ጤና ጣቢያ 4ኛ ፎቅ ይከፈታል፡፡ የመክፈቻ ቀን ቅዳሜና እሁድ ወይም በበዓል ቀን ከሆነ በሚቀጥለው የስራ ቀን በተመሳሳይ ሰዓት ታሽጎ ይከፈታል፡፡
6. ተጫራቾች የጨረታ ሳጥኑ ከመከፈቱ በፊት ለተወዳደሩባቸው ሎት 1፣ ሎት 2፣ እና ሎት 3 የዕቃዎች ናሙና ማቅረብ የሚኖርባቸው ሲሆን ሎት 4 ድርጅቱ የሚያቀርበዉን እቃ በፎቶ እና ማኑዋል ዝርዝሩን በእስፔኩ መሰረት በፖስታ አሽጎ በሳምፕል መልክ ለግዢ ክፍል ማቅረብ አለበት እንዲሁም እንደ አስፈላጊነቱ የመስሪያ ቤቱ ጥራት ኮሚቴ ድርጅታችሁ ባለበት ቦታ ሄዶ እቃውን የሚያይ ይሆናል፡፡ በሎት 5 ደሞ መስሪያ ቤቱ ሳፕል በሚሰጠው መሰረት ዋጋ የሚሞላ ይሆናል በሎት 6 ተጫራች ባስገባው ዋጋ የሚወዳደር ሲሆን በሎት 7 ደግሞ ተጫራች መስሪያ ቤቱ ባስቀመጠው ዲዛይን እና ቦታውን በአካል አይቶ ዋጋ የሚሞላ ይሆናል፡፡
7. ተጫራቾች ለሚወዳደሩባቸው ዕቃዎች ለእያንዳንዱ ከቫት ጋር ያለውን ዋጋ ማስቀመጥ ይጠበቅባቸዋል፡፡ አሸናፊ ተጫራቾች ያሸነፉባቸውን እቃዎች በራሳቸው ትራንስፖርት ግዢ ፈፃሚው መስሪያ ቤት ድረስ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡
8. መስሪያ ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
9. መስሪያ ቤቱ ለጨረታ ካቀረባቸው እቃዎች ውስጥ እስከ 20% ድረስ ጨምሮ ወይም ቀንሶ የመግዛት መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**ማሳሰቢያ፡-** ተጫራቾች ለሚያቀርቡት ለእያንዳንዱ እቃ ዋጋ ከቫት ጋር ተሰርቶ መቅረብ አለበት

**አድራሻ፡- በልደታ ክፍለ ከተማ ዳግም ህዳሴ ጤና ጣቢያ ከአባ ጅፋር መስጊድ ከፍ ብሎ መሰረተ ዕድገት ት/ቤት ፊት ለፊት**

**ስልክ ቁጥር፡- 011-2-79-13-59/ 011-2-79-14-80/**

**በልደታ ክ/ከተማ ጤና ፅ/ቤት የዳግም ህዳሴ ጤና ጣቢያ**

---

### ቸነነም ትሬዲንግ አክስዮን ማህበር
### የስብሰባ ጥሪ ማስታወቂያ

አክስዮን ማህበሩ በስኬት ህንፃ አዳራሽ ህዳር 28 ቀን 2018 ዓ.ም በጠዋቱ 3፡00 ሰዓት በሚያደርገው ስብሰባ በሚከተሉት አጀንዳዎች ላይ ተወያይቶ ለመወሰን ስለሚፈልግ ጠቅላላ ጉባኤ አባላት ወይም ህጋዊ ውክልና ያላቸው የታደሰ መታወቂያ እና ህጋዊ ውክልና በመያዝ እንዲገኙ በድጋሚ በዚህ ጋዜጣ ማስታወቂያ እናሳውቃለን፡፡

**የስብሰባ አጀንዳዎች**

1.. አክስዮን ማህበሩ እንዲፈርስ ስለመወሰን፤

2.. የሒሳብ አጣሪ ስለመሾም፤

3.. ሌሎች በተጨማሪ የሚነሱ አጀንዳዎች ላይ ተወያይቶ መወሰን።

**ማስታወቂያ**፡- ተጨማሪ አጀንዳ ማስያዝ ከፈለጉ ስብሰባው ከመካሄዱ ከ5 ቀን በፊት በፅሑፍ ለጽ/ቤቱ ማቅረብ ይችላሉ።

**ቸነነም ትሬዲንግ አክስዮን ማህበር**

---

### ንብሮት ትሬዲንግ አክስዮን ማህበር
### የስብሰባ ጥሪ ማስታወቂያ

አክስዮን ማህበሩ በስኬት ህንፃ አዳራሽ ህዳር 28 ቀን 2018 ዓ.ም በጠዋቱ 4፡00 ሰዓት በሚያደርገው ስብሰባ በሚከተሉት አጀንዳዎች ላይ ተወያይቶ ለመወሰን ስለሚፈልግ ጠቅላላ ጉባኤ አባላት ወይም ህጋዊ ውክልና ያላቸው የታደሰ መታወቂያ እና ህጋዊ ውክልና በመያዝ እንዲገኙ በድጋሚ በዚህ ጋዜጣ ማስታወቂያ እናሳውቃለን፡፡

**የስብሰባ አጀንዳዎች**

1.. አክስዮን ማህበሩ እንዲፈርስ ስለመወሰን

እና ሒሳብ አጣሪ ስለመሾም፤

2.. ሌሎች በተጨማሪ የሚነሱ አጀንዳዎች ላይ ተወያይቶ መወሰን።

*ማስታወቂያ*፡- ተጨማሪ አጀንዳ ማስያዝ ከፈለጉ ስብሰባው ከመካሄዱ ከ5 ቀን በፊት በፅሑፍ ለጽ/ቤቱ ማቅረብ ይችላሉ።

**ንብሮት ትሬዲንግ አክስዮን ማህበር**

---

### መቻቻል ትሬዲንንግ አክስዮን ማህበር
### የስብሰባ ጥሪ ማስታወቂያ

አክስዮን ማህበሩ በስኬት ህንፃ አዳራሽ ህዳር 28 ቀን 2018 ዓ.ም ከሰዓት 6፡00 ሰዓት በሚያደርገው ስብሰባ በሚከተሉት አጀንዳዎች ላይ ተወያይቶ ለመወሰን ስለሚፈልግ ጠቅላላ ጉባኤ አባላት ወይም ህጋዊ ውክልና ያላቸው የታደሰ መታወቂያ እና ህጋዊ ውክልና በመያዝ እንዲገኙ በድጋሚ በዚህ ጋዜጣ ማስታወቂያ እናሳውቃለን፡፡

**የስብሰባ አጀንዳዎች**

1. አክስዮን ማህበሩ እንዲፈርስ

የሒሳብ አጣሪ ስለመሾም፣

2.. ሌሎች በተጨማሪ የሚነሱ አጀንዳዎች ላይ ተወያይቶ መወሰን።

*ማስታወቂያ*፡- ተጨማሪ አጀንዳ ማስያዝ ከፈለጉ ስብሰባው ከመካሄዱ ከ5 ቀን በፊት በፅሑፍ ለጽ/ቤቱ ማቅረብ ይችላሉ።

**መቻቻል ትሬዲንግ አክስዮን ማህበር**

---

### ወሄነት በሜና ትሬዲንግ አክስዮን ማህበር
### የስብሰባ ጥሪ ማስታወቂያ

አክስዮን ማህበሩ በስኬት ህንፃ አዳራሽ ህዳር 28 ቀን 2018 ዓ.ም በጠዋቱ 5፡00 ሰዓት በሚያደርገው ስብሰባ በሚከተሉት አጀንዳዎች ላይ ተወያይቶ ለመወሰን ስለሚፈልግ ጠቅላላ ጉባኤ አባላት ወይም ህጋዊ ውክልና ያላቸው የታደሰ መታወቂያ እና ህጋዊ ውክልና በመያዝ እንዲገኙ በድጋሚ በዚህ ጋዜጣ ማስታወቂያ እናሳውቃለን፡፡

**የስብሰባ አጀንዳዎች**

1.. አክስዮን ማህበሩ እንዲፈርስ ስለመወሰን፤

2.. የሒሳብ አጣሪ ስለመሾም፤

3.. ሌሎች በተጨማሪ የሚነሱ አጀንዳዎች ላይ ተወያይቶ መወሰን።

*ማስታወቂያ*፡- ተጨማሪ አጀንዳ ማስያዝ ከፈለጉ ስብሰባው ከመካሄዱ ከ5 ቀን በፊት በፅሑፍ ለጽ/ቤቱ ማቅረብ ይችላሉ።

**ወሄነት በሜና ትሬዲንግ አክስዮን ማህበር**

---

### ፀደይ ትሬዲንግ አክስዮን ማህበር
### የስብሰባ ጥሪ ማስታወቂያ

አክስዮን ማህበሩ በስኬት ህንፃ አዳራሽ ህዳር 28 ቀን 2018 ዓ.ም ከሰዓት 7፡00 ሰዓት በሚያደርገው ስብሰባ በሚከተሉት አጀንዳዎች ላይ ተወያይቶ ለመወሰን ስለሚፈልግ ጠቅላላ ጉባኤ አባላት ወይም ህጋዊ ውክልና ያላቸው የታደሰ መታወቂያ እና ህጋዊ ውክልና በመያዝ እንዲገኙ በድጋሚ በዚህ ጋዜጣ ማስታወቂያ እናሳውቃለን፡፡

**የስብሰባ አጀንዳዎች**

1.. አክስዮን ማህበሩ እንዲፈርስ ስለመወሰን፤ 2.. የሒሳብ አጣሪ ስለመሾም ፤ 3. ሌሎች በተጨማሪ የሚነሱ አጀንዳዎች ላይ ተወያይቶ መወሰን።

*ማስታወቂያ*፡- ተጨማሪ አጀንዳ ማስያዝ ከፈለጉ ስብሰባው ከመካሄዱ ከ5 ቀን በፊት በፅሑፍ ለጽ/ቤቱ ማቅረብ ይችላሉ።

**ፀደይ ትሬዲንግ አክስዮን ማህበር**

## የጠፋ ካርታ በጋዜጣ እንዲወጣ ስለማሳወቅ ይመለከታል

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በየካ ክ/ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ወረዳ 12 በወ/ሮ አበራሽ አለሙ ወልደማርያም ስም የተመዘገበ የኮንዶሚኒዬም ካርታ የቤት ቁጥር 016፣ የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000051207312፣ የተሰጠበት ቀን 12/01/2014 ዓ/ም እና የሴሪ ቁጥር C205442 የተመዘገበው ይዞታ ጠፋብኝ ብለው ማመልከቻ ማቅረባቸው ይታወቃል፡፡ በዚህ መሰረት ይህንኑ ይዞታ በጋዜጣ 90 ቀን ውስጥ በይዞታው መብት አለኝ የሚል እንዲያሳውቅ እና የጠፋ ካርታ በመሆኑ ከላይ የተጠቀሱት ግለሰብ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሬትና ምዝገባ መረጃ ኤጀንሲ የካ ቅርንጫፍ ማስታወቂያ እንዲወጣልኝ ሲሉ ያመለከቱ ስለሆነ ካርታው መጥፋቱን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባ መረጃ ኤጀንሲ የካ ቅርንጫፍ እንዲያሳውቅ እየገለጽን ይህ ባይሆን ለአመልካቹ አዲስ ካርታ ወጪ ተደርጎ የሚሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ወረዳ 08 የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ቁጥር W8-8-52-181-9183/02 ሴሪ ቁጥር 063075 የሆነው በወ/ሮ ፋጤ ኢብራሂም ስም የተመዘገበ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት(ካርታ)የጠፋባቸው መሆኑን በቀን 01/03/2018 ዓ.ም በመግለጽ ምትክ ካርታ እንዲሰጣቸው ያስታወቁን በመሆኑ በማናቸውም ምክንያት ይዤዋለሁ ወይም አግኝቼዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ቀን ጀምሮ እስከ በ30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ/ወ/ሮ/ሪት እነ ትዕግስት ሃ/ማርያም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቀድሞ ወረዳ 19 ቀበሌ 60 በአዲሱ ን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ወረዳ 11 የቤት ቁጥር 260 ነዋሪ የሆኑት በካርታ በቁጥር 16/33/4031/68543/01 የሴሪ ቁጥር 0119065 ይዞታ ማረጋገጫ ተመዝግቦ የተሰጣቸው ጠፋ የተባለው ስለተገኘ በማንኛውም ምክንያት ቀድሞ የታወጀው በአዲስ ልሳን ጋዜጣ መሻሪያ እስከ 20 ቀን ድረስ ድጋሚ ማስታወቂያ ከወጣበት ጊዜ አንስቶ በን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ይዞ/አስ/ጽ/ቤት ይቅረብ፡፡

ካርታው የተገኘ በመሆኑ ከአሁን በፊት ታህሳስ 30 ቀን 2011 ዓ.ም በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ----------------------- ላይ ጠፋ የተባለው የተሻረ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የን/ስ/ላ/ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 በ ዶ/ር ዳኛቸው ሺበሺ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ የ ካርታ ቁጥር ቦሌ17/155/89-4022/00 የሆነ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ የቤት ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንዲሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ወ/ሮ አስናቀች ለጋ ደበላ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 01 ክልል ውስጥ የሚገኝ ይዞታ ካርታ ተመዝግቦ የተሰጣቸው ካርታ ቁጥር 015213/B/2 የሴሪ ቁጥር 0237382 የይዞታ ስፋት 207 ካ.ሜ የሆነ ካርታ የጠፋባቸው መሆኑን ከፖሊስ ማስመዝገባቸውን በቁጥር ወ/መ/10/8187/18 በቀን 20/02/18 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ በተገለፀልን መሰረት ወጪውን ግለሰቡ በመቻል በጋዜጣ እንዲታወጅላቸው እየገለፅን በማንኛውም ምክንያት የጠፋው ካርታ ይዤዋለሁ የሚል አካል ካለ እስከ 30 ተከታታይ የስራ ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ፅ/ቤት ካላቀረቡ በምትኩ ሌላ ካርታ የምንሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በልዑልሰገድ ይልማ ስም የተመዘገበ በካርታ ቁጥር ለ/ኩራ/6/1/7/3/136421/00 የሴሪ ቁጥር 1662319 የተሰጠበት ቀን 21/07/2015 ዓ.ም የቦታው ስፋት በሰነድ 63.52 ካ.ሜ የሆነው ካርታ መጥፋቱ ተገልጾ ለፖሊስ እንዲጻፍልኝ በማለት አመልክተዋል።

በመሆኑም በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት ወረዳ 02 የሆነው መኖሪያ ቤት በልዑልሰገድ ይልማ ስም የተመዘገበ በካርታ ቁጥር ለ/ኩራ/6/1/7/3/136421/00 የሴሪ ቁጥር 1662319 የተሰጠበት ቀን 21/07/2015 ዓ.ም የቦታው ስፋት በሰነድ 63.52 ካ.ሜ የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ኦርጂናል የጠፋ ስለሆነ ይዞታ ቤቱን በዕዳ ይዤዋለሁ፤ አስይዤዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለተቋሙ እንዲያሳውቁን እያልን በዚህ ምክንያት ለ30 ቀናት የሚቆይ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ እየጠየቅን ይህ ጋዜጣ ጥሪ ከተደረገ በኋላ ካርታውን የምናዘጋጅ ይሆናል፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር በወረዳ 01 ክልል ውስጥ በአቶ ተስፋዬ ደሳለኝ አበበ ስም በይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000070104781 ሴሪ ቁጥር 020008 በሆነ የተመዘገበው ይዞታ፤ የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ/የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት/ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም መልኩ በእጁ ይገኛል የሚል አካል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን 28/02/2018 ዓ.ም ጀምሮ በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው መቅረብ የሚችሉ መሆኑን እያሳወቅን ይህ ካልሆነ በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 01 በካርታ ቁጥር 01/455/13433/00 በሴሪ ቁጥር 0653285 በመአዛ ንጉሴ ወንድሙ ተሰጥቷቸው የነበረው ማህደር የጠፋ ስለሆነ በባለጉዳዩ አናንያ መስፍን በኩል ስለደረሰን በማናቸውም ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል በጋዜጣ ከወጣበት እስከ 20 ቀን ድረስ ለንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት ድረስ አቤቱታ እንዲቀርብ፡፡ ይዤዋለሁ የሚል ከሌለ ሌላ ማህደር እንደሚከፈትላቸው እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የን/ስ/ላ/ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በስንቅነሽ በየነ አባተ ስም የተመዘገበ በካርታ ቁጥር ቦሌ/ሰሚ/158/5852/03 የሴሪ ቁጥር 021247 የተሰጠበት ቀን 05/09/03 ዓ.ም የቤት ቁጥር B158/12 የቤቱ ስፋት 47.02 ሜ.ካ የቤቱ አገልግሎት ለመኖሪያ የሆነ ኮንዶሚኒየም ቤት ካርታ መጥፋቱ ተገልጾ እንዲጻፍልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

በመሆኑም በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት ወረዳ 10 የሆነው መኖሪያ ቤት በስንቅነሽ በየነ አባተ ስም የተመዘገበ ቦሌ/ሰሚ/158/5852/03 የሴሪ ቁጥር 021247 የተሰጠበት ቀን 05/09/03 ዓ.ም የቤት ቁጥር B158/12 የቤቱ ስፋት 47.02 ሜ.ካ የቤቱ አገልግሎት ለመኖሪያ የሆነ ኮንዶሚኒየም ቤት የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ኦርጂናል የጠፋ ስለሆነ ይዞታውን (ቤቱን) በዕዳ ይዤዋለሁ፤ አስይዤዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለተቋሙ እንዲያሳውቁን እያልን በዚህ ምክንያት ለ30 ቀናት የሚቆይ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ እየጠየቅን ይህ ጋዜጣ ጥሪ ከተደረገበት በኋላ ካርታውን የምናዘጋጅ መሆኑን እየገለፅን የማስታወቂያው ወጪ በባለጉዳዩ የሚሸፈን መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአቶ አማረ ተፈሪ ማንደፍሮ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ይዞታ በልደታ ክ/ከ በአዲሱ ወረዳ 03 የቤት ቁጥር 1817 የካርታ ቁጥር ዱ2/05/208/1462/002130/01 በቀን 23/12/2010 ዓ.ም የተሰጣቸው ካርታ የጠፋባቸው በመሆኑ በጋዜጣ ታውጆ አገልግሎት እንዲሰጣቸው አመልክተዋል፡፡ በመሆኑም በጠየቁት መሰረት የምትክ ካርታ አገልግሎት ለመስጠት ያመቾ ዘንድ ከላይ በተጠቀሰው የባለይዞታው ስም የተመዘገበውን የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት /ኦርጂናል ካርታም ሆነ ኮፒውን/ ይዤዋለሁ የሚል ማንኛውም አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ልደታ ክ/ከተማ የመሬት ይዞታ መብት ምዝገባ መረጃ ኤጀንሲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ካልቀረበ በመመሪያ ቁጥር 61/2010 አንቀጽ 72 ንኡስ አንቀጽ 3 መሰረት በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ልደታ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በከፈለኝ ሀብቴ ሀብተሚካኤል እና ታከለ አድማሱ ስም የተመዘገበ በካርታ ቁጥር ለ/ኩራ5/47/5/59483/0175/2/02 የሴሪ ቁጥር 1644859 የተሰጠበት ቀን 19/04/2015 ዓ.ም የቦታው ስፋት በሰነድ 80 ካ.ሜ የሆነው ካርታ መጥፋቱ ተገልጾ ለፖሊስ እንዲጻፍልኝ በማለት አመልክተዋል።

በመሆኑም በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት ወረዳ 05 የሆነው መኖሪያ ቤት በከፈለኝ ሀብቴ ሀብተሚካኤል እና ታከለ አድማሱ ስም የተመዘገበ በካርታ ቁጥር ለ/ኩራ5/47/5/59483/0175/2/02 የሴሪ ቁጥር 1644859 የተሰጠበት ቀን 19/04/2015 ዓ.ም የቦታው ስፋት በሰነድ 80 ካ.ሜ የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ኦርጂናል የጠፋ ስለሆነ ይዞታ ቤቱን በዕዳ ይዤዋለሁ፤ አስይዤዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለተቋሙ እንዲያሳውቁን እያልን በዚህ ምክንያት ለ30 ቀናት የሚቆይ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ እየጠየቅን ይህ ጋዜጣ ጥሪ ከተደረገ በኋላ ካርታውን የምናዘጋጅ ይሆናል፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

# ተስፈኞቹ ከዋክብት

**በሳህሉ ብርሃኑ**

የዓለም አትሌቲክስ በየዓመቱ የወንዶች ‘ራይዚንግ ስታር’ (Men's Rising Star) ሽልማት እጩዎችን ይፋ ያደርጋል። የ2025ቱን እጩዎች የለየ ሲሆን ይህ ሽልማት ከ20 ዓመት በታች ባሉ አትሌቶች መካከል በዓመቱ ውስጥ የላቀ ብቃት ላሳዩ እና ለስፖርቱ ብሩህ ተስፋ ለሆኑ ኮከቦች የሚሰጥ ታላቅ እውቅና ነው። ዘንድሮም ልክ እንደሌሎች ዓመታት በአፍሪካ የሚገኙ ሶስት አዳጊዎች ለእጩነት መቅረባቸው አህጉሪቱ በአትሌቲክስ ውስጥ ያላትን ተሳትፎ ልክ ማሳያ ተደርጎ ተወስዷል።




ፎቶ- ከገፀ ድር

የዘንድሮው የዓለም አትሌቲክስ ‘ራይዚንግ ስታር’ ሽልማት እጩዎች

በእጩነት የቀረቡት የኢትዮጵያው ተስፋ አትሌት ቢንያም መሃሪ እንዲሁም የኬንያዎቹ የመካከለኛ ርቀት ኮከብ ፋኑኤል ኮዌች እና የ3 ሺህ ሜትር መሰናክል ሯጭ ኤድሙንድ ሴሬም ናቸው። እነዚህ ወጣቶች ያስመዘገቡት ውጤት በአዳጊዎች ደረጃ ብቻ ሳይሆን በአዋቂዎች የውድድር መድረክም ጭምር ነበር።

በሴቶች ዘርፍም እንደዚሁ ኢትዮጵያዊቷ አትሌት ብርቄ ሀየሎም በተስፈኛ አትሌት (ራይዚንግ ስታር) የዓመቱ ኮከብ ሽልማት የመጨረሻ እጩ ሆና ተመርጣለች፡፡ የ19 ዓመቷ አትሌት በአንድ ማይል፣ 5 ሺህ እንዲሁም በቤት ውስጥ ውድድሮች በ1 ሺህ 500 እና በ3 ሺህ ሜትር ከ20 ዓመት በታች የክብረ ወሰን ባለቤት ናት።

የአዳጊ ወጣቶች ዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮኗ ብርቄ ሀየሎም በዘርፉ ከቻይናዊያኑ የጦር ወርዋሪ ያን ዢ እና ከመዶሻ ወርዋሪዋ ዣንግ ዜይሊ የመጨረሻ እጩ ሆና ተመርጣለች። የዓለም አትሌቲክስ የምርጦች ምርጫ ከሳምንታት በኋላ በፈረንሳይ ሞናኮ ይፋ ሲደረግ ብርቄ ሀየሎም እና ቢንያም መሀሪ ይጠበቃሉ፡፡

የአትሌቲክስ የወደፊት ዕጣ ፈንታ በእጃቸው ነው የተባለላቸው እነዚህ አትሌቶች ገና በለጋ ዕድሜያቸው ያስመዘገቡት ሪከርድ እንዲሁም በአዋቂዎች መድረክ ላይ ጭምር ባሳዩት ብቃት የአትሌቲክስን የወደፊት ገጽታ የሚያሳዩ ስለመሆናቸው የዓለም አትሌቲክስ መረጃ ያሳያል፡፡

የኢትዮጵያው ተወካይ ቢንያም መሃሪ በረጅም ርቀት ላይ ያለውን ሁለገብ ተሰጥዖ በማሳየት በሁለት ዋና ዋና የዓለም ከ20 ዓመት በታች ሪከርዶች ላይ ስሙን አኑሯል። በኬንያ በኩል የቀረቡት ፋኑኤል ኮዌች እና ኤድሙንድ ሴሬም በአጭርና ረጅም ርቀቶች ላይ ያሳዩት የበላይነት የትውልድ ሽግግሩ ምን ያህል ፈጣን እና ጠንካራ እንደሆነ ያመላክታል።

አትሌት ቢንያም መሃሪ እ.ኤ.አ በ2025 የላቀ ብቃት በማሳየት በረጅም ርቀት ሩጫ ዓለምን ያስደመመ ወጣት ነው። ቢንያም በልጅነት ዕድሜው በአንድ የውድድር ዘመን ውስጥ በርካታ ርቀቶችን በተሳካ ሁኔታ የመቆጣጠር ችሎታውን አሳይቷል።

የቢንያም ዝና የጀመረው በቤት ውስጥ የ3 ሺህ ሜትር ሩጫ ላይ ባስመዘገበው ድንቅ ሰዓት ነው። በሊቪን በተካሄደ ውድድር ላይ 7:29.99 በመግባት የዓለምን ከ20 ዓመት በታች የቤት ውስጥ የ3 ሺህ ሜትር ሪከርድ ሰብሯል። ይህ ውጤት በታሪክ ውስጥ ከ20 ዓመት በታች ባሉ አትሌቶች ያልታየ ፈጣን ሰዓት ሆኖ ተመዝግቧል። ይህን ታሪካዊ ስኬት ባስመዘገበ በጥቂት ወራት ውስጥ ቢንያም በረጅም ርቀት ላይ ያለውን የበላይነት ዳግም አረጋግጧል፡፡ የኦሎምፒክ ማጣሪያ ውድድር በ10 ሺህ ሜትር ርቀት 26:37.93 በመግባት ለ19 ዓመታት የዘለቀውን የሳሙኤል ዋንጂሩን የዓለም ከ20 ዓመት በታች ሪከርድ ሰብሯል።

ቢንያም ከእኩዮቹ ጋር ከመወዳደር ባሻገር በአዋቂዎች መድረክ (ሲኒየር ውድድሮች) ላይ መወዳደር መቻሉ ልዩ ትኩረት እንዲያገኝ አድርጎታል። በቶኪዮ በተካሄደው የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና ላይ በ5 ሺህ ሜትር ፍጻሜ ላይ በመሮጥ አምስተኛ ደረጃን መያዝ ችሏል።

በአዋቂዎች የዓለም ሻምፒዮና ላይ በ20 ዓመት ዕድሜ ወይም ከዚያ በታች ሆኖ ይህን ያህል ከፍተኛ ደረጃ መድረስ የእርሱ የላቀ ብቃት እና የአዕምሮ ጥንካሬ ማሳያ ነው። በዚህ አፈጻጸሙ ቢንያም መሃሪ የኢትዮጵያ የወደፊት የረጅም ርቀት ሩጫ አምባሳደር መሆኑን አስመስክሯል። የሱ ሁለገብነት እና በሪከርዶች ላይ የተመዘገበው ስም ለሽልማቱ ብቁ ተፎካካሪ ያደርገዋል።

አትሌት ፋኑኤል ኮዌች በኬንያ በመካከለኛ ርቀት ሩጫ ያለውን ውጤታማነት ያስቀጠለ አትሌት ነው። በእሱ ዘርፍ ‘Dream Mile’ ተብሎ በሚጠራው የ1 ሺህ 500 ሜትር ሩጫ ላይ የሰበረው ሪከርድ ለአትሌቲክስ ታሪክ አዲስ ምዕራፍ ከፍቷል።

የኮዌች የ2025 የውድድር ዘመን የደመቀው በፓሪስ ዳይመንድ ሊግ ላይ ባስመዘገበው ውጤት ነው። በወቅቱ በ3:27.72 አስደናቂ ሰዓት በመግባት የዓለምን ከ20 ዓመት በታች የ1 ሺህ 500 ሜትር ሪከርድን በመስበር የዓለምን መገናኛ ብዙሃን ትኩረት ስቧል። ይህ ሰዓት በዓለም አቀፍ ደረጃ በ1 ሺህ 500 ሜትር ውድድር ላይ ካሉት ፈጣን ሰዓቶች አንዱ ሲሆን፣ ኮዌች በአዳጊ ዕድሜው ይህን ብቃት ማሳየቱ ለወደፊት በሞሮኮው ሂሻም ኤል ገርሩጅ ሪከርድ ላይ ተፎካካሪ ይሆናል የሚል ግምት እንዲፈጠር አድርጓል።

ሪከርድ ከመስበር ባሻገር፣ ፋኑኤል ኮዌች በዳይመንድ ሊግ ውድድሮች ላይ ወጥነት ያለው አፈጻጸም አሳይቷል። በለንደን የዳይመንድ ሊግ ላይ አሸናፊ በመሆን በትልልቅ ውድድሮች ላይ ጫናን ተቋቁሞ የማሸነፍ ብቃቱን አስመስክሯል። በኦስትራቫ ጎልደን ስፓይክ (Golden Spike) ውድድር ላይም ድል ማድረጉ የ1 ሺህ 500 ሜትር ሩጫ የረዥም ጊዜ መሪ ለመሆን ዝግጁ መሆኑን ያሳያል።

ኬንያ በ3 ሺህ ሜትር መሰናክል ሩጫ የዓለም የበላይነት ያላት ሀገር ስትሆን፣ ኤድሙንድ ሴሬም ይህንን የበላይነት እያስቀጠሉ ካሉ አዲስ ትውልዶች አንዱ ነው። በአዳጊነት ዕድሜው በአዋቂዎች ዓለም ላይ መደፈር መቻሉ ሽልማቱ ላይ ጠንካራ ተፎካካሪ አድርጎታል።

የሴሬም ዋናው ስኬት በቶኪዮ በተካሄደው የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና ላይ በ3 ሺህ ሜትር መሰናክል ውድድር የነሐስ ሜዳሊያ ማግኘቱ ነው። በሲኒየር (አዋቂ) የዓለም ሻምፒዮና ላይ ከምርጥ አትሌቶች ጋር ተወዳድሮ የሜዳሊያ ቦታ መያዝ በራሱ ታላቅ ስኬት ተደርጎ ተመዝግቦለታል። በተጨማሪም ሴሬም የዓለም ከ20 ዓመት በታች የአትሌቲክስ ሻምፒዮና በ3 ሺህ ሜትር መሰናክል የወርቅ ሜዳሊያ አሸናፊ ሲሆን፣ በዘርፉ አቻ እንደሌለው አስመስክሯል።

በሞናኮ በተካሄደው የሄርኩለስ ውድድር ላይ ሴሬም ያስመዘገበው 8:04.00 የግል ምርጥ ሰዓት ደግሞ በአዳጊ ዕድሜው ምን ያህል የላቀ ብቃት እንዳለው ያሳያል። የሴሬም ቴክኒክ፣ ፍጥነት እና በውድድር ጊዜ ያለው የጥንቃቄ ደረጃ ለሽልማቱ ጠንካራ ተፎካካሪ የሚያደርጉት ብቃቶች ናቸው።

የ2025 ‘የወንዶች ራይዚንግ ስታር’ ሽልማት እጩዎች ሦስቱም ከአፍሪካ መሆናቸው የአህጉሪቱን በሩጫ ስፖርቶች ያለውን የላቀ ችሎታ ዳግም ያረጋገጠ ክስተት ስለመሆኑ አፍሪካን ኒውስ ዘግቧል። ኢትዮጵያ እና ኬንያ በሩጫው ዓለም የገዘፈ ስም ያላቸው ሀገራት ሲሆኑ፣ እነዚህ አዳጊዎች የሁለቱን ሀገራት የወደፊት ተተኪዎች ሆነው መቅረባቸው የአህጉሪቱ የአትሌቲክስ ውጤታማነት እንደሚቀጥል ምልክት የሰጠ ሆኗል። እንደዚሁም የእነዚህ የቀጣይ ዘመን ኮከቦች ወደ ዋናው መድረክ መምጣት ከወዲሁ በ2028 እና በ2032 ኦሎምፒክ ጨዋታዎች ላይ ከፍተኛ ተፎካካሪዎች እንደሚሆኑም ተስፋ ተጥሎባቸዋል፡፡

የዘንድሮው የወንዶች ‘ራይዚንግ ስታር’ ሽልማት አሸናፊ የሚታወቀው እ.ኤ.አ ህዳር 30 ቀን 2025 ዓ.ም በሚካሄደው የዓለም አትሌቲክስ ዓመታዊ የሽልማት ድግስ (World Athletics Awards) ላይ ነው። የሽልማቱ አሸናፊነት ከታላቅ የገንዘብ ሽልማት ባሻገር፣ ለአትሌቶቹ ቀጣይ የስፖርት ጉዞ ዓለም አቀፍ ዕውቅና እና የስፖንሰርሺፕ ዕድሎችን ይከፍታል። ከሦስቱ ታላላቅ ተወዳዳሪዎች መካከል ማን ያሸንፋል? የሚለው ጥያቄ በዓለም አትሌቲክስ ደጋፊዎች ዘንድ ትኩረት የሚስብ የውይይት ርዕስ ሆኖ የቀጠለ ሲሆን፣ ከዚህ ቀደም ኢትዮጵያዊው አትሌት ሰለሞን ባረጋ የዘርፉን ሽልማት መውሰዱ የሚታወስ ነው፡፡

የወንዶች ራይዚንግ ስታር (Men's Rising Star) ሽልማት ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ በይፋ መሰጠት የተጀመረ ሲሆን፣ ሽልማቱ የሚሰጠው በዓለም አትሌቲክስ ምክር ቤት፣ በብሔራዊ አትሌቲክስ ፌዴሬሽኖች እና በአትሌቲክስ ቤተሰብ ድምፅ ውሳኔ እንደሆነ የዓለም አትሌቲክስ መረጃ ያሳያል፡፡